
# ላንዳፍታ

# LANDAFTA

*An Amharic Entertainment Magazine*
*Volume 2 No. 2 July 1993.* $2.50
ሰኔ ፲፱፻፹፭ ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፪

**የአማርኛ የመዝናኛና የቤተሰብ መጽሔት**







አልማዝ ደምሰውን ማን ገደላት ?
(ገጽ ፲፪)

የትዳር ጓደኛ ይፈልጋሉ?
(ገጽ 30)












« የተለያየነው በዘር አይደለም »
(ገጽ 7)





# የኢትዮጵያ
# መንደር







# ETHIO VILLAGE
## CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE

ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ገቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

ዘውትር ቅዳሜ ምሽት

መስፍን ዓለሙ በክራሩ ከአቡጊዳ ባንድ ጋር

ያስደስቷችኋል።



መስፍን ዓለሙ በክራሩ

# ማ ው ጫ


ከአዘጋጁ 2

ደብዳቤዎች 4

እናስተዋውቃችሁ 7

"ዳሎል የተከፋፈለው በዘር ልዩነት አይደለም !!"

ልዩ ክፍል 12

"የአሜሪካኑ ሕልም ቅዠት ሲሆን"

የአልማዝ ደምሰው ግድያ

ልብወለድ 13

"ትላንት ማታ በሕልሜ" (ከደምሌ አያሌው)

"የዘመድ ደብዳቤ" (ከማቱሳላ ነጋሽ)

"የዲብራ ጦስ" ካለፈው የቀጠለ (ከገረሱ)

አዳምና ሐዋን 24

"ጋብቻን በዕቅድና በጥናት" (ከየሠራህ ወርቅ አ.አ.)

"ሴቶች ምን ይላሉ?" "ወንዶችስ ምን ይላሉ?"

"እኔ ልጅት የአበሻ ወንድ አልጠይቅም" (ከኤደን)

ጓደኛ ለሚፈልጉ

"ልጅ የሌላት መውለድ ግን የምትፈልግ" (ከኤደን)

"በወንዶች ላይ ያለኝን ጥላቻ እንዴት አጠፋለሁ?" (ከእታለም)

ኑሮ በአሜሪካ 36

"እየተስተዋለ እንጂ!" (ከገረሱ)

"የኛ ልጆችና የባህር ማዶ ስማቸው" (ከግርማ ዘገየ)

"ስለ ምግብ አወሳሰዳችን ጥቂት"

የአበው ቅርስ 40

ተረትና ምሳሌዎች / ከአማርኛ ቅኔዎች

የዘፈን ግጥሞች 41

ቢስቁም ባይስቁም 44

ጨዋታና ሰንጠረዥ 46



በላንዳፍታ መጽሔት ላይ የሚወጡትን ማናቸውንም ጽሑፎች በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ማስተላለፍም ሆነ በተመሳሳይ መንገድ አባዝቶ ለማሰራጨት በቅድሚያ የአዘጋጁንና የጽሑፍ ደራሲውን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።


የሽፋን ፎቶ፤- የ"ዳሎል" ባንድ በኋላም የ"ባሮ"ና የ"ጊዜ" ባንድ አባላት፤

ላንዳፍታ
LANDAFTA
*P.O.Box 49301*
*Atlanta, GA 30359*
*Phone (404)728-9122*

ዋና አዘጋጅና አሳታሚ
መኰንን ገሠሠ

Publisher/Editor
Mekonnen Gessesse

**EDITORIAL ADVISORS**
Dr. Aberra Molla
Girma Zegeye
Abera Sisay
Dawit Deres
Zelleke Nigatu
Dr. Tilahun G. Hiwot
Haile Demissew
Solomon Mellese
Betelihem Girma -Typist

# ከአዘጋጁ

እንደምን ከረማችሁ። መቼም በመዘግየታችን ቅር ሳትሰኙ አልቀራችሁም። ምክንያት ኖሮንነው። አዘጋጅዋ በሥራ ምክንያት ወደ አትላንታ በመዛወሬ "ላንዳፍታ"ም አብራኝ ተዛውራ ለመታተም ሁኔታው እስኪመቻችላት ነበር። ላንዳፍታ የተወለደችበትን ችካጐን ምን ጊዜም አትረሳም። መጽሔቷን ለማሳደግ የቺካጐና አካባቢው ኢትዮጵያውያን ያደረጉትን አስተዋጽዖ ሁል ጊዜ የማስታውሰውና ከልብእንዳመሰግን የሚያደርገኝ ነው። እንግዲህ አትላንታዎች እንዴት እንደሚያስተናግዱት ደግሞ በጉጉት የምጠብቀው ይሆናል።

የላንዳፍታ የኢትዮጵያ ተወካይ ብራና አሳታሚ ድርጅት ጋር ያለን ግኑኝነት በአንዳንድ ምክንያቶች በመቋረጡ የዚህኛው እትም በኢትዮጵያ የመታተሙ ጊዜ ትንሽ ሊዘገይ እንደሚችል ከይቅርታ ጋር እገልጻለሁ። በዚሁ ከብራና አሳታሚዎች ጋር ያለንን ግኑኝነት መቆሙን ሳላገልጽ አላልፍም።

በዚህኛው እትም እንደከዚህ በፊቱ ሁሉ ሰፋ ያለ ዝግጅት ይዘን ቀርበናል።

## የዳሎል ባንድ . . .

በ"እናስተዋውቃችሁ" አምዳችን ቀደም ብሎ የዳሎል ባንድ አሁን "በሮ"ና "ጊዜ" ተብለው የተከፈሉትን ጠቅላላ ታሪካቸውን ይዘን ቀርበናል።

## በአሜሪካ አገር ተገድለው ስለተገኙ ኢትዮጵያውያኖች፤ •

"ልዩ ክፍል" በሚል ደግሞ በቅርቡ ኦርላንዶ ፍሎሪዳ በምትሠራበት ሆቴል ተገድላ ስለተገኘችው ወገናችን አልማዝ ደምሰው ያጠናቀርነውን አቅርበናል። ቺካጐም እንዲሁ መኖሪያ ቤቱ ውስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሎ ስለተገኘው ሉልሰገድ ገ. ሕይወት በመጠኑ ጽፈናል። የሉልሰገድን ታሪክ በሚቀጥለው እትም ሰፋ አድርገን ለማቅረብ እንሞክራለን። በዚሁ አጋጣሚ ልናሳስብ የምንፈልገው አንድ ቁም ነገር አለ። የዚህ ዓይነቱ አሰቃቂ ተግባር በኢትዮጵያውያን ላይ በየቦታው ደርሶ የተደረጉት ግድያዎች ደምበኛ ክትትል ሳይደረግላቸው እየቀረ ገዳዮቹ ሳይያዙ መቅረታቸው በሰፊው ይወራል። ለዚህ ምክንያቱ ምናልባትም "ማን ተከታታይ" አለ በሚል ንቀትም ወይ ግዴለሽነትም ይሆናል። እዚህ ላይ የእኛ የተጠናከረ ትብብር ግፊት ስለሚፈጥር "ነገሩ ነግ በኔ" ነውና ተባብረን ድምጻችንን የምናሰማበት ሁኔታዎች መፍጠር እንዳለብን ሳንጠቁም አናልፍም። በችካጐ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ያደረገው ሙከራ የሚያኮራ ጅምር ነው። በውጭ አገር በስደትም ሆነ በተለያየ መልኩ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን አገር ውስጥ ባለው ሁኔታ ምክንያት የተለያየ አመለካከቶችና የፖለቲካ ዝንባሌዎች ሊኖረን ይችላል። ባብዛኛው ግን አንድ የሚያደርጉን ነገሮች ያይላሉ። ልዩነትን አቻችሎ አብሮ በመኖር በስደት ኑሮ የሚገጥሙንን ችግሮች በጋራ የምንወጣበትን ዘዴ ብንቀይስ ጥሩ ይመስለናል። እንድንናቅም የሚያደርገን ልዩነቶቻችንን እያጐላን ስለምንከፋፈል ነው እንላለን።

## በሌሎች አምዶች፤

ብዙ ጓደኛ ፈላጊዎች ቀርበዋል። የአዳምና ሔዋን አምዳችን ሰፋ ባለ መልኩ የብዙ አንባብያንን አስተዋጽዖ ይዞ ቀርቧል። ሶስት ልብወለዶችም አሉን። በሽ በሽ ነው። ጨዋታዎችም አቅርበናል።

## በመጨረሻም፤

"ላንዳፍታ" በየሁለት ወሩ የምትወጣበትን ሁኔታ በማመቻቸት ላይ ነን። በአትላንታ አካባቢ የምትኖሩ በስነጽሑፍ፤ በአማርኛ የኮምፒውተር ፊደል ለቀማ (ModEth) ልምድ ያላችሁ እባካችሁ ደውሉና እነጋገሩን። ተባብረን ይህችን ማህበራዊ መጽሔታችንን እናሳድጋት።

# ለላንዳፍታ መጽሔት ወዳጆች መልዕክት

ላንዳፍታ ቤተሰባዊና ማህበራዊ መጽሔት በመሆኗ የሁሉን ሕይወት በሚዳስሱ ጉዳዮች ላይ ስለምታተኩር ብዙ ወዳጆች ለማፍራት ችላለች። ውድ አንባብያን የዚችን መጽሔት ዕድገት በመሻት የምትወጣበት ጊዜ እንዲያጥር በተደጋጋሚ ጠይቀዋል። በኛም በኩል አስፈላጊውን መሰናዶ በማጠናቀቅ ላይ ስንሆን አንባብያንን ከዚህ በታች በዘረዘርናቸው ጉዳዮች ላይ ትብብር እንዲያደርጉልን በትህትና እንጠይቃለን።

1ኛ. ደምበኞቿ ሲበዙ መጽሔቷም ታድጋለችና መጽሔቷን ለጓደኛ፣ ለዘመድ ለምታውቁት ሁሉ እንድታስተዋውቁልን። በተጨማሪም የደምበኝነት ቅጹን በማደል ብዙ ደምበኞች እንድናፈራ እንድትረዱን።

2ኛ. መጽሔቷን በምትገኙበት ቦታ ለማከፋፈል ብትተባበሩን። አስራአምስትና ከዚያ በላይ በመውሰድ ለሚያከፋፍልልን ሰው ከሺያጩ በስምምነት ከ20 – 25 በመቶ ለመክፈል ዝግጁ ነን። ደውሉልን ወይም ኮሚሽኑን በመቀነስ መኒ ኦርደር በላንዳፍታ ስም በማሠራት ብትልኩልን ወዲያውኑ እንልካለን።

3ኛ. በዚህ አገር ከሚገኙ ሌሎች ኮሚኒቲዎች እንደምንማረው መደጋገፍ ኃይል ነውና ድርጅት ወይም የንግድ ሥራ ያላችሁ በመጽሔቷ ላይ በማስተዋወቅ እንድንረዳዳ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ስለዝርዝር ሁኔታው በመጽሔቱ ሽፋን ጀርባ የውስጥ ገጽ ይመልከቱ።

4ኛ. የአንዲት መጽሔት ዕድገት የአንባብያን የጽሑፍ አስተዋጽዖ ስለሆነ የጽሑፍ ችሎታ ኖራችሁም አልኖራችሁ፣ ልቦለዶችን፣ የአሜሪካኑሮ ገጠመኞችን፣ ግጥሞችን፣ ተረትና ምሳሌዎችን። ወዘተ . . እንድትልኩልን።

በመጨረሻም መጽሔታችንን አብረን ለማሳደግ እንተባበር።

መጽሔቱ በጊዜ እንዲደርሶት
ገጽ 48 ላይ ያለውን የደምበኝነት
ቅጽ ሞልተው ከክፍያው ጋር
ይላኩ።

**LANDAFTA**
**P.O.BOX 49301**
**Atlanta, GA 30359**


ሞዴት ~ ModEth

የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያ
Ethiopian Word Processor

• COMING UP !

Windows To DOS ModEth

ከዊንደውስ ወደ ሞዴት

የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር
Ethiopian Computers and Software
9781 W. Fremont Pl.,
Littleton, CO 80123
Phone (303) 972-2186
Fax (303) 973-4342

# ደብዳቤዎች

ለላንዳፍታ አዘጋጅ፤

"እዉነተኛ ኢትዮጵያዊ ናቸዉ!"

በቅድሚያ ሠላምታዬ ይድረሳችሁ "...እኔን እንደዚህ ያደረገኝን ወታደር ስለእሱ ነዉ ተናገር የምትሉኝ? ይቅርታ አድርግከት ነዉ የምትሉኝ? ...ካላችሁ አደርግለታለሁ፤ ለአገሬ ባለኝ ፍቅር አደርግለታለሁ፤ ያ የሆነዉ በአዝማቾቹ ነዉ። ያገሬን ሉዓላዊነት አስጠብቆ የቆየዉ ጦር አባላቱ ወገኖቼ ስለሆኑ ሲሰቃዩ ማየት ቀርቶ መስማት አልፈልግም።..." ከእዉነተኛ የአገር ልጅ የሚጠበቅ ዋጋዉን ለመተመን የሚያስቸግር እጅግ በጣም ታላቅ አባባል ነዉ። ወገን ለወገኑ መቆርቆርም አለበት። በደል ያደረሰ ቢሆን እንኳ ይቅርታም ይደረጋልና ለዚህ ወገንስ ችግሩን ለማየትና ለመስማት አለመፈለግን የመሰለ አስተዋይነት ከቶ ምን አለ? ስለሬጀንት ፕሮፌሰር ጌታቸዉ ኃይሌ ያነበብኩት ጽሑፍ እጅግ በጣም አርከቶኛል። ምን አይነት የተመረቁ ኢትዮጵያዊ ምሑር ናቸዉ እባካችሁ? እግዝአብሔር እድሜያቸዉን ያርዝምልን፤ ቤተሳባቸዉንም ክፉ አይንካዉ፤ እሳቸዉ አሁንም ገና ሌላ እመርታ ለማሣየት በብርታት እየሠሩ ነዉ እባካችሁ ላንዳፍታዎች ለኚህ ታላቅ ያገር ልጅ ይበርቱ! በሉልን። ፕሮፌሰር ጌታቸዉ በእስከዛሬዉ መልካም ሥራቸዉ የማካርተር ፋዉንዴሽን ፌሎ ሺፕ ከፍተኛ ተሸላሚ መሆንም ማንነታቸዉን እንድናዉቅ አድርጎናል። እባካችሁ በዉጭ አገር በተለያየ የሥራ ዘርፍ ላይ የሚገኙትን ብርቅዬ የአገራችንን ምሑራን አስተዋዉቁን። በማንኛዉም ግዜ ዉለታችሁን አንዘነጋዉምና።

ሬጀንት ፕሮፌሰር ጌታቸዉ ኃይሌ በተለይ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ችግር ላይ ስላለዉ የወታደሩ ክፍል አባላት የተናገሩት ለብዙ ሰዎች እና ቡድኖች ንፁህ አእምሮ ካለ ታላቅ ትምህርት እንደሚሰጥ እርግጠኛ ነኝ። በዚሁ አጋጣሚ ለ"ላንዳፍታ" ም ምስጋናዬን እያቀረብኩ ይኸው በጉ የትዉዉቅ ጅመር ይለመድ እያልኩ እሰናበታለሁ።

በቸር ይግጠመን

የሠራህ ይወቅ

ከአዘጋጁ፤- አቶ የሠራህ ወርቅ፣ ስላኩልንን መጣጥፎች በአንብብያን ስም በጣም እናመሰግናለን። ቦታና ርቀት ሳያግደን መወያየት መቻላችን ያሳደስተናል። ምስጋናዎን ተቀብለናል። በበኩላችንም የምንችለውን ያህል ለማድረግ ቃል እንገባለን። ይጻፉልን።

---

ለውድ ወንድሜ የላንዳፍታ አዘጋጅ፤

እንደምን አለህልኝ ውድ የላንዳፍታ አዘጋጅ፤ እግዚአብሔር ይመስገን እኛ ደህና ነን። እኛም ዘንድ መሸቶ ይነጋል። እንደ አቅሚቲ ሩጫ ነው። ኑሮን ከብልሃቱ ለማገጣጠም እንታከታለን። አድሮ በበነጋታው ለመገኘት እንሮክታለን። አባዜዋ የማያልቅባት አቢሲኒያ ኑሮዋ ሽቅብ ብሎ ነገር ባይሆንላትም ቁልቁል የመሄዱን ነገር አሳምሮላታል። የሰው ልጅ ኑሮውን ይመስላል እንዲሉ ኑሮአችንን ለመምሰል እኛምእየቀደምነው እንንደረደራለን።

ደግሞም እርም የለን ሆኖ ሽቅብ ያለውም ያምረናል። ሳይሆንልን ሲቀር ምቀኝነታችን አይጣል። ተያይዘን ተጠላልፈን ቁልቁል ለመውረድ እየስርቻው እናደባለን። በቁልቁለት ቁልቁለቱ ሶማሌዎች ቀድመውን ካልሆነ በቀር ሌላም ተፎካካሪ የለብን። አቢሲኒያ የጉድ አገር ናት። ውጭ ባላችሁት ምንኛ እንደምንቀና ልነግርሀ አልችልም። እዚያስ የሚቀናበት ነገር ይኖራችሁ ይሆን? ምልቶ ተርፎ እንዳትለኝ፤ እኔ አላውቅም ብቻ። ሁላችንም በሀሳብ እናንተ ዘንድ ተጉዘን ተጉዘን ልባችችን ወልቋል። "ያሰበውን ያላገኘ ልብ ሁሌም መንገደኛ ነው፤" ይባል የለ። ይህችን "ቅርንጥሳም" አገር ትተን እግር እወሰደበት የትም ለመድረስ፤ እንደተተኮሰበት ድኩላ እንዱ ዘንድ ጭልጥ ለማለት ያላቆበቆበ ልብ ከስንት አንድ ነው። ድሮ ድሮ ተማሪ ሆነን በተረት እንደምናውቃት ፤-ቡቱ ቡቱቱ፤

"አንቺ ድሃ ቅርንጥሳም፤
ቡቱ ቡቱቱ፤
እናት የለሽ አባት የለሽ፤
ሰው አይወጣልሽ፣ ልጅ አያድግልሽ፤
የአገር ማፈሪያ ድራሽሽ ይጥፋ፣
ውሻ ይብላሽ፣ እግዜር ይድፋሽ።"

ብለናት እብስ ለማለት፣

እንዲህ አይምሰልህ ግን በየልባችን ያለው። ለነገሩስ እርሷስ መች ትለቃለች! እዚያ እተኬደበትስ አገር ሰላም አትነሳ አትናፍቅ ይሆን? እኔ አላውቅም። ብቻ እርሷም አልደላት፤ የበቀልንባትም ደልቶን አላፈራን፤ አንዱን ቀን ተያይዘን ዘፍ ሳንለው አንቀርም።

የአምባወርቅ ከአ.አ.

---

ለ"ላንዳፍታ" አዘጋጅ፣
መጽሔቴችሁ በርቱ ተበራቱ የአገር ልጆች የምታሰኝ ፣ በውጭ ያሉ ምሁራኖቻችንን፤ በስደት የሚንከራተቱትን የአገርና የወገን ፍቅር ያላቸውን ኢትዮጵያውያን እየጋበዘች የምታስተዋውቀን፣ ትዳር እንድንይዝ የምትገፋፋንና አጋዥ የሆነችን፣ በተጨማሪም አዝናኝ መጽሔት ናት። ታዲያ ስለአገራችንም ታሪክ ሆነ ሌላ ጉዳይ ማወያየትስ ምን ይመስላችኋል? በወዳጅነት እንሰንብት፣ ጽሑፎችን እልካለሁ። በርቱ።

ሰለሞን ከበደ (ዊንድሰር፣ ካናዳ)

---

በስመ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን! ሰላም ላንዳፍታዎች፣ መጽሔታችሁ እንደማር ጣፋጭ ሆና ስርጭቷ ደግሞ እንደ መስቀል ወፍ ውድ ሁነች። ብታስቡበት ደግ ነው። እዚህ ተወካዮቻችሁ ምን ነካቸው? በሉ ቅዱስ እግዜአብሔር አብ በቸር ይጠብቃችሁ። በሰላም ላገራችሁ ያብቃችሁ። በርቱ።

ዳንኤል ዮሴፍ (ጂማ)

---

ሰላም ላንዳፍታዎች፣
ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። ጅምራችሁ ደስ የሚያሰኝ ነውና። በርቱ። አንዷን ብቻ ነው ያገኘኋት። ብዙ ሰው ይህችን ሸጋዬ መጽሔት እንዲያውቀው በሚወጣበት ጊዜ በቴሌቪዥን አስታውቁን። አድነን እናገኛታለን። በቸር ይግጠመን።

ነቢል ሙቅቢል (ደሴ )

---

ላንዳፍታ አረፍ ብል ይዤ "ላንዳፍታዬን፤"
ብዙ አገኘሁባት የማይረሳውን።
ላንዳፍታ ዕውቀት፣ ላንዳፍታ መዝናኛ፣
ላንዳፍታ ለዕረፍት ሁሉንም ናት ለኛ።
ላንዳፍታ ተይዛ ብዙ ምታሳውቅ፣
ላንዳፍታ ባገርቤት ባለምም ትታወቅ።
ላንዳፍታን አንብቤ እኔ እንደረካሁ፤
ባንዳፍታ ቆይታ ብዙ እንደገበየሁ፣
እናንተም ሁላችሁ ላንዳፍታን አንብቡ፣
ሁሉ አለበትና ቀልድና ጥበቡ።

ምስክር ተገኔ
(ዶዶላ ከተማ/ባሌ)

**ከአዘጋጁ፣** በጣም እናመሰግናለን አቶ ምስክር። ለመሆኑ ዶዶላ እንደ ድሮ ቅቤ ርካሽ ነው። ብርዱስ እንዴት እያረጋችሁ ይሆን?

---

ለላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጅ፣ ሰላምታዬ ከሮቸስተር ኒው ዮርክ ይድረሳችሁ። የመጽሔቷን 1ኛ ዓመት ቁጥር 4 እትም ገጽ 24 ላይ "ዕድሜ ለቀሚሱ" የተሰኘውን ግጥም ተመልክቼዋለሁ። አቶ ዘውዱ እሼቴ እውነት የሳቸው ጽሑፍ ነውን? ቢገርማችሁ ጽሑፉን የደረስኩት እኔ ፀጋዬ አደፍርስ ነኝ። የጽሑፉም ባለቤት እኔ ነኝ። ቀደም ሲል ይህን ጽሑፍ በኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን መሥሪያ ቤታ እሠራ በነበረበት ጊዜ በመ.ቤቱ ሕዝብ ግኑኝነት ክፍል በሚወጣው "ዜና አ.ው.ሥ.ኮ.ባ." በጥቅምት/ታህሣሥ 1980 ቁጥር 2 መጽሔት ገጽ 22-24 ላይ በስሜ አሳትሜዋለሁ። መጽሔቱ አሁንም በእጄ ይገኛል።

ለወንድሜ አቶ ዘውዱ እሸቱ፣ እንዲህ ዓይነቱ ቀንድ ያወጣ ሌብነት አያዋጣም። ባልሠሩበት ሥራ ባለቤት ለመሆን መሞከር ደግሞ አዋቂ አያሰኝም፣ ትንሽነት ነው። ለመሆኑ ስለ Pilagiarism ያውቃሉ። store ከመስበር የበለጠ ወንጀል መሆኑን ይህ ያሉበት የሰለጠነው ዓለም አላስማሮትም መሰለኝ። እስቲ እኔም መረጃዬን ይዤ የምለውን ብያለሁ። እርሶም የሚሉትን ልስማ። የላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጆችና ተሳትፎአቸውን የሚለግሱትን ግለሰቦች አደንቃለሁ። እሰየው የአገር ልጆች ግፉበትም እላለሁ።

ፀጋዬ አደፍርስ (ሮቼስተር/ኒውዮርክ)

**ከአዘጋጁ፣** አቶ ፀጋዬ እኛም ነገሩን ስንሰማ ገርሞናል። የመጽሔቷን ቅጅ ቢልኩልን ኖሮ መረጃውን ይዘን የራሳችንን ሙሉ እቋም እንወስድ ነበር። አሁንም ቢሆን ይላኩልን። የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ባለሥልጣንም የበኩሉን እንዲጽፍ እንጋብዛለን። አቶ ዘውዱም መልሳቸውን እንዲሰጡ እንጠይቃለን። በኛ በኩል የዚህ ዓይነቱን መቆጣጠሪያ ዘዴው ነው የጠፋን። ቀደም ብሎም ይህ ችግር ገጥሞናል። እስቲ ዘዴውን አማክሩን። በነገራችን ላይ አቶ ፀጋዬ እንዳሉት ሁሉ የሰውን ጽሑፍ የራስ አድርጐ ማቅረብ ትልቅ ወንጀል ነው፣ ያስቀጣልም።

---

ለላንዳፍታ አዘጋጆች፣ ሰላምና ጤና እየተመኘሁ እንኳን ለፋሲካው በዓል አደረሳችሁ እላለሁ። የመጽሔታችሁ ፍቅር የተጠናወተኝ አንዷ ደምበኛችሁ ነኝ። በዚሁ አጋጣሚ ታዲያ በርቱ ሳልላችሁ አላልፍም።

ራሔል ብርሃኔ (አዲስ አበባ)

**ከአዘጋጁ፣-** የላከሽልን ካርድ ደርሶናል። በጣም እናመሰግናለን።

---

ለላንዳፍታ አዘጋጅ፤ ሰላምታዬ ይድረስህ። የሚገርምህ ነገር በመጽሔትህ አማካይነት 17 ዓመት የተለየሁዋትን የቅርብ ጓደኛዬን እንዳገኘሁ ላብስርህ። የድርጅቴ ማስታወቂያ ሁሌ በመጽሔትህ ስለሚወጣ ይህንኑ አግኝታ ደብዳቤ ጻፈችልኝና ተገናኘን እልሃለሁ። ችካጐን ለቀህ በመሄድህ ቅር ቢለኝም ባለህበት እንድትበረታ ምኞቴን እገልጽልሃለሁ።

አጸደ ይመር – ኢትዮ ቪሌጅ ቺካጐ

ከአዘጋጁ፤– ኢትዮ ቪሌጅ ሬስቶራንት ለላንዳፍታ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረገች በመሆኗ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። በናንተ አበረታችነት እበረታለሁ።

---

ይድረስ ለተናፋቂዋ ላንዳፍታ፤

ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። ባለፈው እትም የላክሁትን ደብዳቤ በማውጣታችሁ ላንባብያን ያገር ልጆች ምን ያህል አክብሮትና ፍቅር እንዳላችሁ ይገልጻል። አመሰግናለሁ። አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ውድ አዘጋጅ፤– በቅርቡ እዚህ አገር ቤት ውስጥ እንደአሸን ከፈሉት መጽሔቶች መካከል "ማህሌት" የተባለው አንድ ያልተረጋገጠ ጽሑፍ አቅርቧል። ይህም "ዳሎል ባንድ በዘር ተሰነጣጠቀ . . ." በሚል ነው። እነዚህ ልጆች እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ዕንቁ ጌጣችንና በባዕድ አገር እንደተበተኑ ፈርጦች የምናያቸው ነበሩ። በዚህ ከተማ ውስጥ የተለያዩ ወሬዎች ስለሚናፈሱ እባክህ አዘጋጅ "ላንዳፍታ" ለዚህ ጉዳይ ቅርብ ስለሆነች እውነቱን ወሬ ብታቀርብልን ደስታችን ወሰን የለውም። "ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው" ይባል የለ።

ተፈራ ወርቁ (አ.አ. ልደታ)

ከአዘጋጁ፤– አቶ ተፈራ ባደረጉት ጥቆማ መሠረት መጽሔቷን ተከታትለን አገኘናት። ደግነቱ "ላንዳፍታና" የዳሎል አባላት ያለነው አንድ ከተማ ነው። የዚህ መጽሔትም አዘጋጅ የአባላቱ የሁለቱ የሥጋ ታላቅ ወንድም፣ የሌሎቹም በጣም ቅርብ በመሆኔና ሁሉንም ስለማውቀው ጽሑፉን ሳነበው አዘንኩ። አባላቱን በሙሉ ላንዳፍታ ለስብሰባ ጠራችና የተጻፈውን በተለይ አንዳንድ ሰዎች "በዘር እንደተሰነጣጠቁ" አድርገው ማውራታቸውን ሲያዩ በጣም አዘኑ። ማልቀስ ነው የቀራቸው። እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ከባንዱ ጽንሰት ጀምሮ አብሬአቸው የነበርኩትም ግለሰብ ነገሩ አሳዘነኝ። ስለዚህም በዚህኛው እትም ጠቅላላ ታሪካቸውን ለምን ሁለት እንደሆኑ ታሪኩን ከነሱ ባገኘሁትና እኔም በጣም በቅርብ በማውቀው ዘግቤ አቅርቤአለሁ። አቶ ተፈራ፤ ስላደረጉት ጥቆማና በባንዱ አባላት ላይ ስላሎት ግምት እርሶን እንዳመሰግንላቸው ጠይቀውኛልና ይቀበሉኝ። እኔም አመሰግኖታለሁ።

---

ለውድ ላንዳፍታ አዘጋጆች፤ ሰላምና ጤና ክብርና ምስጋና ለእናንተ ይሁን። መጽሔታችሁ ተወዳጅ ናት ብል አልተሳሳትኩም። ምክንያቱም ብዙ ቁም ነገር ያዘሉ ጽሑፎች ስላነበብኩ ነው። ጥሩ ነው በርቱ። አቶ ግርማ ዘገየ ተነበው የማይጠገቡ ጽሑፎች ይጽፋል። በተለይ "ዘሬን አትጠይቁኝ" ና ስለ ጀግናዋ አትሌት ሻለቃ ደራርቱ ቱሉ የጻፈው በጣም አስደስቶኛል። ብዙ ሳላነባቸው ያለፍኩት ያቆጨኛል፤ ወደፊት መጽሔቷ እዚሁ በመምጣቷ ደስ ብሎኛል ደምበኛ እሆናለሁ።እናንተም ለአገር ልጆች ማሰባችሁ በጣም ደስ ያላል። በደጉም በክፉውም ጊዜ ማስታወሱና መረዳዳቱ አስፈላጊ ነው። አንድ ቀን ማን ያውቃል የተበታተኑ ውድ ልጆቿን ሁሉ ሰብስባ በእቅፏ የምትይዝበት ቀን ይኖራል። እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን የሱ ሥራ ረቂቅ ነው።

አንድ ልጠይቃችሁ የምፈልገው ነገር እኔ የተለያዩ የባልትና ውጤቶችን ለምሳሌ በርበሬ፣ ሽሮ ሚጥሚጣ፤ የእጃ የገንፎ ዱቄት፤ ቅመማ ቅመም ወዘተ እያዘጋጀሁ ሱቅ ውስጥም ሆነ ወደ ውጪ ለሚሄዱ ሰዎችም እሸጣለሁ። እዚያ እናንተ ጋ መግዛት የሚፈልጉ ካሉ በናንተ በኩል ጠይቁልኝ እባካችሁ። ስለትብብራችሁ በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

አስቴር አበበ (ዩዲፒኦ –አ.አ.)

ከአዘጋጁ፤– እንደአገሩ ደምብ የማስታወቂያ ባስከፈልኖት፤ ግና እንረዳዳ ብለዋ ልባችንን ቀደም ብለው ነክተውታልና ይኸው መልዕክቶን አስተላልፈናል። የተባለውን ለመግዛት የአስቴር አድራሻ

Aster Abebe
P.O.Box 3040
Addis Ababa ነው።

## ከዝግጅት ክፍሉ፤–

የተላኩልንን ደብዳቤዎች በሙሉ ለማውጣት ቦታ ያንሰናል። በሚቀጥሉት እትሞች በተከታታይ እናወጣለን። ስለመጽሔቷ አድናቆታችሁን የገለጻችሁትን ሁሉ ከልብ እናመሰግናለን።

### የዕድገቷ ዋና መሠረት አንባብያን ናችሁና መጽሔቷን በማስተዋወቅ እርዱን።

# « ዳሎል የተከፋፈለው በዘር ልዩነት አይደለም!»

## ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነው "ማህሌት" የተሰኘው በኢትዮጵያ የሚታተመው ወራዊ መጽሔት በመጋቢት 1985 ዓ.ም. እትሙ ላይ "ኑሮአችን" በሚለው አምዱ ስለ ዳሎል ባንድ ያቀረበው ጽሑፍ ነው። በደብዳቤዎች አምድ ላይ እንደሰፈረው ሁሉ የዳሎልን ባንድ ለሁለት መከፈል በተመለከተ አንባብያን የጠየቁትን መሠረት በማድረግ በአጠቃላይ ስለ ዳሎልና ብሎም ለሁለት ተከፍለው ስለመሠረቱዋቸው የ"ባሮና" የ"ጊዜ" ባንዶች ዝርዝር ታሪክ አቅርበንላችሁዋል።

የዳሎል ባንድ በመጀመሪያ የተመሠረተው እንደ አገራችን አቆጣጠር በ1964 ዓ.ም. አዲስ አበባ ናይጄሪያ ኤምባሲ አካባቢ ነው። ጠንሳሾቹ መላከ ረታ፣ ንጉሴ አስፋው፣ ሙሉጌታ ገሠሠና ዘለቀ ገሠሠ ናቸው። የሙሉጌታና የዘለቀ ታላቅ ወንድም ቤት የተጀመረው ሙሉጌታ ሊድ፣ ዘለቀ ቤዝና መላከና ንጉሴ ኦርጋን፣ የንጉሤ ታናሽ ወንድም ድራም በመያዝ ነበር። ሩፋኤል ወልደማርያም ከአንድ ሶስት ወር በኋላ አባል ይሆንና ድራም እሱ ይይዛል፤ የንጉሤ ወንድም ይወጣል። ባንዱንም ለማሳደግ እንዲረዳ ወንድማቸው ከነበረበት ቤት ይወጣና ሌላ ቤት አፍንጮ በር አካባቢ አቶ ቦጋለ ከሚባሉ ሰው ይከራያል። ዳሎል የሚለውን ስም ያወጣላቸው በወቅቱ የልዑል መኮንን ት.ቤት የጂኦግራፊ መምህር የነበረው ይኸው የነዘለቀ ታላቅ ወንድም ነው።

ስለመሣሪያ አጫዋወት ልምዳቸው ሲያወጉን ሙሉጌታ በወቅቱ ይማር ከነበረበት ጄኔራል ዊንጌት ት.ቤት የሙዚቃ ክለብ፤ መላከ ጉሬ በነበረበት ጊዜ በሚሽን፤ ዘለቀ፣ ንጉሤና ሩፋኤል አዲስ አበባ በነበራቸው ስሜት የተነሳ በራሳቸው ጥረት እንደሆነ ተርከውልናል። ቀጥሎም ድምጻውያንን ጋበዙ። የመጀመሪያዎቹ የዳሎል ድምጻውያን ግርማ አስራት አሁን ያለው ዲ ሲ)፣ ጌታነህ ደስታ፣ ማሜ ዝና በኋላም ዑመር በሃጅ ነበሩ። እዚሁ ሰፈር ቀጨኔ አካባቢ The Jungle Boys በሚል ሌላ ባንድ በእነ ታምራት፤ ራስ መኮንን ድልድይን አለፍ ብሎ ምንጩ አካባቢ The Fifth Sensation በሚል ሌላ ባንድ ደግሞ በነቢቢሻ ተቋቁመው ነበረና ውድድሩ ተጧጧፈ። በነኚህ የሙዚቃ ቡድኖች ይጫወቱ የነበሩ አባላት ሁሉ ዛሬ በታወቁ የተለያዩ ባንዶች



የዳሎል ባንድ በጃሜይካ (198[illegible])
ከግራ ወደቀኝ ሙሉጌታ - መላከ - ንጉሤ - ሩፋኤል - እሥራት - (የተቀመጠው) ዘለቀ

በዝነኛ ተጫዋቾችነት የሚታወቁ ናቸው። የዳሎል ባንድ አባላትን ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር ለረዥም ጊዜ ሳይለያዩ (ከአስራ አምስት ዓመት በላይ) አብረው መቆየታቸው ነው። አልፎ አልፎ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ለጥቂት ጊዜም ቢለያዩ ተመልሰው አብረው ናቸው። በችግርም በስደትም ለረዥም ጊዜ አንድ ላይ ነበሩ።

ወደ ታሪኩ እንመልሳችሁና ባንዱ በመጀመሪያ ለልምምድ ይጠቀምባቸወው የነበሩት ከጊታርም ኤሌክትሪክ ያልነበረ ቦክስ፣ ከኦርጋንም በእግር የሚረገጥ የነፋስ ኦርጋን እንደነበረ በትዝታ ያስታውሱታል። በተለይ ዘለቀ በመጀመሪያ የተለማመደበትን ቦክስ ጊታር $15 ብር ወንድሙን በመለመን ገዝቶ በአራት እስትሪንግ ብቻ ሲለማመድ እንደነበረ ሲያስታውስ በትዝታ ባህር ውስጥ ሰፍኖ ይቀራል። የልምምድ ወቅት ያበቃና ለትርዒት ዝግጅት ሲጀምሩ የሙዚቃ መሣሪያ በርካሽ ያከራያቸው የነበረውን ተሾምን በማመስገን ያስታውሱታል። የዳሎል የመጀመሪያው ትርዒት የቀረበው ለገሃር በሚገኘው ሸመን ደፈር ክለብ ነበር። ከዚያም በየሁለተኛ ደረጃ ት.ቤቶች የምረቃ በዓላት ላይ በመገኘት ብዙ ትርዒቶችን አሳዩ። በምኒልክ ትምህርት ቤት በመገኘት ወደ ድርቅ ቀበሌዎች ለርዳታ የሚሄዱ የአዲስ አበባ እስካውቶች ነጻ ትርዒት አሳዩ። በሴንት ጆሴፍና በልዑል መኮንን ት.ቤት ያደረጉዋቸውን የመድረክ ትርዒቶች በአንክሮ ያስታውሷቸዋል። ከዚያም በወቅቱ በነበረው የቲቪ የወጣቶች ፕሮግራመም ቀረቡ። ይህ ሁሉ ሲሆን አባላቱ ተማሪዎች እንደነበሩ መታወቅ አለበት።

ዳሎል በዚህ ዓይነት ለሁለት ዓመት እንደቆየ የ1966 ዓ.ም. ለውጥ ይመጣና አባላቱ ከየነበሩበት ት.ቤት የዕድገት በህብረት ዘመቻ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይገደዳሉ። ወደ ዘመቻም ሲሄዱ የባንዱ ሥራ ቀዝቀዝ ይልና ጥቂት እንደቆዩ ከያሉበት ኮብልለው አዲስ አበባ ይገናኛሉ። አያሌው መስፍንን ያገኙታል። ከዚያም ከአያሌው መስፍን የጥቁር አንበሳ ባንድ በሚል ስያሜ ይዞአቸው 13 ክፍለሀገራትን ተዘዋውረው ትርዒት ሠሩ። በጉዞው ወቅት የደረሰባቸውን ሁሉ አያሌው በ"ማህሌት" መጽሔት ላይ በትክክል አስቀምጦታል። ከአያሌወው ጋር የነበረው ጉዞ አብቅቶ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ ተበታተኑና ዘለቀና ሩፋኤል ከምኒልክ ወሰናቸው ጋር እቴጌ (አሁን አውራሪስ) ሆቴል፣ ሙሉጌታ ከአሊ ቢራ ጋራ ነፋስ ስልክ ዛምቤዚክ ክለብ፣ መላከ ከታምራት ሞላ ጋራ አራት ኪሎ ኢንተርናሽናል (አሁን ቱሪስት) ሆቴል መሥራት ጀመሩ። ወቅቱ በተለይ ለወጣቶች አስፈሪ ጊዜ ስለነበር እነመላከም የዚሁ ገፈት ሰለባ ሆኑ። በወጣቶች ላይ ይደርስ የነበረውም ጭፍጨፋ እያየለ ይመጣል።

አባላቱን አስጊ ሁኔታዎች እየተፈጠረባቸው መጣ። መላከ አራት ኪሎ በግርማ ከበደ ብዙ ማስፈራሪያ ደረሰበት፤ እንዲያውም አንዴ መድረክ ላይ እየተጫወቱ እንዳሉ ግርማና ግብረአበሮቹ መጥተው እንደደበደቡአቸው ለመደበቅ አልሞከረም። ሙሉጌታ ዛምቤዚክ ክለብ ድረስ ካድሬ ነን ባዮች እየመጡ እንዳስጠነቀቁት እንዲያውም አንዱ አንድ ቀን "ሞትህ በዓይንህ ላይ ሲሄድ አይታይህም?" እንዳለው ነግሮናል። ዘለቀ የሚኖርበት ከፍተኛ ሁለት ቀበሌ 12 ፒያሳ አብዮት ጠባቂዎች ጠብ ጭረውበት ሲታገል የቀበሌው ጠበንጃ ስለተሰበረ የጠበንጃውን ዋጋ እንዲከፍል ተደርጐ በዓይነ ቁራኛ ክትትል ይደረግበት ጀመረ። ይህን ለማንሳት የበቃነው ከአገር ኮብልለው ለመውጣት ውሳኔ ላይ ለመድረስ ያስገደዳቸውን ሁኔታ ለመግለጽ ነው። በመጀመሪያ ትልቅ ዛቻ የበዛበት የወቅቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበረው ሙሉጌታ፣ ባህሩ ሰለሞን ከሚባል ጓደኛው ጋር ሆኖ በአሰብ መንገድ በእግር ወደ ጅቡቲ ይኮበልላል። ስለጉዞአቸው ሲያወሩ የደረሰባቸው ሁሉ ይገርማል። ወደፊት በመጽሐፍ መልክ ለማዘጋጀት ሙሉጌታ እቅድ እንዳለው አልደበቀም። ከዚያም ዘለቀ፤ መላከና ግርማ አስራት 48 ሰዓት ተጉዘው ይከተሏቸዋል። ጂቡቲ ገብተው እንደተገናኙ የአፋር የባህል ሙዚቀኞች ያገኙዋቸውና እነሱን በማጀብ ሥራ ይጀምራሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ አሜሪካን አገር ከሚገኘው ቀደም ብሎ ከሄደው ከሙሉጌታና ከዘለቀ ሌላው ወንድማቸው ከአዲስ ገሠሠ ጋር በቴሌግራም ይገናኛሉ። አዲስም ጀምሮ የነበረውን ትምህርቱን አቋርጦ ለረዥም ሰዓት ታክሲ በመሥራት ገንዘብ አጠራቅሞ ሙሉጌታንና ዘለቀን ወደ ቺካጐ ያስመጣቸዋል። እነ ሙሉጌታም እንደደረሱ ተረባርበው በመሥራት ገንዘብ ይልኩና መላከን ያስመጡታል። ግርማ አሥራት ወደ ካሊፎርኒያ ይሄዳል። ሁሉም እንደተሰባሰቡ የትምህርት ቤት ወረቀት ያስወጡና አዲስ አበባ የቀረውን ሌላውን አባላቸውን ሩፋኤልን ያስመጡታል። ቺካጐ ቀደም ብሎ በመምጣት ይኖር የነበረውን አሥራት አዕምሮ ሣላሴን በፐርከሽንስትነት ያስገቡትና ዳሎል እንደገና ሥራውን ይጀምራል። በኋላም ከኢትዮጵያ ንጉሤ አስፋውን ያስመጣሉ። ንጉሴ በወቅቱ አምባሳደር ቲያትር አጠገብ ከነበረወው የአቡበከር አሼኪ ክለብ በኦርጋኒስትነት ይጫወት ነበር።ባንዱ ተሟላ ሥራውን ጀመረ። አዲስም ያቋረጠውን ትምህርቱን ይገባና ይጨርሳል። እነሱም ከሙዚቃ ሥራቸው ጐን ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ። የተቋቋመውም ባንድ በአሜሪካን የመጀመሪያው የኢትዮጵያኖች ባንድ ይሆናል። ኢትዮጵያውያኖች በብዛት በሚገኙ ከተማዎች በመዘዋወር ትርዒቶችም ያሳያሉ።

በዚሁ ጉዞአቸው ወቅት ታዋቂው እስቲቪ ወንደር አለበት ከተማ ይደርሱና እስቱዲዮው ጋብዞአቸው እንዲጫወቱ ያደርጋል። "መሂዴ ነው ደራ" የተባለውን ዘፈን ሲጫወቱ (የመሐሙድ ዘፈን) ይወድላቸውና ደግመው እንዲዘፍኑ ይጠይቃቸዋል። በነገራችን ላይ "Master Blaster" ተብሎ የሚታወቀውን የእስቲቪ ወንደርን ዘፈን ልብ ብሎ የሰማ ከ"መሂዴ ነው ደራ" ጋር ትንሽም ባይባል ተመሳሳይነት እንዳለው ያስተውላል።

የሚዘፍኗቸውን ዘፈኖች በቴፕ ያዘጋጁና በየቦታው ለሙዚቃ ኩባንያዎች ይበትናሉ። አዲስ ሁኔታውን በማቀነባበር በተለይም ታዋቂ የሆኑ የሙዚቃ ኩባንያዎች ከሩ እንዲደርሳቸው ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ቅጂው ከደረሳቸው አንዱ የቦብ ማርሊ ባለቤት ሪታ ማርሊ በሰማቻቸው ዘፈኖች ትደሰትና የአይሮፕላን ቲኬት ልካ ጠቅላላ ግሩፑን ወደ ጃሜይካ ትወስዳቸዋለች። ግሩፑ ተዋወቀ። ወደ ጃማይካ ኪንግስተን በሙሄድም ቦብ ማርሊ ከሞተ በኋላ ለመጀመሪያው የልደት በዓሉ ምክንያት በመቃብሩ አካባቢ በተደረገው ታላቅ ፌስቲቫል ላይ የመጀመሪያውን ታላቅ ትርዒት ያቀርባሉ።

Tuf Gong የተባለው የታወቀው የቦብ ማርሊ የሬከርድ ኩባንያ ዓይኑን ጣለባቸው። ወዲያው "Reggae Boogie" ና "I do love you" የተሰኙ ሬከርዶች ያወጣሉ። በኋላም የታወቀውን "Children of Africa" የተሰኘውን ሬከርድ ሠሩ። ታዋቂነት እየመጣ ሄደ።

ከዚያም ወደ ቺካጐ አሜሪካን ይመለሳሉ። በትርፍ ጊዜ እየተማሩ የሙዚቃ ሥራቸውን በየክለቦቹ መጫወት ይጀምራሉ። ከነዚህ ክለቦች አንዱ በአሁኑ ጊዜ የራሳቸው የሆነህ የዋይልድ ሄር ክለብ ነው። በየዩኒቨርሲቲዎችም እየተጋበዙ ትልልቅ ትርዒቶች ማቅረብ ጀመሩ። የመጀመሪያው የዩኒቨርሲቲ ጨዋታቸው ቺካጐ የሚገኘው የ North Eastern University እንደነበረ ባንክሮ ያወሱታል።

ደረጀ መኮንን ዳሎል የገባው በ1984 እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር ነው። የደረጀ የኪ ቦርድ የጨዋታ ስልት ቀደም ሲል ከነበራቸው ልምድ ጋር ተዋህዶ በ1985 እ.ኤ.አ. የመጀመሪያውን ታዋቂውን "Land of the Genesis" የተሰኘው አልበም ይወጣል። ይህ አልበም በካሴት ኢትዮጵያ ውስጥ በሳህለጊይርጊስ ብርሃኔ (ሶል ኩኩ ሙዚቃ ቤት) አማካይነት ተከፋፍሏል። "ሰላም! ሰላም!" የተሰኘው ዘፈን የወጣበት ክር ነበር። በሳህለጊዮርጊስ ድንገተኛ ሞት አባላቱ ከፍተኛ ሃዘን እንደተሰማቸው በወቅቱ ለወላጆቹ ገልጸዋል። በስደት የወጡ ኢትዮጵያውያኖችን ዘፈን (እንዲያውም የመጀመሪያውን አልበማቸውን) በኢትዮጵያ፤ በሚወዱት አገራቸው እንዲከፋፈል ሳህሌ ላደረገው ጥረት ከፍተኛ ምስጋናና ትውስታ አላቸው። በLand of the Genessis አልበም የመጣው ታዋቂነት ዚጊ ማርሊን ከፉኛ ይማርካል። የቦብ በኩር ልጅ ዚጊ ከእህቶቹና ከወንድሙ ጋር ሆኖ Ziggy Marley and the Melody Makers በሚል ቅጽል የዳሎልን ባንድ እንዳለ ይወስዳል።



ከእስቲቪ ወንደር ጋር ወንደርላንድ እስቱዲዎ ሎስ አንደለስ (1982 እ.ኤ.አ.)

ዳሎሎችም ለጥቂት ዓመታት ዳሎልነታቸው ይቀርና ከዚጊ ጋር ሁለት ዚጊ የታወቀባቸውን አልበሞች ይሠራሉ። የዚጊም ታላላቅ ትርዒቶች በዓለም በሙሉ ዞረው ሲታዩ ትርዒቶቹ የሚጀምሩት አዲስ በሚያደርገው የ"አባታችን ሆይ" የአማርኛ ጸሎት ሆነው ዘፈኖቹ ኢትዮጵያዊኛ ጣዕም ነበራቸው። ዚጊን በጣም ታዋቂ አደረጉት። በዚሁ አስተዋጽያአቸው በመጀመሪያ የጐልድ ሬከርድ በኋላም የፕላቲነም ሬከርድ ተሸላሚ ሆኑ። ዛሬ በዳሎል አባላት ቤት ስኬድ ከየግድግዳቸው ተሰቅሎ የሚታየው ይህ የጐልድ ሬከርድ ለእነሱ ብቻ ሳይሆን ለወገን ሁሉ ኩራት ኩራት የሚያሰኝ ነው። ከሁለት ዓመት በላይ ከዚጊ ጋር ይጫወታሉ። በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፤ በካናዳና በደቡብ አሜሪካ እንዲሁም በእስያ እየተዘዋወሩ ታላላቅ ትርዒቶችን (concerts) አሳዩ። በኋላም የራሳቸው ባንድ ዳሎል ናፈቃቸውና ተመልሰው የራሳቸውን ባንድ መሥርት ጀመሩ። አንድም ቀደም ሲል ገዝተው የነበሩትን ክለባቸውን በቅርብ በመገኘት ለማሳደግና ለመከታተል እንዲያመቻቸው የራሳቸውን ባንድ ሥራ መቀጠሉ ትልቅ አስተዋጽዓ አደረገ። እስቲ ስለክለቡ ትንሽ እናጫውታችሁ። ዳሎል ከ1981 እ.ኤ.አ.መጫወት የጀመሩበትን የዋይልድ ሄር ክለብን ለመግዛት ፈቃዱ ይሰጣቸዋል።

በወቅቱ ክለቡን በባለቤትነት ይዞ የነበረው አሜሪካዊ በዕጽ (drug) ጋር በተገናኘ ነገር በመንግሥት ተይዞ ክለቡን መንግሥት ይወርሰዋል። መንግሥትም ከdrug ነፃ የሆነ አካል ክለቡን እንዲገዛ ወስኖ ብዙ ተፎካካሪዎች ሲቀርቡ የዳሎል አባላትም ያመለክታሉ። በክለቡ የሚጫወቱ ሌሎች ባንዶችም አመልክተው ነበር። በተደረገው ክትትል የዳሎል አባላት ፍጹም የሚያኮሩ ወገኖቻችን ከተባለው ዕጽ ነፃ መሆናቸው ይጣራና ይፈቀድላቸዋል። ክለቡንም ይገዙታል። የክለቡ ማኔጀር እንዲሆን አሸናፊ በላይን ይሾሙታል። (አሼ ነው የሚባለው።) ክለቡም ከድራግ ነጻ በሆነ መንገድ ያድጋል። የደምበኞችም ቁጥር ከሁሉ ዓይነት እያደገ ይመጣል።በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ወጪ ወጥቶበት ክለቡ ተስፋፍቶ በመካከለኛው ምዕራብ አሜራካ ተወዳዳሪ የማይገኝለት የሬጌ ክለብ ተብሏል። ንግዱና፣ ንግዱ የሚካሄድበት ቤቱ አንድ ላይ ከ1.5 ሚሊዮን በላይ ይገመታል። ይህ የጥቁሮች በተለይም ከአፍሪካ የመጡ ስደተኞች ዕድገት የሚያበግናቸው በአካባቢው የሚኖሩ አንዳንድ ዘረኞች በየጊዜው ክለቡን ለማዘጋት ያላደረጉት ጥረት የለም። በየጊዜው በዘረኞች የሚደረገው ሙከራ ከሽፏል። ወደፊትም ቢነሳ ከየአቅጣጫው ባላቸው ድጋፍ ዕርዳታ እንደሚከሽፍ ይረዳሉ።




በተለያዩ ታዋቂ ጋዜጦች ላይ በየጊዜው ከወጡት አስተያየቶች በጥቂቱ

በቅርቡ እንኳ በቺካጐ ከተማ በሰፊው ይወራ የነበረው ክለቡን ባልተደረጉ ነገሮች (የድምጽ መብዛት - Noise Pollution) በማሳበብ ለማዘጋት አንዳንድ የአካባቢው ዘረኞች ጥረት ቢያደርጉም ከሽፎባቸዋል። የአንድ አናሳ ክፍል በተለይም የጥቁሮች ንግድ ጥሩ ውጤት እያመጣ ሲሄድ ዓይናቸው ደም የሚለብስ ዘረኞች በየጊዜው የመነሳቱ ጉዳይ በአሜሪካ የተለመደ ቢሆንም "ክለቡ ሊወሰድባቸው ነው፤" ከሚለው ሰፊ ወሬ አምልጦ መዳኑ ለብዙ ኢትዮጲያውያን እንደድል ነው የታየው።

ከዚጊ ማርሊ ጋ ከተመለሱ በኋላ የሙዚቃ ልምምድ ይጀምራሉ። በጋራ ለረዥም ጊዜ አብሮ ከመሥራት፣ እንዲሁም በሙዚቃ ከመብሰል የተነሳ በሚጫወቱአቸው የሙዚቃ ዓይነቶች ላይ ክርክሮች ይነሳሉ። አዲስ ለ"ማህሌት" መጽሔት እንደገለጸው የሙዚቃ ፈጠራና ጨዋታ ስሜት ልዩነት ተፈጠረ። አንደኛው ወገን አሁን "የጊዜ ባንድ" የሆነው በንጹህ ሬጌ ላይ እናተኩር የሚል ሲሆን ሌላኛው አሁን "የባሮ ባንድ" የሆነው ሬጌን በአገራችን ሙዚቃ ስልት እንጫወት አለ። ይኸው ልዩነት ተቻችሎ አንድ አቋም መድረስ ስላልተቻለ ቡድኑ በስምምነት ለሁለት ተከፍሎ መሥራት ጀመረ። አንዳንድ የወሬ አሽቃባቾች እንደሚያናፍሱት የጊዜው በሽታ የዘር ፖለቲካ መሐላቸው ገብቶ አይደለም።

የአባላቱን ዕድገት በክፉ የሚያዩ አካላት ለየሚፈልጉት የፖለቲካ ሥራ አመቺ ሆነው ስላላገኙአቸው የሚያስወሩባቸው ወሬ ነው። ዛሬ በሙዚቃ ዓይነት ልዩነት ሁለት ባንድ ቢሆኑም አንድ የሚያደርጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉም በወንድማማችነት ደረጃ የሚታይ በጣም የቀረበ ግኑኝነት አላቸው። መሐላቸው እየገቡ አንደኛውን ለሌላው፣ ሌላኛውን ለሌላው በማማት ሊያጣሉአቸው ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። ሌላው የሚያስሳስራቸው ደግሞ የጋራ ንብረታቸው የሆነው ክለቡ ነው። ከሁሉ በላይ እምነታቸው ነው። ሁለቱም የሚዘፍኑት ስለ ሰው ልጅ ሰላም፤ ስለ ሕዝቦች አንድነት ነው። "አንድ አፍሪካ፣ አንድ ሕዝብ" እያሉ በመድረክ የሚዘፍኑትን ሁለቱን ቡድኖች በዘር ልዩነት መከፋፈል ማማት በጣም የሚያሳዝን መሆኑን ከሁለቱ ወገኖች ለመስማት ችለናል። አባላቱን በጣም ቀርቦ የሚያውቃቸው ይህ እንዴት ሊወራ እንደበቃው ሳይገርመው አልቀረም። ሁለቱም ወገኖች ስላገራቸው አውተው አይጠግቡም። ኢትዮጵያን በየዘፈኖቻቸው ያነሷታል፤ ይወድሷታል። ሰንደቅ ዓላማዋን ይለብሷታል፤ በመድረክም ልዩ አርማቸው ናት። የሚዘፍኑት ስለሕዝቦች ፍቅርና አንድነት ነው። የ"ማህሌት" ጋዜጠኛ በመጨረሻ እንድስቀመጠው ባሮንና ጊዜን አስተሳስሮ የያዛቸው ጥቅም አይደለም። አብሮ ማደግ ነው። ለሕዝቦች አንድነትና ሰላም ያላቸው ቆራጥ አቋም ነው።



"ስለዓለም ሰላም፤ ስለሕዝቦች ፍቅር፤ ስለአፍሪካና የጥቁር ሕዝቦች ሰላም፣ ብልጽግናና አንድነት እየዘፈን መታማታችን ያሳዝናል። ለዓለም ሕዝቦች ሰላም፣ ፍቅርና አንድነት ያለን ዓላማ ምን ጊዜም ጽኑ ነው፤ የተፈጠርናባትን እናት አገራችንን ማወደስን ደግሞ ቅድሚያ እንሰጣለን። "

ዘለቀ ገሠሠ (ባሮ)



"ፖለቲካ ለፖለቲከኞች እንደሆነ ሁሉ፣ ሙዚቃ ደግሞ ለሙዚቀኞች መተው አለበት። የኛ ሥራ ሰውን ማፋቀርና ማገናኘት ነው እንጂ ሌላ ምሥጢር የለውም። ሙዚቃ የተፈጠረው ጭንቀትን ለማስወገድ መሆኑን እንርሳ።"

ሩፋኤል ወ/ማርያም (ጊዜ)

# « የአሜሪካኑ ሕልም ቅዠት ሲሆን! »
# ትክክለኛ ፍርድ ለሚገኝት ትብብር ይጠይቃል!!

ትምህርቷን በመቀጠል ተምራ ለአገሯ ለወገኗ ለዘመዶቿና ለራሷም አጋዥና ኩራት ለመሆን በማሰብ በ1991 ዓ.ም. እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ወደ አሜሪካ ትመጣለች። ቀደም ብሎ ወደዚሁ የመጣው ወንድሟ ኃይሌ ደምሰው ለረዥም ጊዜ ተለይታው የቆየችውን እህቱን እሱም ሥራ ይዞ ከፍተኛ ትምህርቱን ከሚከታተልበት ኦርላንዶ ፍሎሪዳ ሆኖ በደስታ ይቀበላታል። ኃይሌ እህቱን ለትምህርት የነበራትን ጉጉት በመረዳት ከሁለት ዓመት ውጣ ውረድ በኋላ በአሜሪካዊው ጓደኛው ቲመቲ ኢንግሊሽ ሃላፊነት ነበር ያስመጣት። አልማዝ ደምሰው ወደ አሜሪካ አገር እንደመጡት ወጣት ኢትዮጵያኖች ሁሉ እንደደረሰች ወዲያውኑ በወንድሟና በቲመቲ ረዳትነት ትምህርቷን ትቀጥላለች። በወጪ በኩልም ወንድሟን ለመርዳት እንዲያስችላት ኦርላንዶ ከተማ በሚገኘው ክላሪየን ፕላዛ ሆቴል ተቀጥራ መሥራት ትጀምራለች። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል እየሠራች ትምህርቷን ቀጠለች። የነበራት ታላቅ ዓላማ ከሁለት ዓመት ጥረት በኋላ ከግቡ ሳይደርስ ይቀራል።

ቀኑ ፌብርዋሪ 22 ቀን 1993 ነበር። እንደሁሉም ጊዜ አልማዝ ከቤቷ ወጥታ ትምህርት ቤት ሄዳ ከዚያም ወደ ሥራዋ ትሄዳለች። የዛን ዕለት ግን ወደቤቷ አልተመለሰችም። ሌሊት ላይ ሆቴሉ ክፍል ቁጥር 261 ውስጥ ተገድላ አስከሬኗ ይገኛል። አልማዝ በ23 ዓመቷ ተቀጠፈች። የኦርላንዶ ፍሎሪዳ ፖሊስ ክፍል "ባደረግሁት ክትትል አልማዝ ራሷን ነው የገደለችው፤" በማለት ፋይሉን ይዘጋል። "ኸረ ባካችሁ ነገሩ በደምብ ክትትል ይደረግበት፣ አልማዝ ራሷን የምትገድልበት ምክንያት በፍጹም የለም፤" በማለት ወንድሟ፣ ጓደኞቿና ለትምህርቷ ሃላፊ ሆነው ያስመጣት ቲመቲ ኢንግሊሽ አቤት ቢሉ ሰሚ ያጣሉ። በእነ ኃይሌ የተቀጠረ የግል መርማሪ (private investigator) ጥብቅ ክትትል በማድረግ አልማዝ በሰው እጅ እንደተገደለችና ፖሊስም በቂ ክትትል እንዳላደረገ ጠንካራ መረጃዎች ያገኛል። ከሁሉ የሚገርመው ቀን ትምህርት ቤት ሄዳ ስትማር የቆየች ልጅ ማታ ራሷን ለመግደል የሚያስችል ሁኔታ ተፈጠረ ብሎ በማሳመን ፖሊስ ፋይሉን ማዘጋቱ ነው። ከተለያዩ ክፍሎች ማለትም ከፖሊስ ክፍል ፤ ከአደጋ ጥሪ ቁጥር 911 ክፍል፤ ከእሳት አደጋ መከላከያ ክፍል፤ ሆቴሉ ውስጥ ከሚሠሩ ሌሎች ሰዎች፤ በዕለቱ ከቦታው ደረስኩ ከሚለው የፖሊስ ጓድ፣ የተቀነባበሩት ሪፖርቶች በጣም የተምታቱና ከፍተኛ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱ ሁኔታዎች እንዳሉበት የግል መርማሪው እንደደረሰበት ወንድሟ ገልጾልናል።



አልማዝ ደምሰው ደስተኛ ወጣት ነበረች።

በተጨማሪ የትምህርት ቤት ጓደኞቿ March 29, 1992 ለፍሎሪዳ ገዥ "አልማዝ ሞተች በተባለችበት ጠዋት ትምህርት ቤት እንደነበረችና እንደሁሉም ጊዜ ትስቅና ትጫወት እንደነበረ፤ እንዲሁም በጣም ቀርበው በሚያውቋት ባህሪዋ እንኳን ራሷን ለመግደል የምትቃጣ (suicidal) ልትሆን ይቅርና ብስጭት እንኳ አይተውባት እንደማያውቁ በመግለጽ ሁኔታው በከፍተኛ ደረጃ ታይቶ እንዲጣራ፤" በማለት አቤቱታ ያቀረቡበትን ማመልከቻ ቅጅ የዝግጅት ክፍላችን ለመመልከት ችሏል። ለዝግጅት ክፍላችን ከደረሱት ሪፖርቶች መካከል የፖሊሱ ክፍል suicide ነው በማለት የወሰነበትን ባለብዙ ገጽ መረጃ ዋንኛው ነው። ከመረጃው ለመረዳት እንደሞከርነው፤ ምርመራው የተከናወነው በአጭር ጊዜ መሆኑና፣ በተለይም በዕለቱ በሥራ ላይ የነበሩት የሆቴሉ ሠራተኞች በሰጡት ቃል በዕለቱ አልማዝ ምንም ብስጭት እንዳላዩባትና ሁል ጊዜም ተጫዋችና ሳቂታ እንደሆነችና ፖሊሶች ይህንን ምስክርነት በውሳኔአቸው ላይ የተጫወተው ሚና ያለ አይመስልም።

. . . (ወደ ገጽ 19 ይዞራል)

# ልብወለድ

## « ትላንት ማታ በሕልሜ »

(ልብ ወለድ)
ከደምሌ እያሌው

አይኖቼን እያሻሸሁና እያዛጋሁ ሮጬ ከእንቅልፌ የቀሠቀሠኝን ስልክ አነሳሁ። "እስካሁን አልተነሳህም እንዴ? ለመሆኑ ስንት ሰዓት እንደሆነ ታዉቃለህ? እንቅልፋም!" አለች እንደመሳቅም እንደማፌዝም እያሰኛት። ትላንት እንዴት እንደተለያየን ሳስታዉስ እንኳን ስልክ መደወል ይቅርና ድንገት ብንገናኝ የምታናግረኝ አልመሰለኝም ነበር። ሆኖም የስልክ አደዋወሏ ለጤና አይመስልም። የፎዚያ የስልክ ጨዋታ እስታይልም አይደለም። የስልክ ጨዋታዋ ሳቅና ቀልድ የተሞላበት ነዉ። ዛሬ ግን በማፌዝ ጀመረች፤ በሆዷ ነገር የያዘች ትመስለኛለች።

"አይ አልነቃሁም" አልኩ። ከእንቅልፌ የቀሠቀሠኝ ሰዉ ሌላ ቢሆን ኖሮ ስልኩን ጆሮግንዱ ላይ ዘግቸበት ለመሄድ የወጠንኩት ፕላኔ አለመሣካቱን እያሠብኩ።

"አንተ ልጅ ምን ቢያደርጉህ ይሻላል? የምነግርህን አትሠማም" አለች አነጋገሯ እየፈጠነ። መቆጣቷና መናደዷ ያስታዉቃል። ፎዚያ በህይወቷ ቁጣና ኩርፊያ በጭራሽ አታዉቅም። ሳቅና ፈገግታ ልዩ ተሰጦዎ ናቸዉ። የሆነችዉን አላዉቅም፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የፎዚያ ፀባይ እንደ ነፍሠጡር ከዕለት ወደ ዕለት መለዋወጥ ጀምሯል።

"ምን አጠፋሁ ፎዚ?" አልኩ። ስሟን ሙለ ለሙሉ እንዳልጠራ ከዚህ በፊት ተነግሮኛል።

"የምነግርህን ሁሉ አታከብርም። ጥፋትህን ደግሞ ታዉቃለህ ለማመን ግን አትፈልግም፤" አለች መጮህና ለቅሶ በተቀላቀለበት አንደበት። ጥያቄዬን አልመልስ አለች። የመመለሥም ፍላጎት የላትም። ነገር ግን በደፈናዉ የተወነጀልኩበት ጥፋቴ ባወጣ ባወርድ አልከሠትልህ አለኝ። ሁኔታዋ ስላናደደኝም ሁለተኛ ላለመጠየቅ ወሠንኩ። እንደሚፈቀሩ በየዕለቱ ካልተነገራቸዉ የተናቁ የተጠሉና የፍቅር ኮንትራታቸዉ ያከተመ የሚመስላቸዉ፣ እንደሚፈቀሩ ደግሞ ቃል አዉጥቶ ቢነገራቸዉ የማሾፍና የዉሸት ፍቅር የሚመስላቸዉ ብዙ ሀበሾች እንዳሉ ግልፅ ነዉ። ይሄንኑ በመፍራት ነበር ለፎዚያ በአንዳንድ አጋጣሚዎችና በልደቷ ቀን ስጦታ ከመስጠት በቀር እንደቀጣፊና እንደፍቅር ደብተራ መዉደዴን በቃሌ የማልገልፅላት። ታዲያ ሰሞኑን እንደዚህ የሚያነጫንጫት ለዚህ ይሆን ብየ አሰብኩ። የፈረንጆች ባህል ተጋብቶባት ይሆን? ታዲያ እንደማፍቅራት አፍ አዉጥቼ ባለመናገሬ ለብዙ ጊዜ ሲቆጩኝ ኖሯል። ስለዚህ ዛሬ ጥሩ አጋጣሚ ያገኘሁ መሠለኝ።

"ፎዚዬ እንደማፈቅርሽ ለመሆኑ ትጠራጠሪአለሽ እንዴ?" አልኩ ራሴን እያከኩ።

"አታዉቀኝም እንደሡ አትበል!" አለችና የነብር አራስ ሆነች። ለምን አታዉቀኝም እንዳለች ገባኝ። ለፎዚያ ፍቅር ማለት ቁጥር ነዉ። በቁጥር ታምናለች። ስትሄድ ስትቀመጥ መቁጠር ነዉ። ከበደና ገነት 3 ዓመት፤ አልማዝና መንገሻ 8 ዓመት፤ ወይንሸትና ንጉሡ 4 አመት ማለት የሁልጊዜ ወሬዋ ነዉ። እንደማሽለና ጤፍ ሸማች ፍቅርን በጣሳ መቁጠር ትወዳለች። በቁጥር ተወልዳ በቁጥር ያደገች መሣይ ፍጡር። ሁለት ጓደኞች 3 ወይንም 4 አመት አብረዉ ካልወጡ እንደዚህ አይነቱ ፍቅር እሱቴ የሚሉት ዘይቤ አላት። የኔና የሷ ስድሰት ወር መዉጣት አልጣማትምና አታዉቀኝም ለማለት በቃች። ቀጠል አድርጋም። "ራስህን አትጉዳ ርሳኝ" አለች የኔ ሸጋ በሠላም ከኔ መሠናበቷ ነበር። አዝማሚያዎቹ ሁሉ ምክንያት ፈልጋ ከኔ ለመለየት እንደምትጥር ሁኔታዋ ይገልፃሉ። ስለዚህ ከዚህ ማጥ ዉሳጥ የምወጣበትን ዘዴ መፈለግ ጀመርኩ።

"መቼ ልደዉልልሽ? ፎዚ" አልኩ። ተስፋ በቆረጠ በተዳከመ ነገር ግን በማር በተለወሰ አንደበት። ዝም አለች።

"መቼ ልደዉልልሽ? ፎዚ ነው እኮ የምልሽ፤ አልሰማሽኝም መሰለኝ?"ኩ። ተስፋ በቆረጠ በተዳከመ አንደበት ደገሜ።

"አትደዉል፤ እኔ እደዉልልሃለሁ" አለች ሕይወትና ለዛ በሌለበት እስትንፋስ።

ቴሌፎኑን ጆሮየ ላይ እንዳስደገፍኩ እንደበቴ ተዘግቶ አይኖቼ እንደፈጠጡ ቀሩ።

"በል ደህና እደሪ በለኝና ስልኩን ዝጋዉ፤" አለች። አሁንም በዚያ ህይወትና እስትንፋስ በሌለዉ በደረቀዉ አንደበቷ። ትዕዛዟን አከበርኩ፤ ተሰናበትኳት። ጆሮዬን ከተደገፈዉ ስልክ ግን ምንም ዓይነት መልስ አልነበረም። ስልክ አስቀድማ ስትዘጋ ፎዚ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነዉ። ፎዚ በጣም ሴንሲቲቭ ልጅ ነበረች። እንደተዋወቅን ሠሞን ከሁለት ሠዓት በላይ በቴሌፎን አዉርተን የተሠናበተችኝ መሥሎኝ ሥልኩን አስቀድሜ በመዝጋቴ ከሁለት ደቂቃ በኋላ እንደገና ደዉላ "እኔ አልተሠናበትኩህም እኮ፤" ያለችበት ወቅት ነበር።

አሁን ግን ፎዚያ ያ የአፍላዉ ፍቅር አልቆላት ፣ ሴንሲቲቭነቷን አጥታ ልቧ ሊገባበት የማይችል ጥቁር አለት ሆናለች። ገረመኝ።

ቴሌፎኑን ወረወርኩና አንገቴን ደፍቼ እጆቼን ፒጃማየ ኪስ ከትቼ በጠባቧ ቤቴ ተንጎራደድኩና የእሷን ሁኔታ አሰላሰልኩ። በመጨረሻም ወደ መኝታ ክፍሌ ሄጄ አልጋየ ላይ ተጋደምኩ። ለመተኛት ሞከርኩ ሦስት አራት ጊዜ ተገላበጥኩ ፣ ተሸፋፈንኩ ፣ ተገለጥኩ እግሮቼን አጠፍኩ ፣ ዘረጋሁ ሆኖም አይኖቼ ፈጠዉ ቀሩ።

ረገምኩት ቀኑን። "ምነዉ ባልተዋወኳት ኖሮ" አልኩና ከተሸፋፈንኩበት ተገልጬ አይኖቼ ጣራዉ ላይ የሚታየዉን ፊልም ማየት ጀመሩ።

ግንቦት 22 1992 ማክሰኞ፤

ገፆቹን በፍጥነት አገላብጣ ትጨርሥና መፅሐፍ መደርደሪያዉ ላይ ታሥቀምጣለች። በመጨረሻም ሁለቱን መጽሐፍቶች በግራ እጇ በደረቷ አሥደግፋ ሌላዉን ደግሞ በቀኝ እጇ አንጠልጥላ ሦስት የመፅሐፎች መደርደሪያ አቋርጣ ሄዳ ተቀመጠች። አይኖቼ አብረዋት ተጓዙ። "ነች፤" አልኩ በልቤ እሷን ተከትለዋት የተጓዙት ዓይኖቼ ሣይመለሱ። ምናልባት ላትሆን ትችላለች ብዬ በመጠራጠር ማንበቤን ቀጠልኩ። የጥያቄዬ እልባት አለማግኘት ግን ሀሊናዬን ዕረፍት አሳጥቶታል።

የማንበብ ችሎታየ ዛሬ እንዴት እንደተሻሻለ አላዉቅም። ስንቱን ገፅ ግልጥ አድርጌዋለሁ። የአንባቢዉን ተመስጦ የጫማ ኮቴ ረበሸዉ። እኔም ማንበቤን ትቼ ቀና አልኩ። እንደ ሀረግ ሬሣ የተመዘዘችዉ የቀይ ዳማዋ ወጣት የወሠደቻቸዉን መጽሀፍቶች እየተጀራገደች መጥታ መደርደሪያዉ ዉስጥ አሥቀምጣ እየተጀራገደች ወደ መቀመጫዋ ተመለሰች። በአይኖቼ እንደሽንኩርት ላጥ አደረኳት።

አበሻ ናት አልኩ በልቤ። እርግጠኛ በመሆን የሀበሻ መልክ ከብዙ ሠዉ መካከል መንጥሮ የመለየት ችሎታዬ በጓደኞቼ ዘንድ ታዋቂ አድርጎኛል። የሀበሻ መልክ ከብዙ ሺ ሠዉ ጋር ቢቀላቀል አይጠፋም። ሀበሻ ደሙ ፣ ወዙ ፣ አካሄዱና አስተያየቱ ያስታዉቃል የሚል ፈሊጥ አለኝ።

ታዲያ ጆርጋዳዋ ሀበሻ እንደሆነች አዉቄአለሁ። ቢሆንም ደፍሮ ለማናገር ልቤ ወኔ አንስታል። ሀበሻ የማወቅ ችሎታየ ተዳክሞ ተጠራጠሪ ከሆንኩ ዉሎ አድሯል። ከዚህ በፊት አንዷን ህንድ አበሻ መስላኝ ካናገርኳትና አለመሆኗን ከገለጸችልኝ ወዲህ እምብዛም ጠጉረ ለዉጥ ሠዉ ለመጠየቅ አልደፍርም።

ያን ዕለት ግን የዚህችን ልጅ ሁኔታ ሳላረጋግጥ ከዚያ ቤተ መጽሀፍት ቤት ዉስጥ ብወጣ የምፈነዳ መሠለኝ። ከተቀመጥኩበት ድንገት አለፍ አልኩና ጃኬቴን አስተካከልኩ። በሃሳቤ መስታወት ስላኔ ያላት ግምት ምን ዓይነት እንዳማሆን ለማወቅ በመጣር የልቤ ትርታ የጨመረ ቢሆንም ጉዞዬን ወደ ጆርጋዳዋ ቀጠልኩ የጫማዬ ኮቴ ረበሻት መሰል መጽሓፍ ማንበቧን አቋርጣ ቀና ብላ አየችኝ። ምን ብዬ እንደማናግራት አጥንቻላሁ ተለማምጃለሁ። አይኖቼ ቀለሟ ሀበሻ መሆኗን ቢያጋልጡም ተጠራጣሪነቴ አሸንፎኝ በእንግሊዝኛ እንዳናግራት ወስኜ ነዉ ወደሷ የተጓዝኩት።

"አይ ሀቭ ሲን ዩ ኤ ፊዉ ሚኒትስ ኤጐ፤ አይ አምናት ኩዋይት ሹር አርዩ . ." ብየ ሣልጨርስ "ኢትዮጵያን" ብላ ጥያቄየን በፈገግታ ደመደመችዉ።

ከዚያ በኋላ ላለዉ ንግግር አልተዘጋጀሁም ነበርና ከደስታ ብዛት ብዙ ዘባረቅሁ። ግን አልታዘበችኝም። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነዉ ከፎዚያ ጋር የተዋወቅነዉ። ታዲያ ከዛሬዉ የቴሌፎን ንግግራችን በኋላ የረገምኩት ይህችን የኔና የሷ ታሪክ የተጠነሰሰበትን ቀን ነበር። ፎዚን ሳዉቃት ቅን ሠዉ እንደነበረች ነዉ።

ፎዚ ቀጥተኛ ፍላጎቷን ብስጭት ቢኖራትም በቀጥታ መግለፅ የምትችል ልጅ ነች። ትንሿን ስህተት አይቶ ማለፉ ይቅርና ዉሀ ቀጠነ ብላ ብስጭቷን በአንደበቷ ከመግለፅ የማትመለስ የደም ገምቦ ነች። ሆኖም ዉበቷ ጨዋታዋና ፈገግተዋ እዉነተኛ ባህሪዋን ለብዙ ጊዜ ሸፍኖት ኖረ።

ትላንት ከሀመልማል አባተ ፓርቲ አምሽተን ስንመለስ ፎዚ የጥንቷ ፎዚያ አልነበረችም። ያቺን የ1978 ሼቪ ካፕሪስ በግድ እሥነስቼ ለአምስት ደቂቃ አሙቄ ወደ ቤቴ ጉዞየን ስቀጥል

"የት ነዉ የምትሄደዉ?" አለች አይኖቿ ከጉርንዳቸዉ ሆነዉ እየተንጉባለሉ፤

" ወደ ቤት ነዋ" አልኩ በጥያቄዉ በመደነቅ አይኖቼ እሷን እያስተዋሉ፤

እንኳን ከፓርቲ መልስ ይቅርና ሌላም ጊዜ ቢሆን ወደ ቤቴ እንደምትመጣና እኔም እንድምወስዳት ግልፅ ነበር። ጥያቄዋ ከማስደነቅ አልፎ አናዶኛል።

"እቤቴ አድርሰኝ አልሄድም።" አለች በቁጣ፤ የኔን ቁጣ ለማሸነፍ በመጣር እንዢያ አይኖቿ ጉድጓዳቸዉ ለቀዉ ለመሄድ የተዘጋጁ ይመስላሉ። ሰዉ በቁጣ የሚያልቅ ቢሆን ያኔ በሟሸሽኩ ነበር።ያቺ ክብ ፊቷን እንደመፅሐፍ አነበብኳት በንግግሯ ግራ እንደተጋባሁ።

"አሁን ምን ትሠሪያለሽ ፎዚ እኔ ጋ አድረሽ ጠዋት አደርስሻለሁ፤" አልኩ ከፊት ለፊቴ ያለዉ አረንጓዴዉ የትራፊክ መብራት ወደ ቀይ እንዳይለወጥ በመስጋት የቤንዚን መስጫዉን ፔዳል እስከመጨረሻዉ ረግጬ። አልተሣካም በድንገት ፍሬን ያዝኩ። ቀበቶዉን ባታጠልቅ ኖሮ ተላትማ ነበር። በክፉኛ አይን አስተዋለችኝ። እኔም አየኋት። አነዳዴ አላማራትም። ሆኖም አስተያየት ለመስጠት አልፈለገችም። ቀዩ መብራት እንድንወያይ ዕድል ሰጠን።

"አልሄድም! አልሄድምሁ" አለች። የፊቷ ቀለምም ተለዋወጠ ጉንጮቿ ቀሉ። ፎዚያ በየዕለቱ በየሁኔታዉ የምታኮርፍና የምትቆጣ ሠዉ አይደለችም። ተሳክቶላት ስትቆጣና ስታኮርፍ ግን ያቺ እንደ ጨረቃ ክብ የሆነችዉ ፊቷ ለእሸት መጥበሻ እንደተዘጋጀ የወይራ ፍም ትርክክ ትላለች። ያኔ ያቺ የቀላችዉን ጉንጯን ልስማት እሠብኩ። ሆኖም ነገር ላለማበላሸት በማሠብ ወሲባዊ ስሜቴን ገታሁ። እጄን ከመሪዉ ላይ አነሣሁ። ወደ ቀኝ በመዞር የቀኝ እጄን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጌ ፎዚን ማባበል ጀመርኩ። እንዲያዉ ልጨርሰዉ ብየ ነዉ እንጂ በተፈጥሮየ ሴትን በአፍ ካራቴ መጣል አይሆንልኝም።

ፎዚ እንደ ህፃን ልጅ አባበሉኝ ለምኑኝ አቴንሽን ሰጡኝ የምትል ፍጡር ነች። አንዳንድ ጊዜ ስንጣላ ስንኮራረፍ አቅፌ ሳሻሻት ስስማትና ሳባብላት ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጋ ትረሣዋለች።

ፎዚ ቂም የማትይዝ የዋህና ንፁህ ልጅ ነች። እስከዛሬ ከተዋወኳቸዉ የሴት ጓደኞቼ ልዩ የሚያደርጓት ፀባይ ቢኖር ይህ ይቅር ባይነቷ ነዉ። ትላንት ግን ባደርጋት ብሠራት ፍንክች አልል አለች።

እሷን በማባበል ላይ እንዳለሁ የብዙ መኪናዎች ጥሩንባ ዉይይታችንን እቋርጥዉ። መብራቱ ለካ ወደ አረንጓዴ ተለዉጦ ኖሯል። እንደማይተዋወቅ ግለሠብ እኔ ሾፌር እሷ ተሣፋሪ ሆና ሣንነጋገር አልፎ አልፎ በጎሪጥ እየተያየን እሷ ቤት ደረስን። ስትሰናበተኝ እንኳን ለከንፈርና ለጉንጭም ያልታደልኩ ነበርኩ። የአፓርትመንቷን ቤት ከፍታ እስከምትገባ ድረስ አየኋት። ዞር ብሎ እጅ ማዉለብለብ ዘብት ነዉ። ዓይኗን አይቼ የማልጠግባት እንደቅንቡጥ ልጅ የምሣሣላት ሽጋ ወረቁ አልቆላት እንደቀልድ የመኪናዩን በር ከፍታ ሹልክ ብላ ቀረች።

ታዲያ እንደዚህ ብላ የተለየች ልጅ ዛሬ ትደዉላለች ብየም አላሰብኩ ነበር። ብትደዉልም ለጤና እንዳልሆነ ማሠብ ነበረብኝ። ግን ሳላስበዉ መርዶ ነግራኝ ሄደች።

ከተለየችኝም በኋላ እየተንጎራደድኩ "ያገርሽ አድባር ይከተልሽ" አልኩ።

በቃልኪዳኗም መሠረት ትደዉልልኛለች በማለት ስልክ ተጠባበኩ። ሆኖም ሳትደዉል ቀኑ ወደ ሣምንት ሳምንቱ ወደ ወር ወሩ ወደ መንፈቅ ተለወጠ። የኔ ፍቅር የኔ አለኝታ የዉሃ ሽታ ሆና ቀረች። ከፎዚ ጋር በጊዜና በቦታ አልተዋሃንም ነበርና ከረሳኋት ጊዜዉ ዉሎ አድሯል።

የበጋዉ ፀሐይ ቀኑን ሙሉ ሲቀቅለዉ የዋለዉ አፓርትመንት ሙቀቱ እቤት ዉስጥ አያስቀምጥም። የኤሌክትሪክ ቢል ካላማረራቸዉ ጥቂት ሠዎች በሥተቀር ከባልኮኒዉ ላይ ሆኖ የማታዉን ነፋሻ አየር የማይመገብ ሠዉ የለም። የአፓርትመንቱ ኗሪዎች በሙሉ በአዋጅ የታዘዙ ይመሥል ባልኮኒ ላይ ዉጥትዉ ተድርድርዋል። እኔም እቤቴ እንደገባሁ ልብሴን ከቀየርኩ በኋላ ሰዉን ለመምሰል የተፈተለኩት ወደ ባልኮኒዩ ነዉ።

የአስቴር አወቀን ሲዲ አስገብቼ እሠማለሁ። ለአስቴር ዘፈንና ድምፅ እስከዚህም አይደለሁም። የዘፈን ግጥሞቹን ግን በጣም የጠለቁና ሚስጥራዊ ስለሆኑ አዳምጣታለሁ፣ አደንቃታለሁ። አንዳንድ ጊዜ ከሷ ሌላ ደግሞ እንደኩል የጠራዉን የበጋ ሰማይ እያየሁ የትዝታ ማዕበል ያነሳኝና አዉርዶ ያፈርጠኛል።

"ስንዴ ዳቦ ጋገርኩ በጨረቃ ፍም" ብላ አሥቴር ግጥሟን ሳትጨርስ ድንገት በሬ ተንኳኳ። በር ቶሎ ሄዶ መክፈት እወዳለሁ። ዛሬ ግን በር መክፈት ይቅርና ወደ በሩ የተንዝኩት ሁለት ጊዜ ተንኳኩቶ ሶስተኛዉ ሲጀምር ነዉ።

"ኖ በዲ ሆም"? አለ የማውቀዉ የሴት ድምፅ ነገር ግን ለብዙ ጊዜ ያልሰማሁት። ነፍሴ እስከትበር ድረስ ሮጬ በሩን ከፈትኩ። ቆማለች። ሰዓሊዉ በኪነጥበቡ በህሊናዉ በብሩሹ ካንቫስ ላይ ህይወት የዘራባት ማስተር ፒስ መስላ። ሙቀት እንደነካዉ ቅቤ ቀለጥኩ።

ፈገግታ አሣየችኝ። እኔም አፀፋዋን መለሥኩላት። የኔ ፈገግታ ግን ድንጋጤ የተቀላቀለበት ነበር። ለብዙ ጊዜ ያላዩት ያልሠሙት ግለሠብ ሳያስቡት ሲታይ የሽንጥ ዉሃ ያፈሣል።

ቀሚሷ በጥልፍና በመልጎም አሸብርቋል። ባለህብረ ቀለሙ መቀነቷ ወገቧን እቅፍ ድግፍ አድርጓታል። በወፍረሙ የተጎነጎነዉ ፀጉሯ እንደፈረስ ጭራ በትከሻዋ ላይ ወርዶ ተነሥንሷል። በጥቁር ወፍራም የሀር ማተብ አማካይነት የተንጠለጠለዉ ድንብሏ እንደጉጥ ቀሚሷን ቀሥረዉ በያዙት ሁለት ሎሚዎች መካከል በሚገኘዉ የተንጣለለ ሜዳ ላይ አርፏል። ከፊት ለፊቴ ያለዉን ዉበት በዚያን ወቅት ማየቴን ማመን አቃተኝ።

"ቤት ለንቦሳ!" አልኩ የፍርሀት የድንጋጤና የደስታ ድምፅ በተቀላቀለበት አንደበት። ሶሪት የሚመስሉት እግሮቿ አልቦ አጥልቀዋል። ረድኤት ባለዉ አረማመድ ወደኔ ቀረበች። የተቆጠቡ ፈገግታዋን በደንብ ባልተገለጡት ከንፈሮቿን መሀል በሚገኙት ጥርሶቿ ብልጭታ አበሠረችና ጉንጮቿን ሠጠችኝ። ጊዜዉም ቢረዝምም ከተለያየን የጥንቱ መዓዛቸዉ አልተለወጠም። ትንፋሿ እንደሣት ይጋረፋል። እጆቹ ወገቧን ዳሠሡና ሂደዉ ዳሌዋ ላይ አረፉ፤ ወደላይ ቀና ብላ አይኔን ያለማቋረጥ አየችኝ። የኔም ዓይኖች በዓይኖቿ ዉስጥ ቀልጠዉ ቀሩ።

"የኔ ሸጋ ይሄን ያህል ጊዜ ከእኔ ከተሠወርሺ በኋላ ዛሬ ምን እግር ጣለሽ?" አልኩ ለሁለት ደቂቃ የሠፈነዉን ፀጥታ በማደፍረስ።

"ከፎዚያ ጋር እንደተጣላችሁ ስለሠማሁ ልታረቅህ ፈልጌ ነዉ፤" አለች ሮማን ፎዚያን ለመበቀል ጊዜዉና ሁኔታዉ አመች መሆኑን እያሰላሰለች።

====================================

## ለአንባብያን፤

በመዘከራችሁ ያስቀመጣችሁት አጫጭር ልብወለድ ታሪኮች በተለይ በእውነተኛ የአሜሪካ ኑሮ ገጠመኝ ላይ ያተኮረ ካላችሁ ላኩልን። በቅርቡ ውድድር ስለምናዘጋጅ ለዚሁም ተሰናዱ እንላለን።

====================================

# የዘመድ ደብዳቤ

ከማቱሳላ ነጋሽ
አዲስ አበባ

እንዴት ነህ ባያሌው
እንዴት ነህ ወንድሜ?
አሁንስ ናፈቅሽኝ
መምጣት ጀመርከ በልሜ።
ታትዬ እናትህ ሂደኮ ብትለኝ፣
አድራሻ ወስጄ ልጥፍ ተነሳሁኝ።
አብዬም እማማም ሁላችን ቤተሰብ፣
ፈጣሪ ይመስገን ደህና ነን አታስብ።
ታናሽ እህትህም ትምህርቷን ይዛለች፣
ወንድምህም አራት
እርሷ አምስት ደርሳለች።
ከፍ ያለውም ቢሆን ተከታይ ወንድምህ፣
'አትሪከ' ወስጃለሁ ብሎኛል እንግዲህ!
እኔም ከዋልድባ እዚህ ከመጣሁኝ፣
የዛሬው ጊዮርጊስ ድፍን ወሬን ሞላኝ።

በዋልድባ ያሉ ድፍን ዘመዶችህ፣
አደራ ብለዋል
"እንዴት ነህ?" እንድልህ።
ለመሆኑስ አንተ ባዕድ አገር ሆነህ፣
ኑሮውን ለመድከው ጓደኛስ አገኘህ?

አይዞህ የእኔ ሎጋ ባይተዋር አትሁን፤
ፈልገህ ጠጋ በል አንዱን አበሻውን።
አሜሪካን አገር በዛ ጮሌነትሽ፣
እተማመናለሁ ችግር እንዳይገጥምሽ።
ታዲያ የነጭ ጥበብ ተምረሽ ስትመጪ፣
መቼም አትቻይም ታየኝ ስትፈነጪ።
ድሮም በኔ አጉትሽ ማላገጥ ለምደሻል፣
አሁንስ ብልጥ ነኝ የድሮው መስሎሻል!

ታዲያ ነጩ ሁሉ ደህና እንዳይመስልህ፣
አሣቻ አግኝቶ እንዳያዘናጋህ!
አንድዬ ነቃ በል ጠንቀቅ ነው የሚበጅ፣
ጅል ሰው እንዳይመስልህ
ምን ቢነጣ ፈረንጅ።

ሽየ አዲስ አባ እኔ እንኳ ያየሁት፣
ብትሰማ ጉዳዩን የሚያስቅኝ ነው ትንግርት።
በማርያም ዋዜማ ከተማውን ስናይ፣
ይገርምሃል አንድሽ ያጋጠመኝ ጉዳይ።

ይኼ 'ንበርሲቲ ይኼ አራት ኪሎ ነው፣
ይኼኛው 'ጥፈት ቤት' በቀኝ የሚገኘው።
እያለ ሲያሳየኝ ታናሹ ወንድምህ፣
ሰው ሲሯሯጥ አየን ሲሉ ወዲያ ወዲህ።
ምን ይሆን ጉዳዩ ብለን ስንጠጋ፣
ባየሁት አዘንኩኝ - ሽረ ምኑን ላውጋ?

ሁለት ሰዎች መሀል በጥላቸው ደክመው፣
እንዲያ ሲተሻሹ በደማቸው ታጥበው፣
ያ ሁሉ ያገር ሰው ሮጦ የተጠጋው፣
የዶሮ ጥል ይመስል እንዳጥር ከቧቸው።
አሁን አንዱ ገብቶ "በገላጋይ" ይላል፣
ብዬ ባስተውለው ሁሉም ፈዞ ያያል።
"ሽረ እናንተ ሆዬ! ምነው ዝማላችሁ፣
ተይህ ሁሉ ጉብል
አንድ እንኳን የላችሁ?"
ብዬ ጥልቅ አልኩኝ ከሰብሰቡ መሀል።
"ባዛኝቱ ልቀቅ ሰውስ ምን ይልሃል፣
በማርያም ይዣለሁ በገላጋይ ብዬ፣
አንተም እጅህ ይረፍ ልቀቀው ሰውዬ።"
እያልኩኝ ሳላቅቅ ሁለቱን ስቆጣ፣
ፈጠንጠን እያለ አንዱ ነጭ መጣ።

ሰውን ሰነጣጥቆ እየገፈተረ፣
እመሐል ቢገባ ሁሉም ሰው በረረ።
"ካራቲስቱ መጣ ወይኔ ጉድህ ፈላ፤
ዘወር በል አንተ ሰው
እንዳይቆጭህ ኋላ።"
እሱ ልማዱ ነው ሰዎችን ማጣላት፣
አንዱ አቸንፎ እስከሚለይለት።
እያለ በፍርሃት ሽሽ ያ ሁሉ ሰው፣
ይኼም የኔ ዘመድ ከኔ ጋር የቆመው።
"ከዚህ ቦታ እንሂድ ይቅርብህ አጉቴ፣
ይኼ ሰው ክፉ ነው ይችላል ካራቴ።
ኩንጉፉና ዋሹ ጁዶ ሌላ ነገር፣
አሰልጣኝ ነውና የታወቀ ባገር።
አይሆንም እንቀጥል ሳይመጣብን ጣጣ፣
ኋላ ጉድ ይፈላል ይሄ ሰው ቢቆጣ!"
ቢለኝ ተገርሜ ተቆጥቼ ክምር፣
"ሳልደርስ አይነካኝም ካላመመው በቀር፣
ላዛኝቷ ብዬ ሰውን ብገላግል፣
ምን ቁርጥ አድርጉት እኔን ይነካኛል?"
ብዬ ቆሜ ቀረሁ፣
ይነካኝም እንደሁ።
ባየው ተገርሜ እያጣፋሁ ኩታ፣
ነጩ ሰው ተጠጋኝ በግሩ እየተማታ።
እንዴት እንዴት ይላል ይህ የነጭ ድንጉላ
በምንስ አረደው ይህን ሰው በሞላ?
በራሴ ልብ እያልኩ እስኪ ንክች ያርገኝ!
ሳላስበው ደርሶ ጉንጩን አቀመሰኝ።

ታዲያ ይኼን ጊዜ የጐንደሪቷ ልጅ፣
'ወንድሻ' አልኩና ተነሳሁ ልበጃጅ።
እንኳን ተነክቼ አርፌ እያለሁ፣
ድሮም ልማዴ ነው ትግል እወዳለሁ።
እኔም አገራለሁ ትግል ከተባለስ፣
የሾኬ አጠጣለፍ አያያዝ የደንደስ፣
ከጋይንት ተነስቶ በዋልድባ ይዞ፣
በጐንደር ከተማ ደግሞም በአዘዞ።

የሚችለኝ ካለ በድፍን በጌምድር፣
ያገር ልጅ ይጠራ ስለኔም ይመስክር።
እንኳን ይቺን መሳይ ኮሳሳ ሙጥልቅ፣
ማንም ጉበዝ ሁሉ እንደምፎጠርቅ።
እነ ደጃች ጉሹን የሆኑት ትልልቅ፣
ቢሻው ድፍን ሀገር ጉንደርን ይጠየቅ።
እንግዳ ነኝ ብዬ ላክብር ልፈርህ ብል፣
ትግልማ ካልከኝ እኔም ደስ ይለኛል።
ሁኔታዬን አይቶ ኮስተርተር አለና፣
ልብሴ ላይ "ጢቅ!" አለ በንቀት አየና።
ይህን ጊዜ ታዲያ ኩታዬን አኑሬ፣
ቁምጣዬን አጥብቄ ቆምኩኝ ተሰትሬ።
እኔም "ጢቅ!" አልኩበት
"ብታርፍ ይሻልሃል፣"
ኋላ ጠንቀቅ በል እለቅህ መስሎሃል።
የማነህ ቡሆ ፊት እኔን የምትደፍረኝ?
ዋ 'ባህ' አልኩኝና ጣቴን ወዘወዝኩኝ።
ይኼን ጊዜ ታዲያ የተጣሉት ሳይቀር፣
እኔና እሱን ከበው ይሳለቁ ጀመር።

ባላየሁት ዛቻ ነዶ እሳት ጉርሶ፣
ይጮህ ይዘል ጀመር መልሶ መላልሶ።
መበረቁን ያዘ አካሌን በመዞር፣
ቁንጫም ይመስል ይፈናጠር ጀመር።
ሄደት መጣ እያለ ሲያወናጭፍ እጁን፣
ሰይጣኑን መሰለኝ ወላዲት እምላክን።
ደግሞም በየመሀል የሚጮኸው ጩኸት፣
ጆሮ ይሰቀጥጣል እንድዩ እእኔ ልሙት።

ንክ እንደሁ እያልኩኝ ሀዘኔን ሳልጨርስ፣
እግሩን አነሳና አለኝ እንካ ቅመስ።
በሽተኛ መስሎኝ የኔ ሆድ ሲባባ፣
ከምሩ ነው ለካ ይኼ ነጯጭባ።
በል እንግዲህ ምጣ እኔን ከፈለግሽኝ፣
እያልኩ በትግል ስልት ጥቂት ተጠጋሁኝ።
ግራ እጄን ወደፊት ቀኙን ወደኋላ፣
አድርጌ ብጠጋው ለትግል በመላ።
አልጠጋም አለኝ ገባው መሰል ፍርሃት፣
እኔም ይሻህ እንደሁ ቀኙን ቀየርኩለት።
ዝቅ ከፍ አለና አነንዴ ተወርውሮ፣
እግሩን ቢወረውር አገኘኝ አክሮ።
'በመላ ካልያዝኳት ይህ መፈናጠሯን፣
ጉድ ትሠራኛለች አልቻልኩም ጥበቧን።'
ብዬ በተጠንቀቅ ስጠብቅ እራሴን፣
ድንገት ቢወረወር ለቀም አረኩ እግሩን።
ይኼን ጊዜ ታዲያ እግሩ ምን ሊረባኝ፣
እሱን ጥዬ ወገብ ለቀም አደረግሁኝ።
የትግሌ አያያዝ አልተስተካከለም?
ደስታዬን ተወው ምን ልበል የኔ ዓለም።
ጨመቅመቅ አድርጌ ሆዱን ፈተንኩና፣
ለማወራረጃ ጣልኩት ከጉዳና።
ተዚያ ስትነሳ ሾኬ አግብቼ በንዲህ፣
ታፈር ደባለቅኋት ሁለት በል እንግዲህ።

እንደገናም የግሯን መኋሂት አምቄ፣
ከፍ ዝቅ አረኳት ለሙከራ አውቄ።
ምን አላት መሰለህ ውፍረትስ የላትም፣
ያካላቷ ሙሌት እንደኔም አይሆንም።
ግን ሆራጣ ቢጤ ነች የከረረ ጅማት፣
ምንም ብትቀጥን ነገሯስ "ጠጅ ናት፤"
ወይራ ሆነችብኝ እስከምጠመዝዝ፣
በጥሩ ሁኔታ ወገቧን እስከይዝ።

ሳያት ባትፈትነኝ አልኩ እንደመዝናናት፣
የጐንደሪቷ ልጅ መቀለጃ አረግኋት።
ከፍ አደረግሁና እተከሻዬ ላይ፣
ሶስት ጊዜ ባዞራት ጠፋት ምድር ሰማይ።
ኋላማ እንደሩር አጉኜ ብጥላት፣
ያ ትልቁ ድንጋይ ወገቧን ሰበራት።

ይኼን ጊዜ ታዲያ ዘልዬ በፍጥነት፣
በምኒልክ ቡጢ አንዴ አቀመስኳት።
ደግሞም ከሆዷ ላይ ባሳርፍ ቡጢዬን፣
አመለጣት መሰል አልቻልኩም "ቁኔዋን።"
ፍርግጥ የለምኮ አልሞካከረችም፣
አንዲ ምን ልበልህ አልተመጣጠንም።

እልህ ስለያዘኝ ባሳየችኝ ንቀት፣
አፍንጫዋን ደግሞ እንቺ ቅመሺ አልኳት።

ሰው አጨበጨበ ባየው ሁሉ ትንግርት፣
ደም ቢወጣ ባፏ እኔን ገባኝ ስጋት።

ኋላ ዘመዶቹ እኒያው ሳላያቸው፤
ለተንኮል ነው መሰል መጡብኝ አድብተው።
መድያው ያ ሁሉ ሕዝብ ግልብጥ ቢልባቸው፣
በነፍሳቸው ደርሶ ቡሊስ አዳናቸው።

ወዲያው ሳይዘገዩ
ግራ ቀኝ ሳያዩ፣

በወሳንሳ አንስተው ገብተው ከመንገዱ፣
ውዳቂውን ይዘው ወደሳይ ነጐዱ።

ኋላ ባጠያይቅ የትውልድ ሀገሩን፣
አማሪካን ቢሉ ጭንቅ አላት ልቤን።
የሰው ሆድ እሩቅ ነው
እኔን ሲያጡኝ እዚያ፣
እንዳይፈታተኑህ ጠንቀቅ ነው ታዲያ!

እልሳሁ አንድሽ ያጋጋጠመኝ እኔን፣
እዚህ አዲስ አባ በዚያች አንድ ሰሞን።

ታዲያ አንዳንዱ ነጭ ልብም ስለሌለው፣
ሰብዕና ስላጣ ተግባሩ ሳያንሰው፣
የሰው ልክ አያውቅም ይንቃል እንከፍ ነው።

ይህን ጊዜ ጐንደር ሰው ቢጠይቅ ኖሮ፣
ውርደት የለም ነበር ራሱ ነገር ጭሮ።
መቼም የኔ ነገር እንደዚ ተያዝኩኝ፣
ንዝንዜም አይቆም የለም
'ሰው ምን ይለኝ።'

በል ልሰናበትህ አልጨቅጭቅ እንግዲህ፣
ለመሆኑስ ወዲህ መቼ ትመጣለህ?
ወረቀት ጣፍልኝ ልትመጣ ስትል፣
ቀኑን እንዳውቅና መጥቼ እንድቀበል።
በደንቡም ተምረህ ድግሩን ካመጣኸው፣
የማደርግልህን እኔ ነኝ የማውቀው።

በርታ ጥናት ይስጥህ፣
ጠንክር ነው እንግዲህ፣
አካላቴ . . .
በዓይኑ ሥጋ መጥተህ እስከምንገናኝ፣
መጣፉን አትርሳ በል ደህና ሁንልኝ።

አጐትህ ወንዳፍራሽ ገላግሌ።

==============================

## ማ ሳ ሰ ቢ ያ

የ"ላንዳፍታን" መጽሔት በደምበኝነት ካዘዙ በታተመ ቁጥር በቀጥታ ገበያ ላይ ከመውጣቱ በፊት በፖስታ ቤት ይላክልዎታል። በዛውም ለመጽሔቱ ዕድገት አስተዋጽዖ አድርገዋልና ሊኮሩበት ይገባል። በራስ ቋንቋ የተጻፈ ጽሑፍ ውጪ አገር እያሉ በየጊዜው ሲደርሶት ምን ያህል እንደሚያስድስቶት ይረዳሉ።

የማዘዣ ቅጹን ከገጽ 48 ላይ በማባዛት በአድራሻችን ከነክፍያው ይላኩልን። ጽሑፎችም ካልዎት ይላኩልን፤ በኛ ይሁንብዎ ከቆሻሻ መጣያ አጠገቡም አናደርሰውም።

አድራሻችን፤

LANDAFTA
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359 ነው።

+=+=+=+=+=+=+=+=+=+=+
ድርጅትዎን፤ ንግድዎን ሌላም ሌላ

በ"ላንዳፍታ" ላይ ቢያወጡ

በብዙ ኢትዮጵያውያኖች ዘንድ

ይተዋወቅሎታል።
+=+=+=+=+=+=+=+=+=+=+

በተለያዩ አቅጣጫዎች የቀረቡት አቤቱታዎች ሰሚ በማጣታቸው በዋሺንግተን የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ግፊት እንዲደረግ ኃይሌ (የአልማዝ ወንድም) አቤት ቢል ከዛሬ ከነገ በማለት ጉዳዩ ቸል እንደተባለበትና እንዲያውም ስልክ በደወለ ቁጥር የመሰላቸትና ቸል የማለት ዝንባሌ እንዳጋጠመው እንባ እየተናነቀው ነግሮናል። ከእንግዲህ የተዘጋው ፋይል ተከፍቶ ጉዳዩ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ ማድረግ የሚችለው የዩናይትድ ስቴት አተርኒ ጀነራል በመሆኑ በምንችለው አቅም ሁሉ ግፊት ለመፍጠር ለተባለው ቦታና ለF.B.I. ለሴኔተርስ፤ ለኮንግሬስማኖች በፔቲሽን ሆነ በስልክም አቤት ብንል ድጋፍ ልንሆን እንደምንችል ታውቋል። በተጨማሪም ለዚሁ ተግባር ክትትል፣ የጠበቃ የአመራማሪ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚሁ ጉዳይ በተከፈተው የባንክ ቁጥር ዕርዳታችሁን እንድታደርጉ ወገኖቸች ሁሉ ተጠይቃችኋል። ፍትህ አጣሁ በማለት አገሩን ለቆ ፍትህ ያለበት አገር መጣሁ ያለው ወገን ፍትህ ሲያጣ ጉዳዩ "ነግ በኔ" ነውና ትብብራችንን እንቆጥብ። የኃይሌ ስልክ ቁጥር (407)578 - 1830 ነው።

አልማዝ ደምሰው ታህሣሥ 23 1962 (በእኛ አቆጣጠር) ከአባቷ ከአቶ ደምሰው እንዳርጌና ከእናቷ ከወይዘሮ ያምሮት ሰንደቅ ጐንደር ክፍለ ሀገር ናበጋ ጊዮርጊስ ተወለደች። ታላቅ እህቷ ወ/ሮ አመልማል ደምሰው ጋር በመኖር በ1977 ዓ.ም. ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ጨርሳ በጐንደር ከተማ ይሰጥ የነበረውን የአንድ ዓመት የመምህራን ማሰልጠኛ ትምህርት ትመረቃለች። የመምህርነቶ ሥራዋን ጀምራ አንድ ሁለት ወር ያህል እንደሠራች በ ወንድሟ በኃይሌና በቲመቲ ዕርዳታ July 12, 1991 ወደ አሜሪካን መጣች። በነበራት መግባባት ችሎታዋ ስለአሜሪካ አገር አኗኗር ማወቅ ጊዜ አልፈጀባትም። በMid Florida Technical School የሚsጠውን የቋንቋ ትምህርት እያገባደደች ወደ Valencia Community College ለመግባት በApril 1993 የመግቢያ ፈተና ለመውሰድ በመዘጋጀት ላይ ነበረች። አልማዝ ኢትዮጵያም ት. ቤት በነበረችበት ጊዜም ይሁን እዚህ በጣም ጉበዝ ተማሪ እንደነበረች ለማወቅ ችለናል።



አልማዝና ወንድሟ ኃይሌ ደምሰው

ለምታደርጉት ዕርዳታ የሚቀጥለውን አድራሻ ተጠቀሙ።
Almazs Fund for Justice Assoc. 315 Alston Dr.Orlando, Fl 32835
በ Sun Bank, N.A. በኩል Acc. No. 0703703050246 (የባንክ ቁጥር)
የወንድሟ የኃይሌ ደምሰው ስልክ ቁጥር (407)578-1830 ነው።

# ሉልሰገድ ገብረ ሕይወት መኖሪያ ቤቱ ተገድሎ ተገኘ።

ለረዥም ጊዜ በስደተኝነት ይኖር ከነበረው ኬኒያ በቅርብ ጊዜ (6 ወር በፊት) ወደ ቺካጐ የመጣው ሉል ሰገድ ገብረ ሕይወት (ሉሌ) በሚኖርበት አፓርተማ ብዙ ቦታ በጩቤ ተወግቶ ተገድሎ መገኘቱ ታውቋል። ቺካጐ ከተማ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ክፉኛ ያሳዘነና ያስቆጣ ይህ ግድያ ምርመራው እየተካሄደ መሆኑን ለመረዳት ችለናል።

በቺካጐ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አማካይነት ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀው ስብሰባ (hearing) የቺካጐ ፖሊስና የከተማው መማክርት አባላት በመገኘት ጉዳዩን በከፍተኛ ደረጃ የሚያዩት መሆኑን በወቅቱ ለተሰበሰቡት ኢትዮጵያውያን መግለጻቸውን ለመረዳት ችለናል። የሉልሰገድም አስከሬን በቺካጐ ኢትዮጵያውያን ዕርዳታ ከፍተኛ አሸኛኘት ተደርጐለት ወደ ኢትዮጵያ ተልኳል። ዝርዝር ታሪኩንና የምርመራውን ውጤት በሚቀጥለው እትማችን እናወጣዋለን።

# የዴብራ ጦስ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብ ወለድ)
ከገሪሱ
"የዴብራ ጦስ" በተሰኘ ርዕስ የተጻፈው ልብወለድ
ረዥም ስለሆነ በተለያዩ ክፍሎች በተከታታይ ይወጣል።

## ካለፈው እትም የቀጠለ፤-

ያለፈው እትም መጨረሻ ዓረፍተ ነገር...

. . ."ደግሞ የአበሻ ሴት።" አለ በሆዱ። ይህ ምሽት ነበር ለካሣሁን በዴብራ ፍቅር መጠመድ ምክንያት የሆነው። የዛን ምሽት ዴብራ እሱ ጋር አድራ ከሄደች ጀምሮ ደስተኛ ሆነ። . . .

ካሣሁን ዴብራ በሕይወቱ አይቶ የማያውቀው ፍቅር ስለሰጠችው ተማረከላት። ደረችበት ዕለት ማግስት ቁርስ ጋብዟት የስልክ ቁጥሯንና አድራሻዋን ቢጠይቃት ልትሰጠው ፈቃደኛ አልበረችም።

"ምን አለበት?" አላት፣ ለስለስ ባለ የማስተዛዘን ልመና።

"እኔው ራሴ እደውልልሃለሁ፣ የስልክ ቁጥሬንና አድራሻዬን ለአንተ ከመስጠቴ በፊት ማረጋገጥ የምፈልገው ነገር ይኖረኛል።" አለችው በለኮሰችው ሲጋራ ጪስ ውስጥ በፈገግታ እያየችው።

"ምን ይሆን ማረጋገጥ የምትፈልጊው?" አላት።

"እየህ መጀመሪያ ምን ያህል እንደምትወደኝ ማረጋገጥ አለብኝ። እናንት ወንዶች ከየትም ብትመጡ ከየት የማይለቃችሁ ዓመል አመላችሁ።"

"ወድጀሻለሁ። sweet ነሽ።"

"Sweet መሆኔን አውቀዋለሁ። sweet መሆኔን መቀበልህን ደግሞ በአፍህ ስለነገርከኝ ሳይሆን በተግባር ላየው እሻለሁ።"

ምን ዓይነት ተግባር ይሆን? ብትፈቅደኝ ነው እንጂ እንዲህ የተጨነቀችው ዝም ብላ ባይሆን ይህን አትልም። ደግሞ አበሻ አይደለችም። እነሱ እኮ ግልጽ ናቸው። ከወደዱ ወደዱ፣ ከጠሉ ጠሉ ነው።" አለ በሆዱ።

"ለመሆኑ አንቺ ወድደሽኛል?" አላት ጥቂት ከተዋጠበት የሃሳብ ባህር መለስ ሲል።

"ምን ዓይነት የሞኝ ጥያቄ ነው የምትጠይቀው? ባልወድድህ እቤትህ ድረስ ውሰደኝ ብዬ እኔው እራሴ እለምንህ ይመስልሃል?"

"Ok! ok!" እንዳልሽው አላት።

ካሣሁን አልከፋውም። እሷ ከደወለች ምን ችገረው። እንደትላንትና ማታ ሁኔታዋ ደግሞ በየቀኑ እንደምትደውል ተነበየ። ብዙ ሊጨቀጭቃት አልፈለገም። ያን ማታ ያገኘውን ሲሳይ ማጣትም መሰለው። በዚህ ላይ ደግሞ እነሱ ጭቅጭቅ አይወዱም የሚባል ወሬ አንዱ አንድ ቀን ሹክ ብሎታል። ስለዚህ ደጋግሞ መጠየቁን አልፈለገም። ደግሞ ተግደርዳሪዎች አይደሉም እንደኛ ልጆች። ከሆነ ሆነ ከአልሆነ አልሆነም ነው ብሎ ዝም አለ። የዛን ዕለት ሲለያዩ ግጥም አድርጋ በአደባባይ ሳመችው። አጋጥሞት አያውቅም። እሱ የሚያውቀው ሰው እየኝ አላየኝ ተብሎ በድብቅ መሳም። ያውም በስንት ልምምጥ።

"ብራቮ ካስሽ . . . ነፃነትህን አውጀሃል። የአበሻ ሴት ስለማመጥ አትገኝም። እንግዲህ ዴብራ ጋር መደሰት ነው። ቆንጆ ናት፤ ከማንም የአበሻ ሴት አታንስም፣ ምን ይወጣታል? . . ." እያለ ራሱን ሲክብ ነበር የዋለው።

ዴብራ የመጀመሪያው ግንኙነት በተከናወነ በሶስተኛው ቀን ደወለችለት። ማታ እቤት እንደምትመጣ ነገረችው። ደስታውን አልቻለውም። ሁለት ቀን ስትጠፋበት ጊዜ ጨንቆት ነበር ።

እመጣለሁ ባለችበት ጊዜ ማንንም በተለይ አበሻ ማግኘት አልፈለገም። ከከተማ ለሥራ እንደሚወጣ ጓደኞቹ ጋ አወጀ።

"የኛ ሰው ምንም ጓደኛ እንኳ ቢሆን ምቀኛ ነው።" አለ በሆዱ። የልብ ጓደኛው ፈጠነም ቢሆን በዚህ ጉዳይ ልዩ ሊሆን አይችልም።

ቤቱን ጠራረገና እየተቁነጠነጠ ጠበቃት። ልክ ባለችው ሰዓት የቤቱ ሰዓት ተደወለ። "ከች አለች እሳቷ!" አለ በሆዱ።

"ልክ በሰዓቷ፣ አይ አሜሪካዊ!" አለ። በአራት ሰዓት ቀጥረው በስድስት ሰዓት የሚመጡ አበሻ ሴቶችን ለአፍታ አስታወሰ። በሕሊናውም "ደህና ሁኑ፣ ቻው!" አላቸው።

ስትገባ ተንጠልጥላ ሳመችው። ቅልስልሱ ካሣሁን እሱ ሳይደክም ሴት ራሷ መጥታ ሳመችው። ፊቱ በፈገግታ ተሞላ። "ብትወደኝ አይደል?" አለ በሆዱ። እሱም ዓይን አወጣና አጸፋውን ለመመለስ እንቅ አድርጐ ሳማትና እንዳቀፋት ቀረ።

የእቅፉ ጡንቻ አይሎባት ይመስላል፤

"Easy!" አለችውና ለቀቃት። እንዳለችው ካልሆነ የማይደረግ ነገርስ አድርጐ ቢያስበረግጋት ቀረ ማለት አይደል። እሷ ያለችህ ሁሉ ልክ ነው።

"Did you miss me?" ነበር የመጀመሪያው ጥያቄዋ።

"Of course!" አላት፤ እየሳቀ። ከልቡ ነበር የተፍነከነከው።

እጎኑ ተቀምጣ እያሻሸች ውሃ አደረገችው። መቅለስለሱን፣ እንደፈለገች ልታደርገው መቻሏን በጣም ወደዋለች። እየተሳደበ ከሚጮህባት ወንድ ለስለስ ያለ፣ ትህትና ያለው መሆኑ በተለይ ጥቁር ሆኖ፣ በጣም አስደስቷታል።

"ለምን ወጣ ብለን አንመለስም? እኔ ትንሽ መዝናናት እፈልጋለሁ፤" አለችው። አጠያየቋ እንደ ፈተናም ነበር። የአዎንታ መልስ እንደምታገኝ የተጠራጠረች አትመስልም።

"እሺ፤" አላትና ተያይዘው ወጡ። በእሱ መኪና። የመጀመሪያ ፈተናዋን አለፈ። ቀደም ሲል እንዳጋጠሟት ወንዶች ምክንያት አልደረደረም።

"መጀመሪያ አንድ ቦታ መድረስ አለብኝ፤ አንተ መኪና ውስጥ ትቆየኛለህ፤ እኔ አንዳፍታ ደርሼ መጣለሁ።" አለችው መኪና ውስጥ እንደገቡ።

"እሺ፤" አላት አሁንም።

በድጋሚ ፈተና አለፈ። የአለችውን ሁሉ እሺ ከሚል ወንድ ሌላ ምን ዓይነት ወንድ ትፈልጋለች ሴት ልጅ። በዛሬ ዘመን ደግሞ የት ሊገኝ። "እሺ ይበልህ እቴ፤ አፌ ቁርጥ ይበልልህ፤" አሉ ሴትዮዋ።

ከዚያም መንገድ እየመራችው ከአንድ ፈጽሞ ደርሶ ከማያውቅበት አካባቢ ወሰደችው። "በዚህ! በዚህ!" እያለች መንገዱን እየመራችው እሱ እሷ እንዳለችው ሲኳዝ ገደልም ይዛው ትሂድ አያውቅም ነበር። ይህን ለማሰብ አቅሙ ቢኖር አይደል። የወሲብ ጥማት ከሁሉ አየለ ማለት ነው?

አንድ አሮጌ ሕንጻ አካባቢ ደረሱ።

"በቃ እዚህ አካባቢ አቁምልኝ መጣሁ።" አለችው።

"እዚህ ቦታ?" አላት መፍራቱ እንዳይገባት እየተጠነቀቀ።

አካባቢውን አልወደደውም። በመንገድ ላይ የሚተላለፉ ሰዎች ገልመጥ ገልመጥ እያሉ ያያሉ። በሕንጻዎች መካከል ደግሞ ዕድሜአቸው ዝቅተኛ የሆኑ ልጆች እያጮለቁ አላፊ አግዳሚውን ያያሉ። ብቻ አልወደደውም።

"ምነው? ችግር አለ?" አለችው።

"ኖ! ዝም ብዬ ነው፤" ደግሞ ሴት ጋ ፈራሁ እንዴት ይባላል።

ከአስተያየቷ "እስቲ አባክ አትጠብቀኝና!" የምትል ትመስላለች። የሚጠብቅ መሆኑን እንዳረጋገጠላት፤

"እስቲ አንድ $15 ስጠኝ፤ የኔ ጉድ! ረስቼ መጣሁ።" አለችው በጥሩ ፈገግታ።

ከመቅጽበት ቦርሳውን አውጥቶ ድፍን $20 ሰጣት። ግጥም አድርጋ ሳመችው። ደስ አለው። እንደዛ የምታስደስተውን ልጅ ማስደሰት የሚያህል ምን ደስታ አለና። ሄደች። በመስታወት ሲያያት መንገድ ላይ ስትሄድ እሷም እንደአካባቢው ሰዎች ገልመጥ ገልመጥ ማለቷን ሲያይ "ምን ቦታ ይሆን?" በሚል ጥርጣሬ ውስጥ ገባ። እሷ ሄዳ ትንሽ እንደቆየ የፖሊስ መኪና ሳይረን ድምጽ እየቀረበ ሲመጣ ተሰማው። አካባቢው በየጥጉ የነበሩት ልጆቹም ትልልቆቹም ባንዴ ተሰወሩ። መኪናው በፍጥነት በአጠገቡ አለፈ። ጭንቀት ቢይዘውም የሚያደርገው ነገር ስለሌለ ዝም ብሎ መጠበቁን መረጠ። የፖሊሱ መኪና ጩኸት ርቆ እንደጠፋ በየቦታው ተደብቀው የነበሩት ሁሉ ወጣ ወጣ ማለታቸውን እንዳየ ትንሽ ነፍሱ መለስ አለ። ትንሽ እንደቆየች ዴብራ ፈጠን ፈጠን እያለች ስትመጣ በመስታወቱ አየ። ምን ፈጠን ፈጠን እንደሚያደርጋት ግራ ሳይ ገባው አልቀረም። እነደደረሰች በፍጥነት መኪና ውስጥ ገባችና ከዚያ አካባቢ በቶሎ እንዲወጣ ነገረችው። ትንሽ ቁና ቁና መተንፈሷ ሳይገርመው አልቀረም። መኪናውን አስተንስተቶ እሷ ባለችው መንገድ ሲሄድ ቦርሳዋን ከፍታ አንድ ነገር አየት አደረገችና መልሳ ዘጋቻው። ገልመጥ ገልመጥ እያለች ማየቷን ተመለከተና፤

"Any problem?" አላት።

"No! It is not something that serious. Keep on driving." አለችው።

ለካሣሁን የሚታየው ማታ አልጋ ላይ የምታስደስተውን ዴብራን ማስደሰቱ ብቻ ነው። ስለሌላ ነገር እንዳይጠራጠር ታውሯል። እንኳን የሚጠረጥረውም ነገር የለም።

ዴብራ እንደ ቄና ተነፈሰችና የሚቅበዘበዘውን ዓይኖን ወደሱ መለስ አድርጋ፤

"እንዲያውም ለምን wine ገዝተን እቤትህ አንሄድም። ሌላ መዝናኛ ቦታ መሄዱን ሌላ ቀን እናደርገዋለን።" አለችው።

እሷ እንዳለችው እንደሚሆን ማረጋገጫዋ ነበር።

"እንዳልኩት ካልሆነ የምትፈልገውን አታገኝም!" ብላ የምታስብመም መሰለው። ሃሳቧን በቀየረች ቁጥር አብሮ መቀየር አለበት።

እውነት አልመሰለውም።

"Sure! Why not?" አላት።

እሱ የቸኮለው ለሌላ። ያ የቤቱ ጨዋታ በዓይን ሕሊናው ለአፍታ ሽው አለበት። መኪናውን ወደ ቤቱ ረገጣት። የወሲብ ስሜቱ በረገጣት መኪና ፍጥነት ፈላበት። እቤት ደርሶ እሷ እንዴት አድርጋ እንደምታስደስተው ብቻ ነበር የሚታየው። እመንገድ ላይ አንድ ግሮሰሪ ጐራ አለና የምትፈልገውን ዓይነት wine ለሌላም ጊዜ በሚል ሁለት ጠርሙስ፣ የምታጨሰውን ሲጋራ አንድ እስቴካ ገዝቶ አምጥቶ ሲያስታቅፋት በወፍራሙ ከንፈሩን ሳመችው። ካስሽ ጋለ። ከአለፈው ጊዜ የበለጠ መዝናናት ዛሬ እንደሚጠብቀው ተረዳ። በአንጻሩ ዴብራ እንዲህ ያለ ወተት የሆነ፤ ረጋ ያለ humble, generous ወንድ ማግኘቷ አስደሰታት። የረዥም ጊዜ ጸሎቷ እንደሰመረላት ተረዳች። የወሲብ ጥመኛ እንደሆነም ከሁኔታው ስለተረዳች ወሲብን መሣሪያ አድርጋ የምትፈልገውን ሁሉ እንዲያደርግላት ማድረግ እንደምትችል መገንዘብ አልተሳናትም። ውሃ ጥም ላቃጠለው ሰው ይህን ብርጭቆ ውሃ ስጥሃለሁና ይህን አድርግልኝ ቢሉት ውሃዋን ለማግኘት የተባለውን ነገር ለመፈጸም ወደኋላ እንደማይል ዴብራ ቀደም ሲል በነበራት ልምድ ታውቀዋለች። በተለይ የወሲብ ስሜት ያጣደፈው ወንድ። እሷም ባስደሰታት መጠን ልታስደስተው ቆርጣ ተነሳች። እስረኛዋም ልታደርገው ወሰናለች።

እቤት እንደደረሱ ከላይ የለበሱትን ኮቶቻቸውን አወለቁና የመጀመሪያው ታምር የተፈጸመበት ሰገነት (ሶፋው) ላይ ቁጭ አሉ። ዘሎ ሊያንቃት ምንም አልቀረው። እጇን ዘርግቶ ጠጋ አላት።

"Wait! wait! cool it baby! don't be like an animal. ok?" አለችውና ቆጣ አለች።

"We will be together all night, ok? Let's have wine first baby." አለችውና ባቱን መታ መታ አድርጋ ከቁጣዋ ከመቅጽበት መለስ ብላ ፈገግታ አሳየችው። በሪሞት ኮንትሮል የምትቆጣጠረው መሰለ።

ባላየው ሁኔታ አፈር አለና ምንተፍረቱን ብድግ ብሎ ብርጭቆዎችን አመጣና እየቀዳ እያለ፤

"Why not we order pizza or something?" አለችው።

"Are you hungry now?" አላት።

"You bet!" አለችው።

ፒዛው እስከሚመጣና እስከሚበላ ድረስ ምንም እንደማያደርግ ሲያስበው ትንሽ ቅር ቢለውም ሌሊቱን ሁሉ አብራው መሆኗን ሲያስብ ተጽናና።

ስልኩን ብድግ አድርጐ ደወሎ አዘዘ። ከአርባ አምስት ደቂቃ በኋላ እንደሚደርስ ነገሩት። ድምጹ ያለወትሮ ሰሏል። በስልኩ ሲያወራ አንዳንድ ቃላት መደጋገሙ ዴብራንም ሳይገርማት አልቀረም።

የቴሌቪዥኑን ሪሞት አንስታ እየቀያየረች አንድ የሙዚቃ ጣቢያ ላይ አደረገችው። ድምጹን ከፍ አደረገችና ዳንስ አይሉት እስክስታ አንገቷን ፣ እጇን፣ ትከሻዋን እየወዘወዘች እተቀመጠችበት ታስነካው ጀመር። ከዘፈኑም ጋር አብራ እያዜመች ብድግ ብላ ቦርሳዋን ይዛ ወደ ሽንት ቤት ሄደች።

ካሣሁን በገዛ ቤቱ የሚያደርገውን ሁሉ እየተጠነቀቀ ነው፤ ጥላው እንዳትሄድ ስለሚፈራ። ተነስቶ እንኳ ቂጡ ድረስ ለቃ የሄደችውን የቲቪ ድምጽ መቀነስ ፈራ። ሽንት ቤት ሄዳ ትንሽ ቆየችበት።

እተቀመጠበት ቁጭ ብሎ በሚጮኸው ሙዚቃ ባሻገር ሲቁነጠነጥ ከሽንት ቤት ወጣች። ለወጥወጥ ብላበታለች። ዓይኗ ደፍረስረስ ብሏል። ፍዝዝም ያለች ትመስላለች። ሽንት ቤቱን ከፍታ ስትወጣ ተከትሏት የመጣው ሽታ በጣም አልተሰማውም። አፍንጫውንም የደፈነው ነገር አለ ማለት ነው። አጅሪት ምናምን ብጤ አጭሳ ነበር።

መብራቱን ደብዘዝ አደረገችና እተቀመጠበት ቁልቁል ታየው ጀመር። ቀና ብሎ አያት። ፈገግታ ሰጠችው።

"Forty five minutes?" አለችው። የለበሰችውን ሱሪ ቁልፍ እየፈታችና ቁልቁል ምርኮኛዋን እያስተዋለች።

"እ!" የሚለው ጠፋው።

"A lot can be done in half an hour."

ሱሪዋን ወደታች እየገፋችው በወረደ መጠን የካሣሁን ዓይን እየፈጠጠ ሄደ። ሱሪዋን እታች አደረሰችውና ጫማዋን አንዱን በሌላው እየገፋች አውጥታ አሽቀንጠረቻቸው። የተወረወረው ጫማ ቴሌቪዥኑን ለጥቂት ሳተው። ባት ባቷን እያየ የሚያደርገው ጠፋው። የልቡ ምት ፈንቅሎት ሊወጣ ደርሷል።

"What are you waiting for?" አለችው።

ዘሎ አቀፋት።

"No! take off your clothes."

እየተንቀጠቀጠ ልብሱን እያወላለቀ ጣለው። በውስጥ ሱሪው ብቻ ቀረ።

"Everything!!" አለችው ሲቃ በተመላበት ጩኸት።

"Everything?" አለ ለቅሶ በመሰለ ድምጽ።

"I said everything!" አለችውና እሷም አውጥታ እርቃኗን ቆመች ፊትለፊቱ።

እሱም አወለቀና ቆመ። ሰው ቢያየውስ? በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ እርቃኑን ሴት ፊት ሲቆም።

ትክ ብላ አየችው። ዓይኗን ወረድ ስታደርግ እንደማፈር ብሎ አንገቱን ሰበረ። ጠጋ አለችና በጣቶቿ ከላይ ከአንገቱ አጠገብ ጀምራ በቀስታ ትዳስሰው ጀመር። ጣቶቿ በሚሰሩት ተዓምር ካሳሁን ጠቅላላ ሰውነቱን ይነዝረው ጀመር። እንደ እንጨት ደርቆ ሲቆም፤

"Why are you standing there like a statue?" አለችው።

ዓይን ዓይኗን ከማየት በስተቀር ማድረግ ስለሚገባው ነገር ያወቀ አይመስለም።

እጁን በእልህ ሳብ አደረገችና አንገቷ ስር አስገብታ ተወችው። እሱም ያሻሻት ጀመር። እያሻሸችው የበለጠ ጠጋ አለችው። አስተሻሸቱንም ያጣበት ይመስል አንድ ቦታ ብቻ ገላ እንደሚያጥብ ሰው ሲሞዠርቃት ጊዜ እጁን ወደምትፈልገው ቦታ በእጇ መራችው። ቦታውን ቀደም ብሎ በእጁ ነክቶት የማያውቀው ቦታ ስለነበረ ትንሽ ቅፍፍ ቢለውም የነበረበት ሁኔታ እንዲያደርግ አስገደደው። እሷስ ቢሆን እሱንስ እየነካችው አይደል?

የጋለው ትንፋሿ አንገቱ ስር ተሰማው። ስሜቱ ግሎ ጧ ሊል የደረሰ መሰለው። ሳያስበው ከአንገቱ ስር ተፈትልካ ወጥታ ከንፈሩን ጉረሰችው። ምላሷን አፉ ውስጥ ሞላችው። መቆም አቃተው። አንደኛው እጇ ከታች የሚሠራው ሥራ ጠቅላላ ሰውነቱን የሚወረው ነገር ፈጠረ። የሚሟሟም መሰለው።

በአፏ ከንፈሩን ለቃ አንገቱን፣ አንገቱን ብላ ደረቱን፣ ደረቱን ብላ ሆዱን፣ ሆዱን ብላ እምብርቱን፤ እምብርቱን ብላ ከታች በእጇ የያዘችውን ስትጠጋ ያልታሰበ ጩኸት አቆማት። ካሣሁን አልነበረም የጮኸው፣ ሌላም ሰው አልነበረም በቦታው፤ ትታው ወንበሩ ላይ ቁጭ አለች። ብሽቅ አለች። ካሣሁን ፈዞ እንደቆመ ነው።

"Pick it up!" አለችው በጩኸት።

"Pick what?" አላት ግራ ገብቶት አሁንም ለቅሶ በመሰለ ድምጽ።

እንደ ብራቅ ጮሆ አስደንግጦ ያላቀቃቸው ለፒዛው ትዕዛዝ ብሎ አጠገባቸው አምጥቶት የነበረው ስልክ ተደውሎ ነው።

(ታሪኩ በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል።)


====================================

"ላንዳፍታ"ን

ማከፋፈል ለምትፈልጉ፤


የ"ላንዳፍታ"ን መጽሔት በየአካባቢያችሁ
በማከፋፈል ለመጽሔቷ ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግ
የምትፈልጉ በስልክ ቁጥር
(404) 728-9122 አነጋግሩን።
ለአከፋፋዮች ከ20 እስከ 25 በመቶ ኮሚሽን
እንከፍላለን።

====================================




# አዳም ና ሔዋን

©



# አዳምና ሔዋን

"እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጐ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፤- 'ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት፤ . . ."ኦሪት ዘፍጥረት፤ ም. 1 ቁ. 27-28

## ጋብቻን በዕቅድና በጥናት!

ከየሠራህ ወርቅ
(አዲስ አበባ)

በ2ኛ ዓመት ቁጥር 1 "ላንዳፍታ" መጽሔት "ጋብቻን እንፍራ!" በሚል ርዕስ አቶ እንዱዓለም ላቀረቧቸው ጥያቄአዊ መጣፍጥ መልስ ለመስጠት የእያንዳንዱን ሰዉ ርብርቦሽ ይጠይቃል። ምክንያቱም ፀሐፊዉ ብዙ ሊገነዘቧቸዉ የሚገቡ ነጥቦች ይኖራሉና። ቀሪዎቹን ግላዊ አስተያየት ለሌሎች ኢትዮጵያዉያን ትቼ እስቲ በንፁህ አመለካከት የምለዉን ልበል።

አቶ እንዱአለም በመግቢያቸዉ ላይ በአግባቡ እንዳስቀመጡት ዛሬ የምንገኝበት የሳይንስና የቴክኖሎጂ ምጥቀት በዉጥንቅጥ የኑሮ ደረጃ ላይ ያለነዉን የዓለም ሕዝቦች ጉድ ያሰኙና ያሰደነቀ ነዉ። በእርግጥ ግኝቱ ዕድገቱ ያልተጠበቀ ሣይሆን በረዥም ጊዜ የሠዉ ልጅ የምርምር ጥረት እዉን የሆነ ነዉ። ይልቁንስ አሳኙ ነገር ከአህጉር የሰይና የምድር ያህል ልዩነት መኖሩ ነዉ። ይህም ማለት በሰጠነዉ ዓለምና በታዳጊ አገሮች መካከል ያለዉ እጅግ በጣም ሠፊ የዕድገ ልዩነት ሆኖ መታየቱ አልቀረምና።

ጠያቂዉ ታዲያ ይህንን ዕድገት አጭርና ግልፅ በሆነ አባባል ጠቁመዉን ወደ "ድንጋይ ዳቦ ዘመን" ወይም ወደ "ጥንታዊ ሥርዓት" የኋሊዮሽ የሄዱ መሰለ። እንደ አጀማመራቸው ወደፊት ቢንደረደሩም ኖሮ ምንኛ ጥሩ በሆነ። ሆኖም ግን ይህ ሊሆን ባለመቻሉ አልሆነም።

ለመሆኑ ፀሐፊዉ እዉነት ከልባቸዉ የሚቀጥለዉ ትዉልድ ይኖርበታል የምትባለዉ ዓለም(ምድር) ሰዉ አልባ ትሆናለች ብለዉ ያስቡ ይሆን? ይህ ማለት ዛሬ ያሉበትን የዓለማችንን ሁኔታ በዉል እንዳልተረዱት ያስገነዝበናል። የዓለም ሕዝብ ቁጥር እኮ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ መጥቷል። እንደ እሳቸዉ ግምት ሣይሆን ዓለም ለሰዉ ልጆች መኖሪያ ትጠባለች የሚል ስጋት ፊት ለፊታችን ተደቅኗል። ይህም በመሆኑ እኮ ነዉ በተለይ በታዳጊ ሀገሮች ያለዉ ገደብ ያጣ የቤተሰብ ቁጥር መጨመር እንዲገታ እየተወተወተ ያለዉ። ይህንን ስል ታዲያ ጋብቻ አያስፈልግም ወይንም ደግሞ የዓይን ማረፊያ አይፈጠር ማለቴ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ። ጥቅል አባባሌ የሰዉ ትዉልድ "ይጠፋል" የሚለዉ ስጋት ሊኖር አይገባም ለማለት ነዉ። ለሰዉ ልጅ ከምድር ገጽ መጥፋት ስጋት የነበረዉ የኒዩክለር ጦር መሣሪያና የቀዝቃዛዉ ጦርነት አሳሳቢ አደጋ በምሥራቅ አዉሮፓ በመፈረካከስ እፎይታን ከሠጠን ወዲህ የሚቀጥለዉ ትዉልድ የመኖር ሕልዉና እንዲቀጥል (እንዲኖር) የሚያደርገዉ ዕድል ሚዛኑን ደፍቷል።

ወንድሜ እንዱአለም ዛሬ እድሜያቸዉ እየገፋ በመምጣቱና በጊዜያቸዉ በአግባቡ ባለመጠቀማቸዉ ኢትዮጵያዊ ወገኔ ናቸዉና ሀዘኑ የእኔንም ጎን መዉጋቱ አይቀርም። አሁንም ቢሆን ግን ብሩህ ዕድላቸዉ ያከተመ አይመስለኝም ።

ስለ ተቃራኒያቸዉ በዉጫዊ ገጽታ ብቻ ብቃት የሌለዉ ጥናት አድርገዉ "መሽቶብናል" በሚል ፈሊጥ ምንም እንኳን እህታችን ባል ፈላጊ ብትሆንም ጥያቄዉን ወዲያዉኑ ተቀብላ አጣዳፊ ምላሽ እንድትሰጣቸዉ መጠበቃቸዉ ስህተት ነዉ።

ለዚህ ነጥብ እውነተኛነት ራሳቸዉ ፀሐፊዉ "የሚተዋወቁት ሰዎች በተወሰነ ደረጃ ላይ መስማማት እንደሚገባቸዉና መደራደር ተገቢ መሆኑን" አስምረዉበታል በጣም ተቸግረዉና ተጨንቀዉ ሊሆን ቢችልም በሌላ ገጽታቸዉ ደግሞ "...ለዘላቂ ግንኙነት የምናቀርበዉ መስፈርት ከባድ ስለሚሆን አይሳካም፤ ሁለት ሰዎች በመልክ የሚለያዩትን ያህል በጠባይም በዓላማም በብዙ ነገር ይለያያሉ። ሁለቱም ፍፁም አንድ የሆነ አመላካከት ሊኖራቸዉ አይችልም ይህ እስኪሟላ ብሎ መጠበቁ መክረም ነዉ ፤ ሞኝነትም ነዉ።..." ብለዋል። ይቅርታ ይደረግልኝና አቶ እንዱ አለም አባባላቸዉን መርምረዉት ይሆን? ወይንስ ብዕራቸዉ ወረቀት ላይ ያፈሰሰዉን ብቻ ነው ያቀረቡት? እንዴ! ይህ እኰ ትክክለኛ ጐዳና አይደለም!! የሰዉ ልጅ በሁለንተናዊ መልኩ እንደሚለያይ ቢታወቅም፤ አንድ አካል አንድ አምሳል ለመሆኑ የተዘጋጁ እና የተዋሃዱ ሰዎች ፍፁም እንኳን የማይወጣለት አንድ ዓይነት የሆነ ባህርይ ይላበሳሉ ለማለት ባያዳግተኝም፤ የተቀራረበና ሊያጣጥማቸዉ የሚችል መንፈሳዊና አካላዊ አንድነት እንዲሁም አመለካከት

እንዲኖራቸዉ ማስፈለጉ ሊታመንበት ይገባል። አለያማ የሚቀጥለዉ የኑሮ አቅጣጫ ንትርክ፣ ጭቅጭቅና መለያየት ይሆናል። ይህ ደግሞ በቤተሰብ ምስረታ ሕይወት ዉስጥ አደገኛዉ ጉዞ ነዉ። ስለዚህ ጋብቻ ደረጃ ላይ ከመድረሳችን በፊት መግባባት፣ መጣጣምና ባህርያዊ አንድነትን፣ መቻቻልንና መተሳሰብን ቀድሞ መፍጠር አይገባም ይላሉ?

ጥሩ ቤተሰብ እኮ የጠንካራና ጤናማ ሕብረተሰብ መሠረት ነዉ። እንዴት ዛሬ ባለንበት ደረጃ ላይ ስለአባቶቻችንና እናቶቻችን የጋብቻ ሁኔታ ይገመግማሉ? እሺ! አስፈላጊ ከሆነ ይህንንም እንመልከተዉ። ከጅማሬዉ አንስቶ ፍቅር ያልተለየዉ ጋብቻ ባይጠፋም ምን ያህሉ ቤተሰብ ነበር ጥሩ የትዳር ሕይወት የመራዉ? በእዉነት ረዥም ዓመታት አብረዉ መኖራቸዉን ብቻ ቆጠሩት እንጂ ትዳራቸዉ "የጡንቻ" እንደነበር ንፁህ በሆነ ሕሊና ሊያስተዉሉት ፍቃደኛ ይሆናሉ? ባልተማሩት "ጥንታዉያን" ቤተሰቦንና በሳይንስና ቴክኖሎጂ የዕድገት ሂደት ዉስጥ ባለነዉ "ቀለም በጠጣን ሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን የጋብቻ ሂደት በንጽጽር መመልከትዎ ስህተት ብቻ ሣይሆን የአመለካከት ኋላቀርነት ነዉ ብል እንደ ዘለፋ ይቆጠርብኝ ይሆን?

አቶ እንዱአለም እንዳሉት በተቃራኒ ጾታዎች መካከል የሚደረግ ግንኙነት ሥርዓት የያዘ መሆን አለበት። ይህንንም በትክክል እንዳብራሩት ፍቅርና መተሳሰብ ያለዉ ዘላቂ የሆነ ግንኙነት ማለት ነዉ። ይህ ተገቢ የሆነና አስፈላጊ የሆነ ጋብቻ ነዉ። ይህንን በባለቤትነት ለመጐናፀፍ ግን እርስዎ የተጓዙበት መንገድ ለዉጤት አያበቃም። ይልቅስ ልጅቷ የእዉነተኛ ጋብቻ አቅጣጫ ልታሳይዎት ሞክራ ነበር በዕድሉ ሊጠቀሙበት አልቻሉም እንጂ።

ሌላዉ የእርስዎ ችግር የጥያቄዎ ጨዋነት የጐደለው መሆን ይመስለኛል። ምንም እኮ በሠለጠነዉ ዓለም ውስጥ የምንገኝ ወይንም የሣይንስና ቴክኖሎጂ ዘመ ትዉልዶች ብንሆንም አግባብ ያለዉ አቀራረብ ከሁሉ የተመረጠ ነዉ። ተዘንግቶዎት ቢሆን እንጃ እንጂ ኢትዮጵያዊ ባህላችን፣ ስብዕናችንና አቀራረባችን በዓለም ሕብረተሰብ ዘንድ ተወዳጅነት ያተረፈልን ነው። በዚህ ዓይነት አቀራረብዎ "ምንም ትሁን ምን እጅና እግር ያላት ትሁን እንጂ ግድ የለኝም፤" ወደ ማለት ቢደርሱም እኔ ደግሞ ይህንንም የሌላትን እንዳያጡ በጣም እሰጋለሁ። የእርስዎ ሌላዉ ችግር የእድሜዎ በፍጥነት መሄድ መሠለኝ። ዳሩ ምን ያደርጋል? ልጅነት እንኳን ደግሞ ተመልሶ አይገኝም። ምናልባት ከሞት በኋላ ዳግም ሕይወት እንኳን ቢኖር ካቆምንበት ዕድሜ በመቀጠል የምንዘልቀዉ የሚሆን ይሆናል። ታዲያከተገቢዉ በላይ ሣይጨነቁ ከአሁኑ ትኩረት

ቢያደርጉበት አይሻልም። በበኩሌ እንግዲህ አንዳንድ የስህተት አቅጣጫዎችን የጠቆምኩዎት ቢሆንም የተሰባሰቡና የተጨመቁ ጥቂት ምክር አዘል ሀሳቦችን ደግሞ ላቅርብ እነዚህን ሀሳቦቼንና ጥቅል አስተያየቴን ሣቀርብልዎት ግን እኔም የአመለካከቴ እንጂ በዚህ የሙያ ዘርፍ የተካንኩኝ አለመሆኔን እንዲያዉቁልኝ በቅድሚያ አሳስበዎታለሁ።

1ኛ.በተቻለ መጠን ከድምጽ በፈጠነ ጉዞ ላይ ካለዉ የዕድገት ደረጃ ጋር ራስዎን ለማጣጣም በቅድሚያ ዝግጁ ይሁኑ።

2ኛ.የዓለም ሕዝብ ቁጥር ከተገቢዉ በላይ ለመጨመር አስተዋጽዎ ለማድረግ ከመዘጋጀት ይልቅ ከአንድ ሁለት ይሻላል የሚለዉን መርህ ተከትለዉ የትዳር ጓደኛዎን ፣ እዉነተኛ አጋርዎንና መካሪዎን፤ በአጠቃላይ ደግሞ ሁሉንም ልትሆንለዎ የምትችል ዘላቂ ባለቤት (የትዳር ጓደኛ) ለመምረጥና ለማግኘት እንዲሁም ሳይበዛና ሳይንዛዛ ለዘር የሚሆን ፍሬ ለመተካት ብቻ ያስቡ።

3ኛ "መጠነኛ መተዋወቅ" የሚለዉን ከመንደርደሪያ ጽሑፍዎ እንደረተዳሁት ከሆነ እርስዎ ክትትል አደረጉበት እንጂ እርሷ ዕድል አግኝታ ስለእርስዎ የምታዉቀዉ ያለ አይመስለኝም። ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ሣይኖርና "ስለመሸብዎ" ብቻ ይሁን ጥያቄ እንደ ዱብ ዕዳ አቅርበዉ በምላሹ መናደድዎ ከስህተትም ስህተት ነዉ።

4ኛ "ላንዳፍታ" በጥያቄ መጨረሻ "አካላዊ አንድነት የጠነከረበት፣ መንፈሳዊ ዉህደት የጐለበተበት፣ ፍቅር ማሠሪያዉ የሆነለት ጋብቻ ወንዝ ዳር እንደተተከለ ዛፍ ነዉ ።" ብላ አስተምራዎታለች። እነዚህ ሁሉ ደግሞ የሚገኙት በቅድመ ጋብቻ ነዉ።

5ኛ የሚያቀርቧቸዉ ሀሳቦች እርስ በርስ ባይምታቱ እጅግ ይመረጣል። ወደማጠቃለዬ ከመሄዴ በፊት ግን እስከ 200 (እ.ኤ.አ) የታዳጊ አገሮች ሕዝብ በ1600 ሚሊዮን ሲያድግ የእርሻዉ ምርት ዉጤትና ምርታማነት ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሊከተል የሚችለዉ ችግር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በዚህ ረገድ FAD እስከ 2000ዓ.ም ባደረገዉ ትንባታዊ ስሌት የ90 ሀገሮች ስሌት ተንብይዋል። ከተጠቀሰዉ ቁጥር አገሮች ግማሹን ሕዝብ በሚይዙት ከ34 በማያንሱ ሀገሮች የምግብ አቅርቦቱ ሲታይ የነፍስ ወከፍ ድርሻ በቀን አስፈላጊ ከሚባለዉ ዝቅተኛ የምግብ ካሎሪ ያነሰ ይሆናል። ለንጽጽር ያህል በለሙ ሀገሮች ዉስጥ 213 ሚሊዮን ቶን ከፍጆት ዉጭ የሆነ ትርፍ የምግብ እህል ሲኖር በታዳጊ ሀገሮች የ165 ሚሊዮን ቶን እጥረት ዮኖራል።ምናልባት አቶ

እንዱዓለም አሜሪካ የሚገኙ ከሆነ በዚህ ትርፍ የምግብ እህል ተከራርተዉ ይሆን የዓለምን ህዝብ ቁጥር ለማሣደግና ስለወደፊቱ ትዉልድ ይህንን ያህል የተጨነቁት?

እንዲያዉም የሚቀጥለዉ ትዉልድ በመጨናነቅ ብዛት የችግር ቀበኛ ሆኖ እርስዎንና እኔን ጨምሮ ሌሎች የሚያልፉ ትዉልዶችን እንዳይረግም የጋብቻ ዕቅድ ያለፉ አፈፃፀሞችን መሠረት በማድረግ በየጊዜዉ የተከናወኑትንና የወደፊቱን ጉዳና የመቀየስ ሂደት ነዉ። ለዚሁም "የጅብ ችኩል..." እንዳንባል ለረዥም ጊዜ ዓላማዎቻችን ስልቶችን እያዘጋጀን መጠናናቱና ከዚያም መዋሀዱ ይበጃል።

ከዋልተር ትሮቢሽ መጽሐፍ ተወስዶ በአዲስ ዘመን አድማስ አምድ ላይ ታትሞ ከወጣዉ ጽሑፍ ትንሽ ቀንጨብ አድርጌ ሃሳቤን ልቋጨዉ።

"ሁለት እጮኞሞች ለመጋባት እኔ ዘንድ መጡ እኔም ከተዋወቅሁአችሁ በኋላ 'ምን ያህል ጊዜያችሁ ነዉ?' ብዬ ብጠይቃቸው 'ከተዋወቅን 3ኛ ሣምንታችንን ጨርሰን 4ኛዉን ሣምንት ጀምረናል።' የሚል መልስ ሰጡኝ። 'ይህ በጣም አጭር ጊዜ ነዉ፤ ቢያንስ ቢያንስ ተዋዉቃችሁ አንድ ዓመት መቆየት አለባችሁ፤ እንዲያዉም ሁለት ዓመት ብትቆዩ የበለጠ መድህን ያለዉ ይሆናል፤ እርስ በእርሳችሁ መተያየት ያለባችሁ በበዓላትና በሰንበት ቀኖች የምትለብሱአቸዉን ንፁህ ልብሶች ለብሳችሁ ብቻ ሣይሆን፤ አንቺም የሥራና የማዕድቤት ልብስሺን ለብሰሽ፣ አንተም ተራ የሥራ ልብስህን ለብሰህ ጢምህን ሣትላጭ እንዲሁም በተበሳጫችሁና አደጋም በደረሰባችሁ ጊዜም መገናኘት አለባችሁ።" ይላል። አሁንስ? እቶ እንዱአለም ተግባባን?

በመጨረሻም ምንም እንኳን አመለካከትን ማንፀባረቅ መልካም ቢሆንም ለብዙሀን ጆሮና እይታ ከማድረስዎ በፊት እርስዎ ራስዎ ከሀሳብዎ ጋር ጥቂት ቢጋጩና ቢፋጩ ኖሮ፤ በመቀጠልም የቅርብ ጓደኞችዎንና ወዳጆችዎን ቢያማክሩ ምንኛ ጥሩ ነበር? ግድየለም አሁንም ለእኛ ወገኖችዎ ነዉና ያቀረቡት ለከፋ አይሰጥም። በጣም የማደንቅዎት ግን ለመማር ዝግጁ መሆንዎን በመረዳቴ ስለሆነ ሊመሰገኑ ያስፈልጋል።

በበኩሌ መልዕክቴን እዚሁ ላይ እየገታሁ ደህና ሁኑልኝ እያልኩ እሰናበታለሁ። እግዚአብሔር በቸር ይግጠመን።

## ሴቶች ምን ይላሉ ?

### አንድ ወንድ አንዷን ገና ሲተዋወቃት፤-

- ለፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ብቻ የሚያስባትና ስለልጅቷ ያለው ግምጋሜም በዚሁ ላይ ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ሴትን 'ለፍቅር ዕቃነት' ብቻ እንደተፈጠረች አድርጉ እንደማሰብ ስለሚቆጠር እባካችሁ ወገኖች አስተውሉ!

- ስለራሱ ብዙ የሚያወራ ከሆነ ችግር አለበት ማለት ነው።

- የስልክ ቁጥሩን ሲጠየቅ የሚደብቅ ከሆነ ወይ ባለትዳር ነው ውሽማ የሚፈልግ፤ አለበለዚያም በቴሌፎን ዕዳ ስልኩ የተቆረጠበት ነው።

- "መቼ ነው ወደ አሜሪካን የመጣሽው?" ብሎ ጥያቄ ከጀመረ ከመጣ የከራረመ ሆኖ ስለ አሜሪካ የበለጠ አዋቂነቱን ለመግለጽ የተዘጋጀ ጉረኛ ነው።

## ወንዶችስ ምን ይላሉ ?

### አንዷን ሴት ገና ስትተዋወቃት፤-

- ብዙ ከለፈለፈችና አላስወራ ካለች እንዳትጠየቅ የምትፈራው ነገር አለት፤ ወይም አንድ ራሷ የምታውቀው የምትደብቀው ነገር አላት ማለት ነው።

- ስለ ኑሮ ችግር ብቻ የምታወራ ከሆነች የኑሮ ችግሯን የሚያቃልልላት ወንድ እየፈለገች ናት ማለት ነው።

- ስለ ጓደኞቿ ብዙ ካወራችልህ፣ ስላንተም ብዙ ታወራዋለች ማለት ነው።

---

አዲሱ አድራሻችን፤
LANDAFTA
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359 ነው።

# « እኔ ልጅት አበሻ ወንድ አልጠይቅም . . . »

(ለወይዘሪት "Don't Give Up" መልስ)

ኤደን
ከዋሽንግተን ዲ.ሲ.

ይህን ጽሑፍ እንድልክ ያነሳሳኝ ባለፈው እትም "በእኔው የደረሰ" በሚል ርዕስ ወይዘሪት "ዶንት ጊቭ አፕ" የጻፈችው ነው። የእሷን ያህል ጥንካሬ አጥቼ ሳይሆን በኔ በኩል ከወንዶች እንድገለል ያደረገኝን ምክንያት ሳሰላስል ዛሬም ስለሚገርመኝ ነው። ከገጠመኜ ልነሳና ከ"ዶንት ጊቭ አፕ" ጋር ልወያይ።"

ስለኛ ከተማ ወንዶች ሳጫውትሽ መጀመሪያ መሰለኝ። ወዲህ ወዲያ ተሯሩጦ ዲግሪ የማይጠይቅ ሥራ አይታጣም መቼስ። ዛሬ በአገራችን ከአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን እኩል የወር ደመወዝ በአንድ ቀን አትርፎ የሚገባበት ሥራ ቢኖር ዌይትረስነት ነው። በአበሻው ሬስቶራንት በsale የተገኘ ልብስ ፈልጎ ወይም ተከራክሮ ቅናሽ ሳይጠይቅ ከ$200 ባላነሰ ወጪ የገዛትን ውድ ልብስ ለብሶ፣ ተሽቀርቅሮ ያንኑ ለማሳየት፤ "አቤት የለበሳት ሸሚዝ እንዲባልለት፣" የሚፈልገው የአገሬ ጉብል እኔ እሠራበት ከነበረው ሬስቶራንት ብቅ ይላል። አይ ዝነጣ፣ አይ አረማመደድ። ታዲያ አካሄዱ የከተማ፤ ጉርሻ አሰጣጡ የ . . .፤ (ምክንያቱም የደከመበት ስለማይመስለው)። እኔም ታዲያ ሽር ጉድ ብዬ ለአንዳፍታ እንኳ ሃሳቤን ከሥራዬ ዘንበል ሳላደርግ በሲጋራ አመድ የተሞሉትን አሽትሬዎች ከፊቱ እያጸዳሁ ደጋግሜ የሚፈልገውን በመጠየቅ የምተዳደርበትን ጉርሻ ስጠብቅ ለአፍ መጥረጊያ ከተቀመጠለት ወረቀት (ናፕኪን) የስልክ ቁጥሩን፤ ስሙን እንዲሁም "ፈገግታሽ ስላስደሰተኝ ደውይልኝ፣" የሚል ማስታወሻ ጽፎ ከ$20 ብር ጉርሻ ጋር (የ$10 ብር ምግብ በልቶ እኮ ነው) ሰጥቶ እየተጀባነነ ወጥቶ የሚሄድ አለ። እስከ ሌሊቱ አስር ሰዓት ሲጠጣ ይቆይና ሞቅ ሲለው መቀመጫዬን ለመዳሰስ የሚጋበዝም አለ። በርከት ያለ ጉርሻ ሰጥቶ እቤት የማደርሳት እኔ ነኝ በሚል ራይድ ካልሰጠሁ ብሎ የሚጋበዝም አለ። ስንቱን እንደምነግርሽ አይገባኝም። እዚቹ ላይ እንዳልረሳ ልንገርሽን በቅርቡ ከኢትዮጵያ የመጣች በሙያ የሠለጠነች እህታችን ጓደኛዬ ናት። Carry Out በሚል ስያሜ "ዝጉብኝ" በሚል ቅጥያ ስም ያለው ሥራ ትጀምራለች። እንዳጫወተችኝ ውድቅት ሌሊት ላይ መጥቶ ምግቡን ተመግቦ "ታዲያስ ያልጋ ስንት ነው?" ያላት ዘመናይ እንዳጋጠማት ነግራኛለች።

ወደዚሁ የእኔ የአሜሪካ ገጠመኞች ልመልሳችችሁ። ከሬስቶራንት ባለቤቱ እስከ ወጥ ቤቱ ብል ማጋነን አይሆብኝም የትኛው ከፍ ያለ ጉርሻ እንደሚሰጥ ማን ለምን እንደሚመጣ ስለምናውቅ ለእኛ አዲስ አይደለም። ስላለው ወይንም በሚሰጠው ጉርሻ ብቻ ሳይሆን በቁመናው ወይም በሥነሥርዓቱ ተሸንፌ በዕረፍት ጊዜዬ አብሬው የተዝናናሁት ጉብል በሚቀጥለው ቀን የስልክ ቁጥሬን ከሚያጨሰው የሲጋራ ቁራጭ ጋር አብሮ ሲጥለው፤ አዲስ የገባችው አስተናጋጅ ተረኛነቱን ትቀበላለችች። ለአዲሲቱ አስተናጋጅ ጉራውን መነስነስ ይጀምራል። በቅርብማ ከአገር ቤት የመጣች ከሆነች ጆኒያ ሙሉ ጉራ ያጠብቃታለል። ስለተለያዩ ሬስቶራንቶች ሲያወራ የሬስቶራንቶቹ ባለቤት ይመስላል። ይህ እንግዲህ በኔም ሆነ በሥራ ባልደረቦቼ የተለመደ ስለሆነ ከሚያስፈልገው በላይ ጉርሻ መስጠት ከባላገርነት ሌላ ሌላ ስም አለላገኝለትም።

አንባብያን ምናልባት በአንድ ወንድ ሪጀክት ስለተደረገች ነው እንዲህ የምትለፈልፈው፤ ሁሉም ወንድ አንድ አይደለም ወይንም ትልቅ ጉርሻ በአዘኔታ ስለሰጠ ባላገር ሊሰኝ አይችልም ትሉ ይሆናል። ለፍርድ ቸኮልሽ ልትሉኝ ትችላላችሁ። እስቲ ልጠይቃችሁ ስንቶቻችን ነን ታክስ ላይ 20 ወይም 30 ብር ለማስቀነስ ያገባ ብለን የምንሞላ። የሠራንበትን ገንዘብ የቴሌፎን ካምፓኒ 10 ብር ካለምክንያት ሲያስከፍለን ኡ! ኡ! የምንለው። አዘኔታ ከሆነ አገር ቤት ስንት ወንድሞቻችን $20 ቢላክላቸው (ከትልቁ ጉርሻ ይልቅ ማለቴ ነው) የበለጠ እያስመሰግንም። የሚያናድደኝ እኮ ከ$20ው ብር ጉርሻ ጋር ተያይዞ የሚመጣወው የ"መቼ ይመችሻል?" ጥያቄ ነው። እስቲ አበሻ ሬስቶራንት በዌይትረስነት የሰራችሁ ፍረዱብኝ። የገባው የወጣው ሁሉ ስልክ መስጠት እኛ ደግሞ መቀበል ከሆነ እንግዲህ ይታያችሁ እስቲ።

ይህ ቀጥዬ የምነግራችሁ የዛሬ ሶስት ዓመት ገደማ የተደረገ የኔው ታሪክ ነው። ከእንግዲህ የማንም አሻንጉሊት አልሆንም፤ ትላንት ከኔ ጋር ወጥቶ ዛሬ ጓደኛዬን የሚመኝ የአበሻ ወንድ እርግፍ አድርጌ ከተውኩ በኋላ አንዱን አገኘሁት።

በቁመናውና በሥነ ሥርዓቱ የሚከበር እንዲሁም ትምህርት ቤት እየሄደ ስለሆነ ዓላማም አለው በሚል ፈቀድኩትና እስቲ ልሞክረው፤ እስከ መቼ ቆሜ እቀራለሁ፤ ከአንድ ሁለት ይሻላል በሚል ተዋወቅሁት። የመጀመሪያው እጅ መንሻው ወደ አትላንቲክ ጉዞ ነበር። መቼም እዚህ አገር ከገባሁ ብዙ ያየሁት ነገር ቢኖርም ይህንን ቦታ ስላላየሁት፣ ብቻ ምን አለፋችሁ የመጀመሪያው ሮማንስ አስደሰተኝ፣ ዋው!! አልኩኝ። ለካ ከአመራረጤ ነው። ከሥራ እየጠበቀ ቤቴ አድርሶኝ ከእሱ የሚጠበቅበትን ፍቅር ሲያሳየኝ እኔም አጸፋውን በመመለስ ሶስት ወር ሞላን። ስማቸው ጠፍቶ ስሜን ከአጠፉት አልባሌዎች ጋር ያቃጠልኩት ጊዜ የቆጨኝ ጊዜ ነበር። በመሐል ስለ ትዳር ጨዋታም ተጀመረ። የሚቀጥለው ጉዳይ ሆኖ የተገኘው የቤተሰቦቹ ወደዚህ መምጣት ነበር። የሀይምኖትን ጉዳይ አስታክከና (እሱ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ በመሆኑ) ቤተሰቦቹ ሚስት ሊድሩት እንደሚፈልጉና የተመረጠችውም ልጅ ጂዳ እንደምትኖር አስረዳኝ። እኔ ታዲያ ይህ ፍቅራችንን የሚያቀዘቅዝ መስሎ አልታየኝም ነበር። ምርጫው የሱ እንጂ የቤተሰቦቹ ባለመሆኑ። በቤተሰቦቹ ወደዚህ መምጣት ምክንያት ለጊዜው ግንኙነታችን ተቋርጦ እሱ እንደሚደውልልኝ ነግሮኝ ተለያየን። ደቂቃውና ሰዓቱ በሳምንትና በወራት ተተኩ። ምንም የለም። "ያልታደለች በሰው ሠርግ ተዳረች፣" ሆነና ጭራሽ ተረሳሁ። የጊዜ ማሳለፊያ፣ የስሜት ማርኪያ አድርጎ እንደተጠቀመብኝ ስለተሰማኝ ውስጣዊ ቅናት አቃጠለኝ። አነባሁ። መቼም የአገራችን የኪነት ባለሙያዎች ወጥተው ወርደው መልስ ያላገኙለት ጥያቄ ሁሉ በአንጐሌ ተጉላላ። ፍቅር ምን ዓይነት ይሆን? መውደድ ማፍቀር የሚገባንስ ማንን ነው? ደግሞስ መቼ ነው? አልኩኝ። ጥላሁን ገሠሠ፤-

"ጥቁር ነው ጠይም ወይስ የቀይ ዳማ፤
ዘርዝሮ የሚያስረዳኝ በውነት ካለማ?"

ያለው እውነት ሞክሮ ሰልችቶት ይሆን?

"አቃጠለኝ፣ የማደርገው ጠፋኝ . . ."

ያለቺው የኪነት ባለሙያም ግጥሞች ሁሉ በአዕምሮዬ ተመላለሰ።

ስለፍቅር ማውራት ጊዜውም አይፈቅድልኝም። የሚያውቀው ያውቀዋል። እንዲሁም ወይዘሪት "ዶንት ጊቭ አፕ" እንዳስቀመጠችው "ሴትና በቅሎ . . " ከሚባሉት ተራም ውስጥ አይደለሁም።


ከላይ ከጠቀስኩት የቀድሞ የሶስት ወር ፍቅረኛዬ እልህም ይሁን በቀል ወይንም ቅናት አኳያ የፈለጋችሁትን በሉ ብቻ እጅሬ የደረሰበትን መከታተል ጀመርኩ። ከታወቁት አዲሶቹ ሬስቶራንቶች አንዱ ዘፋኝ እጅ መውደቁን ሰማሁ። ጣዕሟ ሲያልቅ ይወረውራት ይሆን? ወይንስ እኔ የሌለኝን እሷ ምን ስለያዘች ይሆን የሚለውን ሳወጣና ሳወርድ ሰነበትኩ። መድረክ ላይ በዘፈነች ቁጥር ዓይን ዓይኗን ሊያያት ነው? ወይስ ደህና አድርጐ ከቀመሳት በኋላ ሊሸኛት? ሲሰለቻው "የአጐቴን ልጅ አባቴ ሊድረኝ ነው" ይላት ይሆን? መቼም ተነቦ የማያልቅ ልብ ወለድ እንደሆነብኝ ወራት በዓመታት ተተኩ። በቀል ያዝኩኝ እኔ ልጅት። ቂሜን መወጣት ጀመርኩ በሌላው። አበሻ እንደተጠቀመብኝ፣ አልጋ ላይ እስኪያደርሰኝ እንደሚቸኩል ስለተረዳሁ ማመልከቻው እስከሚጠና ካልደወልኩ መደወል አይኖርበትም። እንዲያውቀውም የምፈልገው እሱ በተለያየ መንገድ ከሚያገኘው ገንዘብ በላይ በሳምንት ሳይሆን በቀን እንደማገኘው እንዲገባው ነው። ጭክኔ አስመሰለብኝ ይሆን?

በይሉኝታ የተከበብን ስለሆን እንኳን ወይዘሪት "don’t give up" እንዳለችው እኔ ሄዋኒቱ ወንድ ጠይቄ ጓደኛ ሳደርግ ይቅርና አዲስ ለሚመጡት የዋህ ዘመዶቼ አስተምራለሁ። ወይዘሪት "don’t give up’ እንዳልሽው እናንተ ከተማ አትላንታ ወንዱ ጨዋ ይሆናል፣ ከመርካቶና ከአስኮ የሚመጡ ወንዶች ገራገርና ጨካኝ አይታጣባቸውም አይደል? ተስፋ በመቁረጤም ቆሜ የምቀር አይደለሁም፤ ካለፈው ስለተማርኩ ኑሮዬን በመልኩ እገነባለሁ ብዬ አስባለሁ።


ደግሞ ይታይሽ "Don’t Give Up" እኔ የጠየቅሁት ወንድ "ይገርማችኋል "እከሌ እኮ ጠየቀችኝ እያለ እየዞረ ጉራውን ሲነዛ። ከዚያም አልፎ ከኩራት ብዛት ሲምበጣረር። ታየሽ። ታዲያ ይህን ምኑን ፍቅር ብለሽ ነው ወገኖቼን የምትመክሪ። ይልቅዬስ ወንዱ ሥርዓት ያለው ፍቅር ሊመሠርትበት የሚችልበትን መንገድ ብትመክሪ አይሻልም።

እኔ ግን ልንገርሽ፤ "እኔ ልጅት የአበሻ ወንድ ስለምን አልገኝም። ገባሽ።

---




# ጓደኛ ለሚፈልጉ




ጓደኛ ፈላጊዎች ራሳቸውን አስተዋውቀው፣ ሊተዋወቁ የሚፈልጉትን ሰው ዓይነት የሚጠቁሙበት አምድ ነው። ስምና ትክክለኛ አድራሻ በመጽሔቱ ላይ አይወጣም። በስምና አድራሻ ፋንታ የኮድ ቁጥር ይወጣል። የኮዱን ቁጥር የምንሰጠው እኛ ነን። በስምና አድራሻ ምትክ የኮዱ ቁጥር ይወጣል። ስምና አድራሻ እኛ ጋ በምስጢር ይቆያል። ትክክለኛ ስምና አድራሻ ግን እኛ ጋ መድረስ አለበት።በጣም አጠር ተደርጐ ቢጻፍ ዕድሉን ለብዙ ሰው ማዳረስ ይቻላል።

ለመተዋወቅ የምትፈልጉት ሰው ዓይነት ወጥቶ ካገኛችሁ ቁጥሩን በመጥቀስ ደብዳቤ ጽፋችሁለት/ጽፋችሁላት እነስ ያለ ኤንቨሎፕ ውስጥ አሽጋችሁ ኤንቨሎፑ ላይ የናንተን ሙሉ አድራሻ በቀለም፣ የሚላክለትን/የሚላክላትን ሰው ኮድ ቁጥር በእርሳስ ጥጉ ላይ ጽፋችሁ በሌላ ከፍ ባለ ኤንቨሎፕ ውስጥ ከታችሁ አሽጋችሁ በአድራሻችን ትልካላችሁ። እኛም የኛን ፖስታ በመክፈት ከውስጥ ያለውን ኤንቨሎፕ አውጥተን የኮድ ቁጥር የተጠቀሰውን ግለሰብ ትክክለኛ አድራሻ ከመዝገባችን ኤንቬሎፑ ላይ በመሙላት እንልካለን። ከዚያ በኋላ እንደፍጥርጥራችሁ።

## የሚከተሉትን መመሪያዎች በደምብ አጢኑ።

1ኛ. ለፖስታና ለአገልግሎት አከፋፈሉ በሚቀጥለው ዓይነት ይሆናል፤
   ከአሜሪካ - $5.00 (በmoney order)
   ከካናዳና አውሮፓ - $6.00 (በአሜሪካ ገንዘብ፣ money order)
   ከኢትዮጵያ - ምንም አይከፈልም።
   ለ"ላንዳፍታ ቋሚ ደምበኞች (subscribers)
   (ላንዳፍታ ማዘዣ ቅጽ ሞልታችሁ ክፍያ የላካችሁ) $4.00 ብቻ ነው።
2ኛ. ዕድሜአቸው ከ18 በታች ለሆኑ ይህ አገልግሎት አይሰጥም።
3ኛ. ይህ አምድ ዓላማው ሙተዋወቂያ መድረክ ለመፍጠር ብቻ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።
4ኛ. እባካችሁ እንዲጻፍላችሁ የምትፈልጉትን ነገር አሳጥሩት።
5ኛ. በመጀመሪያ የብዕር ጓደኝነትን በማጠንከር የበለጠ መተዋወቅን እንመክራለን።

## አዲሱ አድራሻችን፤

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

---

## ከአንድ አንባቢ የተሰጠ አስተያየት፤

የቀድሞው አኩሪ ባህላችን ወጣት ወንዶችና ሴቶች ተገናኝተው የሚተዋወቁበት መድረክ በየብሔረሰቡ ባህል አዘጋጅቷል። የአሁኑ የተበረዘ ባህላችን ደግሞ በዘመናዊነት (ምዕራባዊ)ና በኢትዮጵያዊ ይሉኝታና ዓይን አፋርነት መሐል ተንጠልጥሎ ከሁለት የወደቀ ዛፍ ሁነናል። እንደ ነጮቹ በየመዝናኛው ሥፍራ መገናኘትና መተዋወቅ ያስቸግራል። በጉዞ ላይ፣ በመሥሪያ ቤት፤ በት. ቤትና በሰፈር አካባቢ ባጋጣሚ ከመገናኘት ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም። "ላንዳፍታ" ጥንቃቄ በተመላበት ዘዴ (አድራሻችንና ስማችንን ሳያጋልጣ) ጓደኞሞች እንዲገናኙ መድረክ በመክፈቱ ከማድነቄም ሌላ አመሰግናለሁ። ታዲያ በዚህ በኩል ግኑኝነት በማድረግ የሰመረላችሁ (እኔም ልሆን እችላለሁ) "ላንዳፍታ"ችንን ለማሳደግ ምን አስበናል ወይስ ጓደኞችንን እንዳገኘን ዝም እንላለን?

---

# ጓደኛ የሚፈልጉ ሴቶች

---

ስም፤ 1019፤ ዕድሜ 21 መኖሪያ ዩናይትድ ስቴት፤ ሥራ -ኮሚኒቲ ኮሌጅ ተማሪ፤ ቁመት መካከለኛ፤ ቀጠን ያልኩ የቀይ ቆንጆ፤ አላጨስም፣ አልጠጣም፤ በብዙ እስፖርት እካፈላለሁ፤ አገር መጐብኘት ወዳለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፤- የማይጠጣ፣ የማያጨስ፤ ስፖርት የሚወድ፣ በትምህርት ላይ ያለ፤ ግልጽና ተጫዋች፤ ረዥም ሆኖ መልከ ቀና፤ ዕድሜው ከ21-25፤ ነዋሪነቱ አውሮፓ የሆነ ብቻና ዘላቂ ጓደኝነት የሚፈልግ። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፤)

---

ስም፤ 1020፤ ዕድሜ 30፤ መኖሪያ ዩናይትድ ስቴት፤ ሥራ - ፉድ ሰርቪስ፤ መዝሙር መስማት እወዳለሁ። ትምህርታዊ የሆነ ሲኒማ እልጠላም። አላጨስም፣ አልጠጣም። ልጅ የለኝም ግን እወዳለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ - እውነተኛ የትዳር ጥማት ያለው፤ የሁሉ ማሰሪያ የሆነው እግዚአብሔር ነውና ቸርች የሚሄድ ቢሆን እመርጣለሁ።(በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፤)

---

ስም፤ 1021፤ ዕድሜ 25፤ መኖሪያ - አዲስ አበባ፤ ሥራ - ንድፍ ሥራ፤ ትምህርት - ዲፕሎም፤ ቁመት - መካከለኛ፤ አገሬን እወዳለሁ። ማንበብ እወዳለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ ዕድሜ ከ30-35፤ አስተዋይ፤ ከላይ የጠቀስኩትን የሚወድ፤ ትምህርቱ ከኔ በላይ የሆነ። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፤)

---

ስም፤ 1022፤ ዕድሜ 22፤ መኖሪያ - አዲስ አበባ፤ ትምህርት - ንግድ ሥራ ኮሌጅ፤ ሥራ - የለኝም። አልጠጣም አላጨስም። መጽሐፍ ማንበብ፣ ሽርሽር እወዳለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ - ጨዋታ ወዳድ፣ ለቁምነገርና ለቀልድ ቦታ የሚወስን፣ መሳቅና መደሰት የሚወድ፤ የማያጨስ፣ የማይጠጣ፤ ሰውን የሚያከብር፤ (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፤)

---

ስም፤ 1023፤ ዕድሜ 21 መኖሪያ - አዲስ አበባ፤ ሲኒየር እስኩል ዲፕሎም ለሁለት ዓመት በሥራ ላይ ፤ አሁን ሥራ የለኝም። ሙዚቃ፣ ትያትር፣ ሽርሽር እወዳለሁ። አላጨስም አልጠጣም፤ ቁመቴ አጠር ይላል። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ - የማያጨስ የማይጠጣ፣ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው። ዕድሜው ከ23-28፣ ረዘም ያለ፤(በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፤)

---

ስም፤ 1024፤ ዕድሜ -22፤ ቁመቴ 1.60፤ መኖሪያ - አዲስ አበባ፤ ሥራ - አ.አ. ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎም ተማሪ፤ ምንም ዓይነት ሱስ የለብኝም። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ - ዕድሜው ከ23-25 ቁመቱ ከኔ በለጥ ያለ፤ የትምህርት ድርጃው - ቢያንስ ዲፕሎማ፤ ምንም ሱስ የሌለው፤ አገር ውስጥ ሆነ ውጭ አገር ግዴለኝም። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፤)

---

ስም፤ 1025፤ ዕድሜ 21፤ መኖሪያ - አዲስ አበባ፤ የትግራይ ተወላጅ ነኝ፤ በኮምፒውተር ዲፕሎም አለኝ፤ ለዲግሪ መቀጠል እፈልጋለሁ። ሙዚቃ፣ ስፖርትና ትያትር እወዳለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ - ዕድሜው እስከ 30 የሆነ፤ ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ ያለው፤ ጠይም ሆኖ መካከለኛ ቁመት፤ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ያልሆነ፤ የምንም ሱስ ተገዢ ያልሆነ፤ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚኖር።(በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፤)

---

ስም፤ 1026፤ ዕድሜ 21፤ መኖሪያ - አዲስ አበባ፤ 12 ጨርሼ ኮምፒውተር ተምሬአለሁ፤ ሙዚቃ፣ ቲያትር፣ መዝሙር፤ አገር መጐብኘት፣ መጽሐፍ ማንበብ፣ ፎቶ መነሳት፣ ውሃ ዋና ወዳለሁ። ተግባቢና ተጫዋች ሰው እወዳለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ - ምንም ሱስ የሌለው፤ ሥራ ስለሌለኝ የሚያዝን፤ በዕድሜ ከኔ የሚበልጥ፤ ታማኝ፤ (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፤)

---

ስም፣ 1027፣ ዕድሜ 20፣ መኖሪያ - አዲስ አበባ፣ 12ኛ ክፍል ጨርሻለሁ፣ የጽሕፈት መኪና ዲፕሎም አለኝ፣ እስፖርትና አክሮባት አዘወትራለሁ፣ ቀንጆም አስጠሊታም አልባልም፣ ቀላ እላለሁ፣ እስካሁን ከማንም ወንድ ጋር ግኑኝነት የለኝም። ትዳር ለመመሥረት እውነተኛ ፍቅር የምፈልግ፣ መግደርደር አልወድም፣ ፎቶ ካስፈለገ እልካለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ - ከኔ ጋር መስማማት እችላለሁ የሚል። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፣)

---

ስም፣ 1028፣ ዕድሜ 22፣ መኖሪያ አዲስ አበባ፣ 12ኛ አጠናቅቄአለሁ፣ ምንም ሱስ የለብኝም፣ ለስላሳ ዘፈን፣ ማንበብና ተፈጥሮ ማንበብ እወዳለሁ፣ ውሸት አልወድም፣ ንጽህና በጣም እወዳለሁ፣በመነጋገርና በመግባባት የማምን፣ መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ - ግልጽ፣ ጨዋ፣ ሩህሩህ፣ አዛኝ፣ ለሴት ክብር የሚሰጥ፣ ሴት አያያዝ የሚችል፣ ውሸት የማይወድ፣ የማያጨስ፣ ውበቴን ማድነቅ የሚችል፣ ከኢትዮጵያ ውጪ የሆነ። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፣)

---

ስም፣ 1029፣ ዕድሜ 38፣ መኖሪያ - አዲስ አበባ፣ ሥራ - በመንግሥት መ.ቤት ኤክስፐርት፣ 3 ልጆች አሉኝ። ከባሌ ተፋትቼ ያለረዳት አሳድጌአቸዋለሁ፣ ሳቅ፣ ጨዋታ ደስታ እወዳለሁ፣ አታላይ ሰውና ውሸት አልወድም። ግልጽነት አበዛለሁ። ወንድ ልጅ እንዳላምን የደረሰብኝ ገጠመኝ ምክንያት ሆኖኛል። ለደብዳቤ ጓደኝነት፣ (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፣)

---

ስም፣ 1030፣ ዕድሜ - 22፣ መኖሪያ - ቻግኒ፣ ጐጃም፣ በልጅነቴ ተድሬ እናቴ የምታሳድገው አንድ ልጅ አለኝ፣ ከባሌም ስልተግባባን ተፋተናል፣ ለጥሩ ትዳር በጣም እጓጓለሁ። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፣ ዕድሜው ከ25-35፣ የማያጨስ፣ የማይጠጣ፣ የማይቅም፣ ለትዳር አክብሮት ያለው፣ አሜሪካ ወይም ሌላ ውጭ አገር ያለ ኢትዮጵያዊ፣ ጸባዩ ነዝናዛ ያልሆነ፣ ቀይ ወይ የቀይ ዳማ የሆነ፣ሆነ፣ ቆንጆ ጸባይና አመለካከት ያለው። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰህ ጻፍልኝ፣)

---

# ጓደኛ የሚፈልጉ ወንዶች

---

ስም፣ 1031፣ ዕድሜ 19፣ መኖሪያ - ካናዳ፣ 1ኛ ዓመት ኮሌጅ ተማሪ፣ቀይ፣ ቁመት መካከለኛ፣ ስፖርት፣ ሙዚቃ ወዳለሁ። አላጨስም፣ አንዳንዴ በመጠኑ ጠጣለሁ። ልተዋወቃት የምፈልጋት ሴት - መልከመልካም፣ ቆንጆ ፈገግታ የማይለያት፣ ተጫዋችና ሙዚቃና እስፖርት የምትወድ። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ፣

---

ስም፣ 1032፣ ዕድሜ 29፣ መኖሪያ - ሸገር (አ.አ)፣ ከኩባ ሃቫና አድቫንስድ ዲፕሎም ያለኝ፣ ሥራ - የግል ንግድ፣ መልከመልካም ነህ ይሉኛል፣ ግልጽ ነኝ፣ ጨዋታ እወዳለሁ፣ ቲያትርና ሲኒማ አዘወትራለሁ፣ መጽሐፍ አዘወትራለሁ። በርጫ ወዳለሁ (2 ወይም 3 በሳምንት)፣ ሃይማኖቴ ኦርቶዶክስ፣ እንደዘመኑ ፖለቲከኞች የዘር በሽታ አልተጸናወተኝም። ልተዋወቃት የምፈልጋት ሴት - እንደ አቀንቃኟ ነፃነት መለሰ ቆንጆ ከንፈር ያላት፣ ዕድሜ ከ25-30፣ ፍቅር ሰጥታ መቀበል የምትችል፣ ረሃብ ጨለማና ፖለቲካ የማትወድ፣ የዘመኑ የዘር በሽታ የሌለባት፣(በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ፣

---

ስም፣ 1033፣ ዕድሜ 29፣ መኖሪያ - ዩናይትድ ስቴትስ፣ መጽሐፍ ማንበብና ሲኒማ ማየት እወዳለሁ። ልተዋወቃት የምፈልጋት ሴት -የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ የሆነች፣ ዕድሜዋ ከ30 ያልበለጠ፣ ከየትኛውም አገር ቢሆን ለመጻጻፍ ፈቃደኛ ነኝ።(በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ፣

---

## ጓደኛ የሚፈልጉ ወንዶች (የቀጠለ)

---

ስም፣ 1034፣ ዕድሜ 26፣ መኖሪያ አዲስ አበባ፣ ከአ.አ. ንግድ ሥራ ኮሌጅ በሂሳብ አያያዝ ዲፕሎማ አለኝ። መጽሐፍ ማንበብ፣ ሙዚቃና ቲያትር ወዳለሁ። የተለያዩ አገሮች ፖስርተ ካርዶች አጠራቅማለሁ። ከማንኛውም ጾታ በአማርኛም በእንግሊዝኛም መልስ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ፣ (የብዕር ጓዷኛ) (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬ ተጠቅሶ ይጻፍልኝ፣

---

ስም፣ 1035፣ ዕድሜ 31፣ መኖሪያ ዩናይትድ ስቴትስ፣ B.S. ዲግሪ አለኝ፣ አሁን በግል ሥራ ላይ እገኛለሁ። እስፖርትና ሙዚቃ በጣም እወዳለሁ፣ አላገባሁም ልጅ የለኝም። ልተዋወቃት የምፈልጋት ሴት ዕድሜዋ ከ28 የማይበልጥ፣ ልጅ የሌላትና እንመዲኖራት የምትፈልግ፣ ከወገቧ ቀጠን ያለችና የደስ ደስ ያላት፣ እስፖርት የምትወድ፣ ቁም ነገር የምትፈልግ። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ፣)

---

ስም፣ 1036፣ ዕድሜ 24፣ መኖሪያ አዲስ አበባ፣ ሥራ - የመንግሥት፣ 12ኛን ጨርሼ ማታ ዩኒቨርሲቲ፣ ሙዚቃ፣ መጽሐፍ ወዳለሁ። ቀይ ቀንጆ የወንድ ቁመና አለኝ። ልተዋወቃት የምፈልጋት ሴት - ዕድሜዋ ከ18-22 የሆነች፣ ከ10ኛ ክፍል በላይ፣ ሙዚቃና መጽሐፍ የምትወድ፣ ከአሜሪካ ወይም ከአውሮፓ፣ (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ፣

---

ስም፣ 1037 ዕድሜ 20፣ መኖሪያ ሆላንድ፣ በትምህርት ላይ፣ እስፖርት፣ ሙዚቃ፣ መጽሐፍ፣ ፊልም ደስ ይለኛል። ሲጋራ አጨሳለሁ። በባህዬ የምታሳማማ ትጽፍልኝ። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊፊኝ፣

---

ስም፣ 1038፣ ዕድሜ 30፣ መኖሪያ አዲስ አበባ፣ ሥራ ንግድ፣ቀይ ዳማ ነኝ። ማንበብ፣ ሙዚቃ ስፖርትና ሽርሽር እወዳለሁ። እልጠጣም አላጨስም፣ ግልጽ ነኝ። ልተዋወቃት የምፈልጋት ሴት - ክርስትያን፣ ለፍቅር ታማኝ፣ ተማሪ ወይንም ሠራተኛ፣ ቀንጆ ፖስቸር (8 ቁጥር) ካላት መልኳ አያስጨንቀኝም፣ ጸጉሯ ረጅም፣ ዕድሜዋ ከ18 - 25። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ፣

---

ስም፣ 1039፣ ዕድሜ 29፣ መኖሪያ ናዝሬት፣ ትምህርት M Sc፣ ሥራ የመንግሥት፣ ደህና ቁመናና ለወንድ በቂ መልክ አለኝ፣ አላጨስም፣ አልጠጣም። ዝምተኛና ረጋ ያልኩ መሆኔ ይነገረኛል። ሃይማኖቴ ኦርቶዶክስ፣ በኢትዮጵያዊነቴ የማምን፣ በዘረኝነት የማላምን፣ ሙዚቃ መሣሪያ መጫወት፣ ማንበብ፣ ቲያትራና ሲኒማ፣ ሽርሽር ፣ የቤታ ውስጥ ጨዋታዎች (indoor games) እወwዳለ1። ጥሩ ትዳር መመሥረት እፈልጋለሁ። ልተዋወቃት የምፈልጋት ሴት - ዕድሜዋ ከ25 ያልበለጠ፣ ምንም ሱስ የሌለባት፣ ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት የምትሰጥ፣ ግልጽ ቅንና ታማኝ የሆነች፣ (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ፣

---

ስም፣ 1040፣ ዕድሜ 30፣ መኖሪያ ዩናይትድ ስቴትስ፣ 3ኛ ዓመት ዩኒቨርሲቲ፣ በካሽርነት ሥራ ላይ፣ ሙዚቃ፣ ማናበብና መማር እወዳለሁ። ልተዋወቃት የምፈልጋት ሴት - መልከመልካም፣ መካከለኛ ቁመት፣ የማታጨስ አስተዋይ፣ ለመማር ለማወቅ ፍላጐት ያላት፣ ሰው አክባሪ፣ በኢትዮጵያዊነቷ የምትኮራ፣ የአገር ፍቅር ያላት፣ ለዘላቂ ጓደኝነት። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ፣

---

ስም፣ 1041፣ ዕድሜ 25፣ መኖሪያ አዲስ አበባ፣ ሥራ ሕንፃ መሐንዲስ፣ ለሙያዬ ከፍተኛ ፍቅር አለኝ። ሙዚቃ፣ መጽሐፍ ማንበብ፣ ጉብኝት እወዲለሁ። የምፈልገው የብዕር ጓደኛ ነው። ከአሜሪካ ወይም ከዩናይድ አረብ ኤሚሬት ቢሆን ደስ ይለኛል።(በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬ ተጠቅሶ ይጻፍልኝ፣)

---

ስም፣ 1042፣ ዕድሜ 32፣ መኖሪያአዲስ አበባ፣ ሥራ ስፔር ፓርት ማኔጀር፣ ትምህርት MS.C. በአውቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግ፣ የቀይ ዳማ፣ ጃዝና ብሉስ ሙዚቃ፣ ካምፒንግ፣ ፊሺንግ እወዳለሁ። ለብዕር ጓደኝነት ሴት ወይም ወንድ መተዋወቅ እፈልጋለሁ፣ በተለይ በኔ ተመሳሳይ በሆነ ሙያ ላይ ያለ ሰው ባገኝ ደስ ይለኛል። (በ "ላንዳፍታ" አድራሻ በኩል ቁጥሬ ተጠቅሶ ይጻፍልኝ።)

---

አድራሻችን፣

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# ዶክተር ሣህለሥላሴ አርአያ
## የጥርስ ሐኪም
## COSMETIC AND GENERAL DENTISTRY
Sahle S. Araya, B.D.S., D.D.S.

የጥርስ እንክብካቤ ለጠቅላላ ቤተሰብ

የተሟላ ድርጅት

የድድ መቁሰል
የተቦረቦረ ጥርስ መድፈን
የተበላሸ ጥርስ መንቀል
የተሸረፈ ጥርስ መጠገን
ድድ ማጽዳት
ፍንጭት መግጠም
ጥርስ መጥረግ

CALL FOR APPOINTMENT
OPEN
Monday through Saturday
10:30 A.M. to 7:00 P.M.

6044 w. North Avenue
Chicago,Il 60639
(312) 237-8405

# Addisu Gebeya አዲሱ ገበያ
**We Carry Large Selection Of Ethiopian Foods & Spices**

***We have everthing you need to prepare an Ethiopian Feast !***

| DESCRIPTION | QTY(ib) | Price |
|---|---|---|
| 1. Berbere | 1/2 | 3.99 |
| 2. Miten Shiro | 1/2 | 3.50 |
| 3. Aja | 1/2 | 3.50 |
| 4. Mitmita | 1/2 | 3.50 |
| 5. Awaze | 1/2 | 3.99 |
| 6. Butter Maker | 1 | 13.99 |
| 7. Tef | 1 | |
| 8. Mekelesha | 1 | 13.50 |
| 9. Kik | 1 | 0.49 |
| 10. Bakela | 1 | 1.79 |
| 11. Miser | 1 | 0.89 |
| 12. Kinche | 1 | 0.39 |
| 13. Telba | 1 | 1.25 |

NAME ____________
ADDRESS ____________
____________
CITY ____________
STATE ________ ZIP ________
Tel. (   ) ____________

**WE DO MAIL ORDER**

Please Include $5.50 For Shipping And Make Your Check Or Money Order Payable To: Addisu Gebeya

- JEWELRY
- VIDEOS
- CASSETTES
- REKEBOTE (ረከቦት)
- COFFEE
- ETHIOPIAN ARTS
- ETHIOPIAN DRESS AND MUCH MORE

2202 18th St. N.W.,
Washington, DC 20009
202 •986 •6013 / 23

# « ልጅ የሌላት፣ መውለድ ግን የምትፈልግ . . .»

ከኤደን (ዋሺንግተን ዲ.ሲ)


"ትውውቅ፣ ፍቅር፣ ጋብቻ" በሚል ጓደኛ ለሚፈልጉ የተከፈተው አምድ አስደስቶኛል። ግን ያልገባኝና ምሬቱ ያንገሸገሸኝ ፍቅርን ለሚሹ እህቶቼ የተላለፈው የጓደኝነት መለኪያው አሳዛኝ ከመሆኑም ባሻገር እንኳን ለፍቅር መለኪያ ቦታ ሊገባ ቀርቶ ለአንድ ቀን ለአንድ ሰዓት አብሮ ለማሳለፍ ያስቸግራል። "ቆንጆ፣ ረጋ ያለች፣ አስተዋይ፣ ኑሮ አብራ መመሥረት የምትፈልግ፣ በጣም ያልቀጠነች፣ ለቤትዋ ለትዳርዋ የምታስብ፣ ልጅ የሌላት እንዲኖራት ግን የምትፈልግ፣ . . ."። የጓደኝነት መለኪያ እንግዲህ ይህ ከሆነ ያልገባኝ ብዙ ነገር አለ ማለት ነው። "ለልጅ ፍቅር የሌለው ነገር ግን እንድትወልድ የሚፈልግ" በተከታታይ ከወጡት ማስትወቂያያዎች በርከት ያሉትን ስመለከት ዋነኛ መለኪያው ይህ ነው። የሚያሳዝነኝ አባባል ወይም ባለመለኪያዎቹ እንዲመልሱልኝ የምፈልገው ልጅ ያላት ሴት ለትዳር ወይንም ለጓደኝነት ብቁ አይደለችም ማለት ነው? ልጅዋ የእሱን ፍቅርና ጊዜ ይሻማል በሚል ይሆን? ለዚህ መሰለኝ ጉብል የአገሬ ልጅ የወጥ ቅመማ ቅመም ይመስል ሲያማርጥ ጽጉሩ የተመለጠው። በኔ አስተሳሰበብ በእህቶቻችን መለኪያ ላይ "ልጅ የሌለው፣ እንዲኖረው ግን የሚፈልግ" የሚል መመዘኛ ያልተጠቀሰው ለእሱነቱ እንጂ ልጅ ቢኖረውም የእሱ አብራክ በመሆኑ የሁለታቸው ግኑኝነት ወይንም መተሳሰብ ፍቅር እንጂ ከእሱ የሚመጣ ልጅ መለኪያቸውን የሚሰብርባቸው ሆኖ ባለመገኘቱ ይመስለኛል። የአገሬ ወንዶች ምን ነካቸው? እስቲ እዩት፤ "ልጅ የሌላት እንዲኖራት ግን የምትፈልግ፤" ይህ እንግዲህ ለፍቅር መተዋወቂያ መሆኑ ቀርቶ የሥራ ማስታወቂያ ይመስላል። አምራች የሆነችው ተፈልጋ ስትገኝ ነገር ግን ልጅ ስላላት ብቻ ለምርጫው አትቀርብም ማለት ነው። ታዲያ ቁጥር ስፍር ያላቸው በልጅነታቸው በውዴታም ሆነ በግዴታ የወለዱ "ሀ" ብለው ሕይወትን ሲጀምሩ በ15 በ16 ዕድሜ መካከል በቤተሰቦቻቸው አስገዳጅነት ያገቡና የወለዱ እህቶች ለዚህ መለኪያ ብቁ አለመደረጋቸው አስገርሞኛል። ምንም እንኳን ግዴታ ባይሆን ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን ሰው የማግባት መብት ቢኖረውም የአገሬ ኮረዳ መብትና ሞራል በመጽሔት አውጆ መንካት ተገቢ አይደለም እላለሁ። እጅግ ብዙ የአገሬ ልጆች ስንት ልጅ በየቤተሰቦቻቸው ጫንቃ ጥለው የሕይወትን ትርጉም ለመቅመስ ቢሰደዱም ዛሬ በዚህ አምድ የሚተዋወቁትን ጉብል እስከ ሕይወታቸው ግማሽ ደብቀው መኖር አይችሉም። ታዲያ መዛኞች ምን ይመስላችኋል?

---

# በወንዶች ላይ ያለኝን ጥላቻ እንዴት አጠፋው ይሆን?

ከእህታለም (ናዝሬት)
(ስሜን አታውጡ ስላለች እኛ የሰጠናት የብዕር ስም ነው)

በቅድሚያ እኔነቴን ላስታዋውቃችሁ። ዕድሜዬ 17 ሲሆን የ11ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። ቁመቴ ረዘም ይላል፤ መልኬም የቀይ ዳማ ነው። በተፈጥሮዬ የምወደው የድርሰት ሙያ ሲሆን ከሁሉ በላይ የምጠላው ወንዶችን መቅረብ ነው። መቼም ባህርዬ ትንሽ ግር ሳይላችሁ አልቀረም። ብዙ ጊዜ ሊጠይቁኝ የሚመጡትን ወንዶች ይኸው የመሸሽ ባህርዬ ሳያስደነግጣቸው አይቀርም። በወንዶች ላይ በአዕምሮዬ የፈጠርኩት ግምት አለኝ። ከትንሽ እስከ ትልቅ ወንዶች ሲባሉ ትዕቢተኞች፣ ጉረኞችና ዋሾዎች ይመስሉኛል። ወንዶችን በጣም እፈራለሁ፣ እጠላለሁ። ሰው መቼም የልቡን ከተናገረ መማማር እንጂ ሌላ ችግር አያመጣም ብዬ ስለማምን እስቲ ወንዶችን እንድጠላ ካደረጉኝ አንደኛውን ምክንያቴን ላጫውታችሁ። በአንዲት ጓደኛዬ የደረሰ አሳዛኝ ታሪክ ነው። ጓደኛዬ በተፈጥሮዋ ሳቂታና ተጫዋች ስለሆነች የሚቀርቧት ወንዶች ሁሉ ሃሳቧን ሳይረዱላት የእህትነት ፍቅርዋን ገሸሽ ያደርጉባትና "አበድንልሽ" ይሏታል። ሁሉን እንዳመጣጣቸው ትመልሳቸውና በመጨረሻ ግን ለአንዱ ትንበረከካለች። ጣፋጭ ቃላት እየሰነዘረ እጁ አስገባት። በፍቅሩም ይሉኝታን ጥላ በመክነፏ በዚሁ ልጅ ሳቢያ የቤተ ሰቦቿን ሆድ እንኳ ሳይቀር ታሻክራለች። ዳሩ ምን ያደርጋል እንደ አጀማመሩ አልሆን ይልና ልጅቷ መጸነሷን ሲያውቅ አጅሬ አላውቅሽም ይላታል። ጓደኛዬ እንግዲህ የሆነችው ይታያችሁ። በሱ ምክንያት ከቤተሰብ መቀያሟ ሳያንሳት የእሱ መደገም እብድ አደረጋት። ይህን ሁኔታ በመለማመጥ ልታግባባውም ብትሞክር ጭራሽ የውጭ አገር ዕድል አግኝቶ ሊሄድ መዘጋጀቱን ትሰማለች። በዚህ ብስጭት በድብቅ መድሃኒት ትጠጣና ይህችን ዓለም ትሰናበታታለች። "ፍቅር እውር . . ." ይባል የለ? የቅርብ ጓደኛዋ መካሪዋ እኔ እህቷ ያልኳትን ሳትሰማኝ ቀረችና ይኸው ገና በእንጭጩ ተቀጨች። አጅሬም ውጭ አገሩ ሄደ። እኔም ጓደኛዬን በእንባ ሸኝቼ በወንዶች ላይ ጥላቻን አረገዝኩ። እስቲ ምክር ብጤ ስጡኝ፤ ወይ ልክ ነሽ በርቺ በሉኝ፤ አለበለዚያም የሚበጀኝን ምከሩኝ። በዚህ ሁኔታዬ ወንድ የማላይበት ቦታ መፈለጌ ነው።


ኑሮ
በአሜሪካ



# እየተስተዋለ እንጂ . . .

ከገረሱ

እንድ ሰው ታዳጊ ከሆነ አገር የቴክኖሎጂ ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ ከደረሰበት ቦታ ሲመጣ ግር ይለዋል። ያለመደው፣ ያልገመተው ነገር ሁሉ ያጋጥመዋል። ብልህ ከሆነ ቀስ በቀስ እየተላመደው ይመጣል። ችኩል ከሆነ "ችኩል ጅብ . . ." እንደሚባለው ያልሆነ ነገር ላይ ሊወድቅ ይችላል። በቴክኖሎጂ ተስፋፋ ሲባል ሁሉ ነገር ጥሩ፤ ሁሉ ነገር ትክክል ነው ማለት አይደለም። ዛሬ ወንጀሉ፣ ተንኮሉ ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ ተንሰራፍቶበት የሚገኘው ቦታ ይኸው በቴኬኖሎጂ ዕድገቱ የምናደንቀው ቦታ ነው።

ይህንን እንደመግቢያ አድርጌ ላነሳው የተነሳሁበት ምክንያት ስላለኝ ነው። ውድ አገራቸውን ጥለው በተለያዩ ምክንያቶች ዛሬ በአሜሪካንና በአውሮፓ ፈሰው የሚገኙ ያገራችን ልጆች በያሉበት ቦታ አገሬውን መስለው፤ ወጥተው ገብተው፣ ጥረው ግረው ሲኖሩ ችግር እንደሌለባቸው አድርጐ መውሰዱ ትክክል አለመሆኑን ለመጠቆምም ጭምር ነው። ያልለመዱት ቦታ ምን ያህል እንደሚያስፈራ የኖረው ያውቀዋል። በስደት ዓለም መኖር ምን ያህል ችግር እንዳለበት ማወቁ ተገቢ ነው። በተለይ ደግሞ የአሜሪካን አገር ኑሮ ሲኒማ አምባሰደር እንደሚታዩት ፊልሞች ያማረው ሁሉ በቀላሉ ማንም የሚያገኛቸው አይደሉም። እዚህ የመጣነው አንዳንዶቻች አሜሪካንን ልክ ኢትዮጵያ እያለን በፊልም ያየነውን እንደምናገኝ ወይም እንደምንሆን ቆጥረን እንደሆነ ልቦናችን ያውቀዋል። እዚህም ስንደርስ ውጣ ውረዱ፣ ሥራ ፈልጐ ማግኘቱ፣ ብዙዎቻችን የምንመኘውን ትምህርት ቤት ፈልጐ መግባቱ፤ ወዘተ በጠቅላላው እንዳለምነው ቀላል ሆኖ አላገኘውም። ይህ ስንቶቹን እያበሳጨ በሽታ ላይ እስከመጣል እንደደረሰ የሚያውቀው ያውቀዋል። ይህንን ስል በችግር ምክንያት መጠለያ የሆነኝን አሜሪካንን ለመውቀስ እንዳልሆነ አንባቢያን እንድትረዱልኝ እሻለሁ። በስደተኝነት ተቀብላኝ፣ ሕይወቴን አትርፌ እንድኖር ዕድል ስለሰጠችኝ ባለውለታዬ ናት።

እኔን የሚያናድደኝ የአሜሪካንን ኑሮ፣ በተለይም የስደተኝነትን ኑሮ እንዳንዳ ትልቅ የደስታና የትፍስህት ኑሮ በማድረግ "አሜሪካን የመጣ የታደለ . . ." ተብሎ ሲወራና አንዳንድ ያገራችን ጋዜጣዎችና መጽሔቶች ይህንኑ ሲያስተጋቡ ነው።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አገር ቤት በሚወጡአንዳንድ ጋዜጦች ላይ "ሀምበርገር እየበሉ . . . እየዘነጡ አይደለም ስላገር የሚታሰበው . . "

የሚሉ አባባሎች ቀደም ሲል በደርግ ጊዜ እንደነበረው ሁሉ አሁንም ሲሰነዘሩ እሰማለሁ፤ አይቻለሁም። ትክክለኛውን ሐቅ ወይ ካለመረዳት አለያም ሐቁን በመረዳት ሁን ተብሎ በመሸፈን ለሌላ ዓላማ የተሰነዘሩ እንደሆኑ መጠቆም እወዳለሁ። መቼስ ዛሬ በባዕድ አገር ፈሰሶ የሚገኘው ወገን ለዚህ ምን እንዳደረሰው የማይገነዘብ ሕሊና የለም እንልም።

ያ እንዲህ እንደ ትልቅ ነገር ተቆጥሮ ለፖለቲካ ቅስቀሳ እንኳ ሳይቀር የሚውለው "ሀምበርገርም" ቢሆን በቀላሉ እንደማይገኝ መረዳት ብዙ ዕውቀት የሚጠይቅ አይመስለኝም። አንድ ሀምበርገር ከአንድ ለስላሳ ጋር ለመግዛት እስከ $5.00 ብር ወጪ ይጠይቃል። ያችን አምስት ብር ደግሞ ለማግኘት ተሯሩጦ መሥራት ያስፈልጋል። ሥራውን ማግኘቱም ራሱ ሌላ ከፍተኛ ውጣ ውረድ አለው። ታዲያ ይህን ያነሳሁት በሰው አገር የስደት ኑሮ እንዲህ ቀላል አይደለም ለማለት ነው።

ዛሬ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስለ አገራቸው ሰላምና ብልጽግና በየሚያገኙበት መድረክ ሲያወሩ እነኚህ ጋዜጦች እንደሚሉት "ሀምበርገር" በልተው ጠግበው አይደለም። የሚበሉት "ሀምበርገር" ስላልተስማማቸው የሚስማማቸውን እንጀራ የሚበሉበት ውድ አገራቸው ሰላም ሆና እነሱ ወደዛ ተመልሰው የትም ባዕድ አገር ፈስሶ የቀረውን ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን ለብልጽግናዋ ለማበርከት ከመጓጓት ነው። አገር የበለጠ የሚናፈቀው ወጣ ብለው ሲያዩት ነው። ፈረንጆችም "Nothing like home!. . ." "ማ እንደ አገር" ብለውታል።

ታዲያ ጉበዝ ምን ነካን? ይልቅስ ይህንን እንደጨው ዘር ተበትኖ ለባዕድ አገር ብልጽግና የሚባክነውን የአገር ልጅ ዕውቀትና ጉልበት ወደ አገር እንዲመለስ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠሩ አይሻልም የሚበጀው። "ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው፤" ይላል የአገሬ ሰው። በስደት ዓለም አገሩ እየናፈቀው በምሬት ያለውን ወገናችንን በሆነው ባልሆነው ባናቆሳስለው ምናለ? የቆሰለው አይበቃውም እንዴ?

እየተስተዋለ እንጂ!

# « የኛ ልጆችና የባህር ማዶ ስማቸው »

ከግርም ዘገየ ይግለጡ
ካለፈው እትም የቀጠለ

ባለፈው እትም ላይ ያቀረብኩትን አስተያየት ለማጠቃለል እሞክራለሁ። በቀደምት ጽሑፌ መግቢያ ላይ ለመግለጽ እንደመሞከርኩት የኔ አስተያየት በሕፃንነትና በቤት ስማቸው የሚጠሩትን በተለይም ለማሞካሸትና ለማሞገስ ከሚሰጡ ስሞች ጋር ጠብ እንደሌለኝና ብዕሬንም በዚሃ ላይ እንዳላነሳሁ ይታወቅልኝ። የኔ አስተያየት የሚያተኩረው ባህር ሲሻገሩ ስለሚሰጡ ስያሜዎች ነው።

እስቲ አንድ ምሳሌ ላቅርብ። ገረመው ሲባል የከረመ ያገር ልጅ በዚህኛው ዓለም "ጌሪ" ሆኖ ብታገኙት ምን ትላላችሁ? ወይም የበለጠ "ቢሊ" መባል ምን ፍለጋ ይመስላችኋል? በማሞካሸት ደረጃ የሁለቱ ስም ከ"ገሬ"ና ከ"በሌ" አያልፍም። "ጌሪ"ና "ቢሊ" ግን ፈረንጅነት ፍለጋ ወይም ለመመሳሰለል ሲባል የተሰጠ ስያሜ መሆኑን ትረዳላችሁ።

ይህን እንዲያው ለምሰሳሌ ያህል አቀረብኩ እንጂ አያሌ ያገር ልጆች የሀገርኛውን ስማቸውን አሜሪካ ከገቡበት ፓስፖርት ጋራ አጥፈው እንዳስቀመጡት አትጠራጠሩ። ኸረእንዲያውም በቅርቡ አቶ ዮርዳኖስ በመባል የሚታወቁ ያገር አዛውንት በቀጥተኛው የስማቸው ትርጉም "ሚስተር ጆርዳን" መባላቸውን በአደባባይ ስሰማ የትዝብት ሳቅ ያዘኝ።

እስቲ አንድ አስተያየት ላቅርብ። በቆምንባት አሜሪካ ምድር ላይ ከመላው ዓለም የተሰባሰቡና የተለያየ ዘርና ሀይማኖት፣ የተለያየ ባህልና ቋንቋ ያላቸው ሕዝቦች በጋራ ይኖራሉ። አብዛኞቹ የዜግነት መብት አግኝተው ለረጅም ዘመን በዚች አገር ኖረዋል። ግን ስማቸውን ልብ ብላችሁ ተመልክታቸችኋል። ለማገናዘብ እንዲረዳ ከጃፓን፣ ከሜክሲኮ፣ ከቻይና የመጡትን ብቻ ተመልከቱ። በተለይ የሩቅ ምሥራቅ ሕዝቦች ስም ለአጠራር አስቸጋሪ ከመሆኑ ሌላ ለማሳቅም ይከጅላል። የሜክሲካኖችም ስም በተለምዶ ጠጣርና ጠንካራ ነው። የራሺያኖቹ ደግሞ ረዥምና በአጠራር ጊዜ ፊደል ላለመዝለል መጠንቀቅን ይጠይቃል። ለምስሌ ያህል ለመጥቀስ ከቻይና "ኩዋሽ ኪ ሚያው"፤ ከራሺያ "ኮዞልኪኖብስኪያን"፤ ከሜክሲኮ "ሮድሪጉ ጉንዛለስ" የሚሉ ይገኝባቸዋል።

እነዚህን መሰል ስሞች ስትመለከቱ የስሞቹ ባለቤት ሲኮሩበትና አንድም ለውጥ ሳያደርጉ እንደሚጠሩበት ከመስማታችሁ ባሻገር በዚሁ አገር ለሚፈጠረው ልጃቸው የሚሰጡት ስም ላይ ከራሳቸው አገር የስም አወጣጥና ባህል ውጭ ቅንጣት ባዕድ ስም አይጨምሩም። ለምስክርነት ያህል በስሙ አስቸጋሪነት ምክንያት ሌላ የቅጽል ስም የተሰጠው ቻይናዊ "ባትፈልጉ አትጥሩኝ እንጂ ስሜን መቀየር አትችሉም፤" በሚል አምባጓሮ ሲፈጥር ተመልክቻለሁ። በራስ ኩራት ይሏል ከዚህ ነው የሚጀምረው። እስቲ ሌላ ምሳሌ ላቅርብ። አሜሪካንን ለመገንባትና እዚህ ደረጃ ለማድረስ ከፍተኛ የጉልበት አስተዋጽዖ ካደረጉት ውስጥ የጥቁር አሜሪካውያን ድርሻ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። እነዚህ ሕዝቦች ከ"ጨለማው" የአፍሪካ ዓለም በባርነት የተወሰዱ በመሆናቸው ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ የወንዝ ስማቸው ተፍቆ በምትኩ የገዥዎቻቸውን ፍላጐት የሚተካ ስም እንዲይዙ በመደረጋቸው የሁሉም ጥቁሮች ስም ከነጩ ጋር ተነሳሳይ ነው። ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲተካና የራስን ታሪክ መመርመር ሲጀመር ባሁኑ ሰዓት ለሚወለዱ ጥቁሮቸች የሚሰጡ ስሞችን ተመልክታችሁ እንደሆን በአብዛኛው አፍሪካዊ የሆነ ነው። ለምሳሌ ያህል "ነታሻ"፤ "ዴንሳ"፤ "ሸኒኳ"፤ ሌሎችም የሚጠቀሱ ብዙ አሉ። እንግዲህ ራስን ማወቅ ማለት ይህ መሰለኝ። ወይም ማንነትን መረዳትና ወደራስነት መመለስ አዋቂነት መሆኑን መገንዘብ ትልቅ ነገር እንደሆነ ማወቅ ተገቢነቱን የተረዱ ይመስለኛል።

ይልቅስ ከስሙ ይልቅ ሥልጣኔአቸውን መቀበልና የራስ ማድረግ ራስን ከመጥቀሙ ሌላ ነገ ለወገንም ትልቅ አለኝታ በመሆኑእስቲ ራሳችንን እንምሰል። "ራስን መጥላት የሚጀመረው ከዚህ ነው፤ ራስን አለመሆን ደግሞ ጤነኛ አለመሆንን ከማመልከቱ ሌላ፤ ሌላውን ለማምለክ ራስን ማስገደድ ነው፤" የሚለውን የሊቃውንት አባባል ያስታውሰናል።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የምለው የለኝም። ጽሑፌን ከማጠቃለሌ በፊት ግን ያበሻ ፈረንጆችን መሰናበት ስላለብኝ፤ "bye ቢሊ፣ bye ጌሪ፤ bye ጆርዳን" ማለቱ ተገቢ መሰለኝ።

---

# ስለ ምግብ አወሳሰዳችን ጥቂት!

አሜሪካ አገር መቼም የምግብ ችግር የለም። ገንዘቡ ከተገኘ ማለታችን ነው። ከመኪና ሳይወጡ በመስኮት በኩል ላጥ ብሎ የሚፈለገውን እዞ እየበሉ መንጐድ ነው። ታዲያ የምግቡ በተለይም የ"ፋስት ፉድ" ነገር ከተነሳ ብዙ የሚያወያየን ነገር ይኖራል።
እስቲ በዚች ግጥም እንጀምር።

የበርገር ኪንግ ዋፐር ፍራይስ ጋር ሆኖ፣
ወይም ዌንዲስ ሄዶ ከሳላድ ባር ዘግኖ።
    አለያም ቢግ ማክን ከማክዶናልድ በልቶ፣
    አንድ ቢጊ ኮካ በላዩ ጠጥቶ።
ሥጋ ሰልቸት ሲልም
    ኬንተኪ ፍራይድ ቺክን ይበላና፤
    ሲያገሱ መዋል ነው ሥራው ከተቃና።
በፋስት ፉድ ጋጋታ ኮሌስትሮል በዝቶ፤
ሰውነትም ከብዶ ፓውንድም ጨምሮ፤
ልቤን ሊያቆመው ነው የዚህ አገር ኑሮ።

እነኚህ ከላይ የተጠቀሱት የ"ፋስት ፉድ" ሰንሰለቶች ድፍን አሜሪካንን አንዳንዱ ለምሳሌ ማክዶናልድ ከአሜሪካም ውጭ በሰፊው የተዘረጉ በመሆናቸው በሥራ ምክንያትም ሆነ በሌላ ጉዳይ ሲርበን በአስቸኳይ የምንበላውን የምናገኝባቸው ቦታዎች ናቸው። "ፋስት" መባላቸውም ለዚሁ መሰለኝ። በዚህ ላይ ወደድ ይላሉ። የዛሬው ጽሑፋችን ስለነኚህ ድርጅቶች ማስታወቂያ ለማውጣትና ስለነሱም በሰፊው ለመናገር ሳይሆን እነሱን መሠረት አድርገን ስለአመጋገባችን ጥቂት ለመወያየት ነው።

እንደምንረዳው ይህ ዓይነቱ ቋሚ ምግባችን ሊሆን አይገባም እንላለን። ብዙ ምክንያቶች ልንደረድር እንችላለን። በመጀመሪያ ደረጃ የምግቡ አዘገጃጀት የይድረስ የይድረስ ነው። ምግቡ የሚዘጋጅበት ሥጋ በኬሚካል ተላቁጦ (preserve) የተቀመጠ በመሆኑ ተፈጥሮአዊነቱን በጣም ቀንሷል። በነኚህ የማቆያ ንጥረነገሮች (ኬሚካሎች) ሳቢያ ታዲያ የተለያዩ በሽታዎች ሊመጡ እንደሚችሉ ብዙ የሕክምና ሊቃውንት ደጋግመው አስጠንቅቀዋል። ስለ ዶሮዎቹ የሚወራውማ ሌላ ነው። ከዚህ በተረፈ ለገበያ ሲባል ምግቡ ሱስ እንዲያሳድር ተደርጐ ነው የሚዘጋጀው የሚል ሐሜት በሰፊው ይሰፍናል። አንዱ ኢትዮጵያዊ ለሶስት ዓመት ሙሉ "ቢግ ማክ"ን ለምስው እንደወሰደና ይህም ከፍተኛ ሱስ እንድሳደረበትና ሰዓቱ ሲደርስ ካላገኘው ጭንቅ ጭንቅ እንደሚለው አጫውቶናል። እንግዲህ ሱስ እንዲያሳድር የሚያደርግ ሌላ የሚገባበት ነገር አለው ማለት ነው። ስለዚህ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባን መረዳት ያለብን ይመስለናል። እስቲ የጤና ባለሙያዎች ተጨማሪ አስተያየት ስጡን። የአመጋገባችንን ባህል እንዴት አገሩ ከሚያፈራው ጋራ እንደምናዋህደው ጨንቆናል።

---

## ውድ አንባብያን፤

"ኑሮ በአሜሪካ" በተሰኘው አምዳችን በአሜሪካን አገር ኑሮአችን ስለሚገጥሙን ችግሮች ተወያይተን የምንመካከርበትን መድረክ ፈጥረናል። ባለፍው እትማችን እንደጠየቅነው ሁሉ በሚከተሉት ታላላቅ ርዕሶች ላይ ልምዳችሁን፣ በሙያው የሰለጠናችሁ ዕውቀታችሁን እንድታካፍሉን እንጠይቃለን። ግራ ገብቶአቸው የተቀመጡትን አንዳንድ ወገኖቻችንን ሊረዱ የሚችሉ ምክሮችን ላኩልን። እንረዳዳ።

፩ኛ. የትምህርት መቀጠል ጉዳይ፤ ለምሳሌ የትምህርት ዓይነት አመራረጥ፣

፪ኛ. የሥራ ማግኘት ጉዳይ፤ ለምሳሌ አፈላለግ፣ ኢንተርቪው አቀማመጥ፣

፫ኛ. የራስን ንግድ ወይም "ቢዝነስ" የመጀመር ጉዳይ፤ ለምሳሌ ፈቃድ የማግኘት፣

፬ኛ. የጤና ጉድይ፤ ለምሳሌ አመጋገብ፣ ስለ ኤይድስ




# የአበው ቅርስ




ይህ አምድ በአማርኛ የተደረሱ ቅኔዎችን፣ ተረትና ምሳሌዎቻችን፤ ፈሊጦችን፤ የዘፈን ግጥሞችን፣ እንቆቅልሾችን፣ እንካ ሰላንቲያዎችንና የመሳሰሉትን፣ በተለይም ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን የወረስናቸውን፣ እንዳይረሱ የምንዘግብበት፣ የተረሱትን እንድናስታውሳቸው የሚረዳን መድረክ ነው። አንባብያን በየመዘከራችሁ ያከማቻችሁዋቸውን ቅርሶች በመላክ እንድትተባበሩን እንጠይቃለን። ከአገር ርቀን ላለን ባህላችንን ጠብቀን የምናስከብርበት፣ አባት እናቶቻችንን፣ ውድ አገራችንን የምናስታውስበት፤ የቋንቋችንን ምጥቀት እየተረዳን የምንኮራበት ነውና። ቀደም ላሉት እትሞች፣ ለዚህኛውም አስተዋጽዖ ያደረጋችሁትን ከልብ እናመሰግናለን።

---

## ተረትና ምሳሌዎች

እስቲ እነኚህን ተረትና ምሳሌዎች ተወያዩባቸው። ይህን የላኩልንን አቶ ኃይለማርያም ከበደ (ከጂማ) እናመሰግናለን።

1. ሳይጠሩት የመሠከረ ባጎት የሰከረ።
2. ሎሚ ካልበሉት እንቧይ ነው።
3. መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳታይ የሰው ትጠቅማለች።
4. በል በል ይላሉ ሲፈርዱ፤
   ጣል ጣል ይላሉ ሲያርዱ።
5. ወግ አይቀርም ብሎ ይሸታል እንኩሮ።
6. ለፍቅር ብቀርባት ለጠብ አረገዘች።
7. ገበያው ሳይቆም ለማኙ ለቀም።
8. ዕዳ ሲገቡ ዓይን ይጨልማል።
9. ስትወልድ የምትበላውን በእርግዝናዋ ጨረሰችው።
10. በቅሎና ሲኒ ሆዳቸው አይይዝም።

## ከአማርኛ ቅኔዎች

የሚከተሉትን ቅኔዎች የላኩልን አሁን አቶ ኃይለ ማርያም ከበደ (ከጂማ) ናቸው።

፩ኛ.
እንጀራው አይጥምም እርሾ ታልመጠኑ፣
ማጉብጉብ ካልቻሉ ቧለሟል አይሆኑ።

፪ኛ.
ጠጅ ልኬልሻለሁ ውስኪ ላኪልኝ፤
ጠላ ቀረ ብለሽ አትቀየሚኝ።

፫ኛ.
እኖራለሁ እኔ እንዳስቀመጡኝ፣
መንቀሳቀስ አልችል መች እራስ አለኝ።

፬ኛ.
ላረቄውም ኮራሽ፤ ለውስኪውም ኮራሽ
እንቺ ግዴለሽም፤
የወደድሽው ጠላ አልተገኘልሽም።

---

## ታ ላ ላ ቅ  ጥ ቅ ሶ ች

"ሌሎችን ድል የሚያደርግ በእርግጥ ጉበዝ ነው። በራሱ ላይ ድልን የሚቀዳጅ ግን ከማንም ይልቃል።"

"ታላቅ ሰው በሶስት ምልክቶች ይታወቃል። ደግነትን መሠረት አድርጐ ነገሮችን በመወጠን፤ ሰብዓዊ በሆነ መንገድ የወጠነውን በመፈጸም፤ በመጨረሻም በድሉ ባለመኩራራት።

---

## ለቆለኛዋ!

## ለአደገኛዋ!

አንድም ብዬ ዜሮ ዜሮም ብዬ ሁለት፤
ደውዬ አገኘሁሽ የተመረቅሁኝ ለት።
ለምለም ላይ የበቀልሽ እሸት ነሽ ብዬሽ፤
እንደ ዓይኔም ብሌን ልንከባከብሽ፤
ቆላ ድረስ መጣሁ አግኝቼ ላይሽ።
የዛን ዕለት ታዲያ ቀኑ ጠለመና፣
በረዶው ነፋሱ ቤት ዘጋብንና።
እኔ መች አወቅሁት መረግሜን ከቶ፤
ያሰብኩት ያሰብሽው አለቀኑ ሞቶ።
በዓይኔ ያየሁትን ብናገር ማ ያምናል?
አወቅሁት ያሉት ሰው ለካ ሰው ይጐዳል።
ከሰው አማኙ

## የእናት ውለታዋ፤

ከሊሊ ሙሉጌታ (ቺካጐ)

ዘጠኝ ወር አርግዘሽ፤
ጡትሽን አጥብተሽ፤
እንቅልፍሽን አጥተሽ፤
ሌት ተቀን ተቀምጠሽ፤
በትምህርት አንጸሽ።
እኔን ለማሳደግ የምትለፊልኝ፣
እምዬ አንቺ እኮ ነሽ።
ንፋስም ሲነካኝ ትንሽ ሲበርደኝ፤
እንደትኩሳትም ሕመም ሲሰማኝ፣
ትንሽ ለወጥ ብዬ ድንገት ስታይኝ፤
እምዬ ጭንቀትሽ አሁን ትዝ አለኝ።
እምዬ የኔ ሆድ አለኝታዬ ነሽ፤
ሃሳብሽ ሞሎቶልሽ ዶክተር ሆኜልሽ፤
ጤናና ዕድሜ ሰጥቶ አምላክ ያሳይሽ።

---

# የዘፈን ግጥሞች

ዳዊት አስፋው ከኦክላንድ ልከወውልን ካለፈው የቀረውን በመጀመሪያ እናቅርበው።

እሷ፤
ያላደላው ፈረስ ጋሪ ይጐትታል፤
እንዳንተ ዓይነቱም ብዙ አህያ ሞልቷል።

እሱ፤
ጋቢና ከወሎ፤ ዲፈሬንሲያል ከሐረር፤
ሞተር ከሰላሌ፣ ማርሹ ከወለጋ
ሾፌሩ ከትግራይ ረዳቱ ከጐንደር፤
አንቴና ከጐጃም፤
ያንን አሰባስቦ አምቼ ማስገጠም።
ምነው ባደረገኝ መካኒክሽን፣
ፈትቼ እንዳይልሽ ብሮንዚናሽን።

እሷ፤
ይጠየቅ አንቦላው እኔ አልገፋሁትም፤
ይጠየቅ ፍራሹ እኔ አልገፋሁትም፤
ብርድልብስ አግኝተህ ለበስክ አሉኝ የትም።
ሽሞንሟና ጋቢ አሰርቼልህ፤
የማንም ዲሪቶ ትጐትታለህ።

እሱ፤
አንተ አልጋ ተናገር ስንት ሰው ተኛብህ፣
ፍራሹ ተናገር ስንት ሰው ተኛብህ፤
አንሶላው ተናገር ስንት ሰው ተኛብህ፤
ባትናገር እንኳ መቀደድ አለብህ።

እሷ፤
አንድ አልጋ ተኝተን ታማኛለህ አሉ፤
አብሬህ ተኝቼ ታማኛለህ አሉ፤
ስጪኝ አትልም ወይ ያሰኘህን ሁሉ።

እሱ፤
ምን ዓይነት ክፉ ነሽ ጨካኝ ነሽ ያሉሽ፣
ያለሽን በሙሉ ገልብጠሽ ሰጥተሽ።
እንኳን በሳሙና ብታጥቢው በንዶድ፤
አሠጣጥ እኮ ነው ሰው የሚያስወድድ።

==============================

የሁሌ ተሳታፊያችን ወንድ ወሰን ይመር ከቺካጐ የላኩልንን ደግሞ እናቅርብ።

እንጀራው ወልዲያ እየተጋገረ፤
ወጡ ጉባ ላፍቶ ይሸተኝ ጀመረ።
ተይኝ አላልኩመም ወይ ተኳኩሎ ሜዳ፣
ዓይን ወረተኛ ነው ያመጣል እንግዳ።
ከኮምቦልቻ በታቸች ፍቅር መስርቻለሁ፤
ቢመሽም ግዴለም ወረባቦ አድራለሁ።
ይመራል ይላሉ ኮሶ መጠጣት፣
እሱስ የሚመረው ወዶ መለየት።
ከወረይሉ በላይ ስሙ ነው ነዳድ፤
በሳሙና ቢያጥቡት አይለቅም መውደድ።
ተማምለን ነበር እንዳናቀላፋ፤
ተኝተሽ ተገኘሽ የሚያምኑት ሰው ጠፋ።

==============================

# « በኪነት ስም ዘረፋ »

ከነዘነበ (ቺካጐ)

April ሁለትና ሶስት 1993 በቺካጐ ከተማ በኢትዮጵያ ኺሌጅ ሬስቶራንት የሚሠራዉ ክራር ተጫዋችና ከዋሽንግተን ዲሲ የመጣዉ የራስ ቲያትሩ መሰንቆ መቺ የአገር ባህል ሙዚቃ ምሽት አዘጋጅተዉ ነበር። እኛም በቦታዉ የተገኘነዉ የአገር ባሕል መሳሪያዎቻችን ስለናፈቁንና ለመደሰትም ነበር።አርብ እለት ሁለቱንም በአገር ባሕል ልብስ አሽብርቀዋል። መሳሪያቻዉን ጠምዘዝ አርገዉ ጨዋታቸዉን ቀጠሉ። ለብዙ ጊዜ አብረዉ የሰሩ ይመስላሉ። ሙዚቃዉም ቀስ በቀስ እየፈጠነ ሄዶ ወደ ጭፈራ አመራ፤ ደስ የሚል ምሽት አለፈ፤ ዉነትም እኩሪ ባሕል አለን። በማግስቱ ትንሺ ለየት ያለ ነበር፤ ክራር መቺዉ ተገቢዉን የሐገር ባሕል ሲለብስ፣ ባለመሰንቆዉ ኮትና ሱሪ ከነ ክራባቱ አጥልቆአል። ያም ሆነ ይህ ጨዋታዉ እንደተለመደዉ በደመቀ ሁኔታ ተካሂዶ ሳይታሰብ ነጋ። ይበል ይበል ያሰኛል። በሚቀጥለው ቀን ከባለክራሩ ጋር ተገናኝተን ስንጫወት በአለፉት ምሺቶች ሙዚቃ ሲደሰት፣ በባለ መሰንቆዉ ቅር መሰኙቱን ነገረን። እኛም ከታዛቢ የተረዳነዉና ያየነዉ ቢኖር እንደሚከተለዉ ነዉ። ባለክራር መሰንቆ መቺዉን የሚገኘዉን ጥቅም ሊካፈሉ በስልክ ተዋዉለዉ ቺካጐ ያመጣዋል። ባለመሰንቆም የጓደኛዉን የድካም ዋጋ አሻፈረኝ አላካፈልም በማለት እሳፊ ንግግርም ተናግሮ ወደ ዲ ሲ መመለሱን ተረዳን።

እዚህ ላይ ሳንጠቁም የማናልፈዉ ነገር አለ። ብዙዎቹ የመዝናኛ ሥራዎች የሚሰሩት በአሠሪና በሙዚቀኞች መግባባት የሚሠራ እንጅ ሕጋዊነት የላቸዉም መሰለን። ባለምግቤቶቹ የሥራ መስክ በመክፈታቸዉ ሙዚቀኞቹም ህብረተሠቡን በማዝናናታቸዉ ሊመሠገኑ ሲገባቸዉ ፣ባንፃሩ እንደዚህ አይነት የዉንብድና ተግባር የሚያካሂዱ እንደነሻምበል በላይነህ ዓይነት የኪነት ባለሙያዎች ሊወቀሱ ይገባቸዋል። ከአገራችን ሙዚቀኞች የዋጋ መናር ባሻገር የሚከናወኑ ዉስልትናዎች ከአሁኑ ካልተቀጩ ስር እየሰደዱ ሄደዉ ዉስብስብ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። ስለሆነም መላዉ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ትኩረት ቢያደርጉበት መልካም ነዉ እንላለን። ተበዳዩ መሥፍን አለሙም እንዲህ አለን። "በግዜ አለመሣካት አሠርተዉ ያልኪፈሉኝ አሠርቼም ያልኪፈልኳቸዉ ይኖራሉ። ይህ "እዳም ይከፈላል እየሠነበቱ" እንደሚለዉ አይነት ጨዋታ ሲሆን ተራ ነጠቃ ግን ከአንድ የኪነት ባለሙያ የሚጠበቅ አይደለም፤ ድርጊቱ ለኔ ድርሰቴን አዳብሮልኛል። ምክንያቱም ብዙ ተምሬበታለሁና።"

---

# ዘፋኞቻችን ምነው ዋጋቸው ናረ?

ከአትናትዮስ (ሚኒሶታ)

በአሚሪካ አገር የሚገኙ የአገራችንን ሙዚቀኞች አገራችን እንዳይናፍቀን ዜማዎቻችንን እዚህ ድረስ በማምጣት ያደረጉልንን አስተዋጽዖ በቀላል የምናየው አይደለም። ይመስገነው ዛሬ እንደድሮው በቴፕ ብቻ ሳይሆን በሕይወት እያየናቸው ዜማዎቻቸውን እንሰማለን። ግን በጣም ውድ ዋጋ ከፍለን ነው ታዲያ።

ይህ እንዴት እንዲህ ሊወደድ ቻለ ብለን በየስቴቱ የሙዚቃ ዝግጅት የሚያቀነባብሩትን ስንጠይቅ ለዘፋኙ የከፈልነው እኮ ይህን ያህል ሺህ ብር ነው ይሉናል። ኸረ ለመሆኑ አንድ ዘፋኝ ለመጋበዝ ስንት እንደሚጠይቅ ታውቃላችሁ? በሕግ የተወሰነ ይመስል "እከሌ የሚከፈለው ይኸ፣ እከሌ የሚከፈለው ይኼ ." ትባላላችሁ። ማን ወሰነው? ምንን መሠረት አድርጐ ነው የተወሰነው? እኔ አላውቅም።

አላምንም ብዬ አንድ ሁለቱን ስልክ ደውዬ ብጠይቅ አንደኛው (ስሙን አላነሳም) "ለኔ $1,500፣ በተጨማሪ መሣፈሪያዬንና የደምበኛ ሆቴል ወጪ፤ ደግሞ የምግቤን፤ ለመሣሪያ ተጫዋቾች ደግሞ ለያንዳንዳቸው $500 ትራንስፖርትና ሆቴላቸውን ችለህ" አለኝ። ባሰላው ዝግጅቱን እኔ ያለሁበት ቦታ ለማድረግ 200 ሰው እንኳ ቢመጣልኝ ወጪዬን ለመሸፈን የመግቢያ ዋጋ ቢያንስ $25 ብር መጠየቅ ሊኖርብኝ ነው። እዚህ አገር በጣም ውድ የተባሉት ኮንሰርቶች ከ$18 እስከ $20 ብር ነው መግቢያቸው። የኛ ግን ለየት ያለ ነው። ምነው ጉበዝ ብንተዛዘን። በዚሁ አጋጣሚ "ላንዳፍታ" መጽሔትን የምጠይቀው ይህን ነገር ተከታትሎ ጥናት በማድረግ እንዲያስረዳን ነው። ጉበዝ ይህን ዝርፊያውን ሽሽት ዛሬ ስንት ኢትዮጵያዊ የራሱን የባህሉን ዝግጅት እየሸሸ እንዳለ ታውቃላችሁ? ከኔ ጀምሮ። ዋሺንግተንና L.A. ያላችሁ ወገኖቼ ሌሎች እስቴቶች እንዳለነው ምናልባት ላይሰማችሁ ይችላል። ሁሌ ከናንተ ጋር ስለሆኑ ብትጋብዟቸው እንኳ አወዳድራችሁ በማይጐዳ ወጪ ልትዝናኑ ትችላላችሁ። እኛ ዳር ላለነው የጉድ ነው። እስቲ እንተሳሰብ ብላችሁ ምክሩዋቸው።

# ጥቂት ስለ ቋንቋ ዕድገት!

ከየሥራህ ወርቅ

ስለ ቋንቋ ዕድገት ስናወሣ ብዙ አከራካሪ ጉዳዮች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ ሊነሳ የሚችለዉ ደግሞ ማንኛዉም ግለሰብ ወይንም ደግሞ ቡድን የአንድን ቃል የስያሜ አሠጣጥ በሚፈልገዉ ወይንም በመሠለዉ መልክ የሚያቀርበዉ ከሆነና እንደተፈለገዉ መግባባት ሣይችል ሲቀር ነዉ። ይህ ማለት ደግሞ የግለሰቦች ወይንም የቡድኖች የቃላት ስያሜ ለቋንቋ ዕድገት አስተዋጽዎ አያዶርግም ለማለት አይችልም። ይልቁንም እነዚህን አዳዲስ ቃላቶች ለብዙሀን በሚያመች መንገድ በጥልቀትና በዝርዝር ማብራራትን ይጠይቃል። ዋናዉ ቁምነገር ያለዉም እዚህ ላይ ነዉ። በአገራችንም ዉስጥ እኛ ኢትዮጵያዉያን የራሳችን ፊደል ያለን እንደመሆኑ መጠን ቋንቋችንን ለማዳበር ብዙ መወሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች አሁንም ገና የሚቀሩን ቢሆንም የእስከዛሬዉ እንቅስቃሴ ግብ የሚንኳሰስና የሚወገዝ ሣይሆን ለቋንቋችን ዕድገት ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ በመሆኑ ሊበረታታና ሊወደስ ይገባዋል። የሰዉ ልጅ በተፈጥሮአዊ ዕድገቱ ዉስጥ ብዙ አስደናቂ ተግባሮችን እያከናወነ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን ቋንቋዉንም ለማሳደግና ለማበልፀግ የወሰዳቸዉ እርምጃዎች ትልቅ ግምት ሊሰጣቸዉ የሚገቡ ናቸዉ። በኢትዮጵያችንም ዉስጥ በአሁኑ ወቅት ካለንበት ደረጃ አንፃር ለቃላት የተሰጠዉ ቀጥተኛና ተገቢ ትርጉም በፍፁም ሊያኰራን ይገባል። በመሆኑም እነዚህን ቃላት የማብራራት ሥራ በዚሁ መጽሔት በመጀመሩ አድናቆቴን እየገለጽኩ፤ እኔም የተወሰኑ ቃላትን ከእንግሊዘኛዉ ፍቺ ጋር ልኬአለሁ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሙአለ ንዋይ | Investment | ግዛተ አፄ | empire |
| ሁለንተናዊ | universal | ሕውስታ | sensation |
| ልባዌ | perception | ተገብሮት | effect |
| ንድፈ ሀሳብ | theory | ዋርድዮች | guards |
| መፈብረክ | manhfacture | ኑባሬ | being |
| ሕሱም | ugly | ሀሳዊ መሲሕ | demagogue |
| ቅራኔ | contradiction | ግንዛቤ | cognition |
| ነጽሮት | contemplation | መሪር | tragic |
| ሚና | role | ማዕቀብ | sanction |
| መድልዎ | segregation | ገገማ | recovery |

---

## "ይሰውረን!!"

ከእሼቱ ሙላቱ
መድኃኒያለም ት.ቤት፤ አዲስ አበባ

ከጡንቻ ራስ ምሁር፣
ከአደንቁር ዲስኩር፣
ከፖለቲካ ራስ ምታት፣
ከአደባባይ ላይ ቅጥፈት፣
ከእኔ አውቃለሁ ባይ ተኮፋሽ፣
በልቶ ከማያስመሰግን አመድ አፋሽ።
ይሰውረን!!

ከመጥፎ ጠረን ወዝ፣
ከደራሽ ወንዝ፤
ከሽማግሌ ቀጣፊ፣
ከበሽታ ቀጣፊ፤
ከሚያፈስ ጐጆ ጣራ፣
ከፈነዳ ስገራ።
ይሰውረን!!

ካልታሰበ ምላጭ ኪስ አውላቂ፣
ከጓደኛ እየሳቀ አጥቂ፣
ከሴት ልጅ እርግጫ፣
ከወንድ ልጅ አልጫ፣
ከመቀርቀሪያ አልባ ቤርጐ፣
ከሰነባበተ እርጐ።
ይሰውረን!!

ከመርከቶ ግርግር፣
ከዝሆኔ እግር፤
ከድምጸ ደረቅ ዘፋኝ፣
ከአይናውጣ ለማኝ፤
ቶሎ ከማያፈላ ጀበና፣
አረፋ ከሌለው ሳሙና።
ይሰውረን!!

 # ቢስቁም ባይስቁም 

## « ጉርድ እኮ ነው !»

ከእሸቱ ፀጋዬ
(ዋሺንግተን ዲ ሲ)

ሰውዬው ጦር ሜዳ አምስት ዓመት ቆይቶ ወደ ትውልድ አገሩ ሲመለስ ባለቤቱ ሁለት ልጆች ወልዳ ጠበቀችው።

ባል በመናደድ "ይህንን ልጅ ከየት ነው ያመጣሽው?" ብሎ በቁጣ ይጠይቃል።

ሚስት፤ " ምነው ዘመቻ ስትሄድ አስረግዘሽኝ አይደል የሄድከው?" ትለዋለች።

ባል፤ "አ ይቅርታ፣ ልክ ነሽ አስታወስኩኝ። እሺ እሱስ ይሁን፤ ይህን ሁለተኛውንስ ከየት አመጣሽው?" ይላታል።

ሚስት፤ "ሽረ! አሁንስ አበዛሽው። ምነው አንድ ጊዜ በመሐሉ ፎቶሃን አላከልኝም?" ትመልስለች። ባል፤ (በቁጣ) "ታዲያ እኔ የላኩልሽ ጉርድ ፎቶ አይደለም እንዴ?" አላት ይባላል።

## « አፍረን ነው »

ከዑመር መሐመድ
(አዲስ አበባ)

ሌባ አንድ ሰው ቤት ውስጥ ሌሊት ይገባል። የቤቱ ባለቤት ሚስቱን ሌባ ገብቷልና ቁም ሳጥን ገብተን እንደበቅ ብሏት ተያይዘው ቁም ሳጥኑ ውስጥ ይደበቃሉ።
ሌባ ሆዬ ያንጐዳጉድ ያንጐዳጉድና ምንም የሚሰረቅ ያጣል። ግራ ገባውና ጥቂት አሰብ አደረገ።
"ለምን ቁም ሳጥን ከፍቼ አላይም?" ይልና ከፈት ቢያደርገው ባልና ሚስት ቁልጭ፣ ቁልጭ ሲሉ ያገኛቸዋል።
ሌባው ደንግጦ ፈራ ተባ እያለ፤ "ምን ታደርጋላችሁ?" ብሎ ይጠይቃል።
ባልም በመቅለስለስ፤ "አአይ! የመሚሠረቅ ዕቃ ስለሌለነን አፍረን ነው ብሎ ይመልስለታል።

## « ስለጠቀስከኝ!»

ሀብቴ በርሔ
(ከሳንፍራንሲስኮ)

አንድ ሁለት ዓይኑን የታወረና ሌላው ከጉልበቱ በታቸች ሁለት እጋሩን የተቆረጠ በጓደኝነት የሚኖሩ ዓይነስውሩ እግረ ቆራጣውን በጫንቃው በሽኮኮ ተሸክሞ ሲዞር አንድ ሴት በአጠገባቸው አልፋ ኖሮ ዓይነ ስውሩ ወዲያው፤

"አሁን ያለፈችው ሴት ቆንጆ ናት መሰለኝ?" ብሎ ቆራጣ ጓደኛውን ይጠይቀዋል።

ቆራጣውም በመደነቅ፤" አታይ፣ ሳታያት ደግሞ ሴት መሆኗን በምን አወቅህ?" ቢለው፣

ዕውሩም መለስ አድርጐ፤ " ከመሐል ባለው እግርህ እንገቴን ስለጠቀስከኝ ነው።" ብሎ መለሰለት ይባላል።

## « ያው ነው!»

ግርማ ዘገዬ (ዲካልብ)

ለማኝ፤ "እባክዋን ጌታዬ እህል ከቀመስኩ
3 ቀኔ ነው።"
ሰካራም፤ (እየተኮላተፈ) "ምንእሳሰበህ?፣
የእህል ጣሙ ያው እንደድሮውነው፤
አልተቀየረም።" ብሎት እየተንገዳገደ
መንገዱን ቀጠለ።

## « ሽረ እኔ ቴ! »

ከገረሱ

መምህር፤ "እየኮረጅክ ነው እንዴ?"

ተማሪ፤ " አአይ! ሽረ አይደለም ቲቸር፤
የኔ ትክክል መሆኑን እያረጋገጥኩ ነው።"

# ቢስቁም ባይስቁም

## « የኔም ያችውና ! »

ሁለት ወንዶች ቆመው ያወራሉ። በርቀት ሁለት ሴቶችበእነሱ አቅጣጫ ሲመጡ ተመለከቱ።

በዚህ ጊዜ አንደኛው፤ " ዛሬ ደግሞ ባለቤቴ ከማን ገገማ ጋር ነው የምትጓዝ?" ይላል።

ሁለተኛውም ቀበል አድርጐ ፤ "የእኔም ባለቤት ያችውና ፣ ከሆነች ጥፍራም ጋር እየመጣች ነው፤" አለው።

## « ነገ ይታወቃል ! »

አንዱ ሊያስተዛዝን ሐዘን ቤት ይሄዳል።

አስተዛዛኝ፤ "በጣም አርጅተው ነበር?"

አዘንተኛ፤ "አዎን !"

አስተዛዛኝ፤ "እንዲያው አዕምሮአቸውን ስተው ኖርዋል?"

አዘንተኛ፤ "እሱን እንጃ ! እንግዲህ ኑዛዜው የሚሰማው ነገ ስለሆነ ያኔ ነው የምናውቀው።" አለ።

## « ክራቫት »

ሁለት ወንዶች ስለ ሚስቶቻቸው ያወራሉ።

አንደኛው፤ "የእኔ ባለቤት በገንዘብ በኩል በጣም ቆጥቃጣ ናት። ታውቃለህ? ባረጀ ቀሚሷ ነው ክራቫት የሰፋችልኝ፤" ይለዋል።

ሌላው* " አንተ ዕድለኛ ነህ። የኔዋ በክራቫቶቼ ቀሚስዋን ሰፋች።" ይለዋል።

'

## « የሐኪሙ ምክር »

ሐኪም፤ "መጠጥ ዕድሜ ያሳጥራል።"

ጠጪ፤ "እውነቶን ነው?"

ሐኪም፤ "የተረጋገጠ ነው። ይልቅ መጠጥ አቁመው ዕድሜዎን ቢያራዝሙ ይሻልዎታል።"

ጠጪ፤ "ልክ ነዎት ዶክተር፤ ትላንት ፊት የምለው አጥቼ ቀኑ ንቅንቅ አልልልህ ብሎኝ ነበር የዋለው።"

## « አይመቻትም ! »

ባለሥልጣን፤ "ይቅርታ አሁን ላነጋግርህ አልችልም አስቀድመህ ከጸሐፊዬ ጋር ቀጠሮ መያዝ አለብህ።"

ባለጉዳይ፤ "ሞክሬአለሁ። 'ምን ጊዜም አይመቸኝም' አለችኝ። ባል ሳይኖራት አይቀርም።"

መጽሔቱ በጊዜ እንዲደርሶት
ገጽ 48 ላይ ያለውን የደምበኝነት
ቅጽ ሞልተው ከክፍያው ጋር
ይላኩ፤

**LANDAFTA**
**P.O.BOX 49301**
**Atlanta, GA 30359**

# ጨዋታና ሰንጠረዥ

የ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፱ ሰንጠረዥ የመለሱ

ዳዊት አሰፋ (አ.አ)
አስቴር አበበ (አ.አ.)
ሐረገወይን ሽቶ (አ.አ.)
ይፍቱሥራ እንግዳ (አ.አ.)


የ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ሰንጠረዥ የመለሱ፤

ምስክር ተገኔ (ዶዶላ/ባሌ)
ታከለ ኃይሌ (አ.አ.)
ማንያዘዋል ጌታቸው (ደደር/ሐረርጌ)
ዮሴፍ ንጉሤ (ደቡብ ሸዋ)
አፈወርቅ ሀ.ጊዮርጊስ (ድሬ ደዋ)
ትዕግስት ነጋሽ (አርሲ ነገሌ)
ወይንዬ ማርያም (ዳላስ)
ይገደብ አባይ (ዳላስ)
ግርማ ታፈሰ (ሲያትል)
ስንታየሁ ተሰማ (አ.አ.)
ገብሬል መካሻ (አ.አ.)
አበበ አደፍርስ (አ.አ.)
መንግሥቱ ዓለሙ (አ.አ.)
ገብረእግዚአብሔር ዓለሙ (አ.አ.)
ታዬ ጥበቡ (አ.አ.)
ተፈራ ወርቁ (አ.አ.)
አምሐ ይትባረክ (አ.አ.)

የአለፈው ሰንጠረዥ መልስ፤

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢ 1 | ካ 2 | ተ 3 | መ 4 | | | መ 7 | ቀ 8 | የ 9 | ጥ 10 |
| ን 11 | ማ 12 | ር 13 | ቶ 14 | ኢ 15 | ለ 16 | | ሬ 18 | ሥ 19 | ና 20 |
| ጎ 21 | ል 22 | ብ 23 | ዩ 24 | | ኢ 26 | ባ 27 | ሊ 28 | ጋ 29 | ፋ 30 |
| ል 31 | በ 32 | | ጣ 34 | ው 35 | ን 36 | ፋ 37 | | ነ 39 | |
| | ጣ 42 | ው 43 | ለ 44 | | ደ 46 | መ 47 | ፋ 48 | ነ 49 | ው 50 |
| ኢ 51 | | ከ 53 | ፋ 54 | ገ 55 | ነ 56 | ጠ 57 | ል 58 | | ከ 60 |
| መ 61 | ጋ 62 | ጥ 63 | | ለ 65 | ፋ 66 | ጥ 67 | ቅ 68 | | ል 70 |
| ለ 71 | ጋ 72 | | ለ 74 | ጠ 75 | | ም 77 | | ሴ 79 | ፋ 80 |
| ካ 81 | ታ 82 | ወ 83 | ቀ 84 | ወ 85 | | | ቀ 88 | ረ 89 | ና 90 |
| ተ 91 | | ፍ 93 | ፍ 94 | | ሀ 96 | ደ 97 | ፊ 98 | ፎ 99 | |

እንዳለፈው ቃላት በሰንጠረዥ ጨዋታ ነው የሚጫወቱት። በእንግሊዝኛ ለተጻፈው የአማርኛ ትርጉሙን በመስጠት፤ በአማርኛ ተጽፎ ባዶ ቦታ ለተተወው ስሜት በሚሰጥ የአማርኛ ቃል ሰንጠረዡን ይሞላሉ። መልሱን በሚቀጥለው እትም እናወጣለን። በትክክለ ሠርተናል የምትሉ ስምና አድራሻ ላኩልንና እናወጣዋለን።



## ወደጎን

1. ያልደረሰ ጠላ
5. from the past
11. pumpkin
14. tatoo
19. ልፈልግ
23. cover
27. ______ ቃሪያ
31. ቁጭ ሳትል
39. ሰውዬው በሌለበት ስለሱ አወራ
44. great ones
49. got fertile
51. if he stays
55. what?
58. blind
61. he kissed you
65. go between
72. piled up
77. forgetful
83. for the fool
87. it will pass
91. for you (plural)
96. vapor
99. fool

## ወደጎን

1. የ"ፍቅር እስከ መቃብር" ገጸ ባህሪ
2. handicap
4. የአማርኛ መዝናኛ መጽሔት
6. he lost weight
7. don't steal
9. he said,"look for it."
10. dog
15. cooperative
23. thread
32. hanged himself
40. መዋብ
45. I have a cow
46. throat
51. got thinner
53. where did we stay
58. cry
67. ኢትዮጵያን የወረረ
74. for the dead
79. if it burns
80. ______ ያለ ድምጽ
81. he said

(መልሱን ሲልኩ በዚህ ጀርባ ያለውን የደምበኝነት ቅጽ ሞልተው መላክ አይርሱ)

## የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ለመሆን ወይም በስጦታ ለመላክ

የላንዳፍታ መጽሔት ልክ እንደወጣ በፖስታ ቤት እንዲደርስዎ የሚቀጥለውን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።
አከፋፈል፤ - ለአራት ተከታታይ እትሞች

| | | |
|---|---|---|
| ለ | U.S.A. | $12.00 |
| ለ | Canada | U.S.$15.00 |
| ለ | Europe | U.S.$18.00 |

---

## የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

NAME ____________________

ADDRESS ____________________

CITY/STATE/ZIP ____________________

PHONE ____________ ____________

BACK ISSUE ORDERS ____________________

.......................................................................................................

## ላንዳፍታ መጽሔትን ለጓደኛ፣ ለዘመድ ይላኩ፤ የቤተሰብ መጽሔት ናትና፣

NAME ____________________

ADDRESS ____________________

CITY/STATE/ZIP ____________________

PHONE ____________ ____________

BACK ISSUE ORDERS ____________________

---

የሚያዙዋቸውን መጽሔቶች ክፍያ Payable to LANDAFTA በማለት ከቅጹ ጋር በአድራሻችን ይላኩ። እባክዎን አድራሻዎን ሲጽፉ ጉልህ ያድርጉት። ክፍያው በቼክ ወይም በMoney Order ሊሆን ይችላል። ያለፉትን እትሞች ለማዘዝ ከፈልጉ ይህንኑ በቅጹ ላይ ይጥቀሱ።

**LANDAFTA**
**P.O.BOX 49301**
**Atlanta, GA 30359**

# በላንዳፍታ ማስታወቂያ ማውጣት ለሚፈልጉ

በአጭር ጊዜ ዝናን ያተረፈችው የአማርኛ የመዝናኛ መጽሔት ላይ
ድርጅቶን ወይም የንግድ ሥራዎን ያስተዋውቁ።

ማስታወቂያዎን በአማርኛ ተርጉመን ቆንጆ ቅርጽ (Design) በመስጠት እናወጣዋለን።

ጠቅላላ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮጳና በኢትዮጵያ አከፋፋዮች ስላሉን ለብዙ ኢትዮጵያኖች የምትዳረስ
መጽሔት መሆኗን አይዘንጉ።

ክፍያችን ከሌሎች በጣም ያንሳል።

ለአንድ እትም የማስታወቂያ ዋጋችን እንደሚከተለው ይሆናል።

1. ለ 1/4ኛ ገጽ - $45.00
2. ለ 1/2ኛ ገጽ - $80.00
3. ለሙሉ ገጽ - $130.00
4. ገጽ ሽፋን ከውስጥ (ፊትለፊት) - $150.00
   (ከጀርባ) - $140.00
5. ገጽ ሽፋን ከውጭ (ጀርባ) ከለር- $300.00

(Camera Ready ለሆኑና ትርጉምና የመሳሰሉትን የእኛን ምንም ሥራዎች ለማይጠይቁ ማስታወቂያዎች ከላይ ከጠቀስነው ዋጋ 10% እንቀንሳለን። (ዋጋዎች ወደፊት እንደየሁኔታው ይቀየራሉ)
ማስታወቂያ ማውጣት የምትፈልጉ ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ በመሙላት ከክፍያው ጋራ ትልኩልናላችሁ።

------------------------------------------------------------

## የላንዳፍታ ማስታወቂያ ማዘገ

ስም፤- ____________________

አድራሻ፤ ____________________

____________________

ስልክ ቁጥር፤ __________ __________

የሚፈልጉት

ገጽ፤ ____________________

የእኛን ሥራ ይጠይቃል __________ አይጠይቅም (Camera ready ነው __________

ክፍያው $ __________ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተልኳል።

የሚከፈለው በቼክ ወይም በ Money Order Payable to LANDAFTA ተብሎ ነው።

**LANDAFTA**

**P.O.BOX 49301**

**Atlanta, GA 30359**

ለማንኛውም ጥያቄ በስልክ ቁጥር (404) 728-9122 እነጋግሩን።

# Live Reggae

# THE WILD HARE

**& SINGING ARMADILLO FROG SANCTUARY**




# CHICAGO

**(312) 327 - Hare**